ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ከ2008-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ የተመረጡ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖች አንድምታ

በ

አፀደማርያም ሙሉአለም

ሰኔ 2014 ዓ.ም.

ጅማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ከ2008-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ የተመረጡ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖች አንድምታ

ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አፀደማርያም ሙሉአለም

አማካሪዎች

ዶ/ር ለማ ንጋቱ (ዋና አማካሪ)

ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ (ረዳት አማካሪ)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ከ2008-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ የተመረጡ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖች አንድምታ

ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አፀደማርያም ሙሉአለም

የፈተና ቦርድ አባላት

የዋና አማካሪ ስም ____________________ ፊርማ ______________

የረዳት አማካሪ ስም ____________________ ፊርማ ______________

የውስጥ ፈታኝ ስም ____________________ ፊርማ ______________

የውጭ ፈታኝ ስም ____________________ ፊርማ ______________

# ምስጋና

በቅድሚያ የሁሉም ነገር ጅማሬዬና ፍፃሜዬ ባለቤት ፈጣሪዬ ይመስገን፡፡ በመቀጠል ርዕስ ከመረጥኩበት ቀን ጀምሮ ትልመ ጥናቴን በመከታተልና በማረም ዋናውን ፅሁፍ ሰርቼ እንዳቀርብ ለረዱኝ አማካሪዬ ዶ.ር ለማ ንጋቱ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ለረዳት አማካሪዬ ዶ.ር ጥበቡ ሽቴ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ ጥናቱን ሳዘጋጅ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በመጠቆምና ስደክም በማበርታት ከጎኔ ላልተለያችሁኝ ውድ ጓደኞቼ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በመጨረሻ በልዩነት የማመሰግንሽ ልዩዋ እናቴ ገኒዬ በኔ ምክንያት ስላሳለፍሻቸው ነገሮች ሁሉ ችሎታዬ ማመስገን ብቻ ነው፡፡ አመሰግናለሁ!

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ከ2008-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ የተመረጡ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖች አንድምታ በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ዋና ዓላማው የዘፈኖቹን አንድምታ መተንተን ነው፡፡ ንዑሳን ዓላማዎቹ ደግሞ የዘፈኖቹን የጋራ ጭብጥና አንድምታ ማብራራት፣ ዘፈኖቹ የወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነትና ማህበረሰባዊ ስሜት እንዴት እንደገለፁት መመርመር፣ የዘፈኖቹን ማህበረ ፖለቲካዊ ፋይዳ መግለፅ የሚሉት ናቸው፡፡ ጥናቱ በገላጭ የምርምር አይነትና በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ የቀረበ ሲሆን የመተንተኛ ንድፈ ሀሳቡን የሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ንድፈ ሀሳብን (New historicism theory) እና አውዳዊ ንድፈ ሀሳብን (contextual approach) ተጠቅሞ መረጃዎቹን ተንትኗል፡፡ በዚህ መልኩ የተተነተኑት መረጃዎች የሚያሳዩትም ለጥናቱ በተመረጠውና እንደየወቅቱ ፖለቲካዊ ድባብ በሶስት ምድብ ተከፋፍሎ በቀረበው የጊዜ ክልል ውስጥ የተዘፈኑት ሁሉም ዘፈኖች አንድምታ በተለያየ መልኩ ትርጓሜ የሚሰጣቸው እንደሆነ ነው፡፡ በሁሉም ዘፈኖች ውስጥ የተካተቱት ግጥሞች ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር በርካታ ፍቺዎችን የያዙና በዚያው ልክ ለማህበረ-ፖለቲካው ያበረከቱት ጠቀሜታ በተለያየ መልኩ የተገለጠ ነው፡፡ በጥናቱ እንደተረጋገጠው ዘፈኖቹ የማህበረሰብን ስሜት በመጋራት ለውጥ ሽቶ ሲወጣ ለማጠንከርና ትግሉ እንዳይቀለበስ፣ ተቃውሞና ትግሉ ለውጥ ሲያስገኝና ህዝብ ሲደሰት ያንኑ የማህበረሰብ ስሜት አጉልቶ ለማሰማት፣ ተስፋ ሰንቆ ተስፋውን ሳያገኝና እርካታ ሳይሰማው ሲቀር ተስፋ ያሳጣውን ጉዳይ በአንክሮ በመመልከት ዳግም ቅሬታን ለማስተጋባት ውለዋል፡፡ የዘፈኖቹ ዋናው ማህበረ-ፖለቲካዊ ተግባር የነበረውም ትችት፣ ተቃውሞና ውዳሴ ነው፡፡ ውዳሴው በጥናቱ በተለያየ መልኩ የታየ ሲሆን የመጋቢት 24/2010 ዓ.ም ለውጥን የተመለከተ ነው፡፡ ተቃውሞው ደግሞ ከመስከረም 2008 እስከ መጋቢት 24/2010 ዓ.ም እና ዳግም ከ20011- 2013 ዓ.ም ይታዩ የነበሩትን ዘረኝነትን፣ ኢ-ፍትሀዊነትን፣ የሰብአዊ መብት ጥሰትን፣ ሙስናን፣ የመሪዎችን ገደብ የሌለው የስልጣን ፍቅርን በመተቸት የተቃወሙ እንደሆኑ በጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------------i

አጠቃሎ --------------------------------------------------------------------------------ii

የይዘት ማውጫ ------------------------------------------------------------------------iii

**ምዕራፍ አንድ**

**መግቢያ ------------------------------------------------------------------------------------------1**

1.1. የጥናቱ ዳራ ----------------------------------------------------------------------------------1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ------------------------------------------------------------4

1.3. የምርምሩ ጥያቄዎች ------------------------------------------------------------------------5

1.4. የጥናቱ ዓላማ --------------------------------------------------------------------------------6

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ -----------------------------------------------------------------------------6

1.6. የጥናቱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------------7

**ምዕራፍ ሁለት**

**ክለሳ ድርሳናት ----------------------------------------------------------------------------------8**

2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ መነሻ ----------------------------------------------------------------------8

2.1.1. የዘፈን ምንነት ---------------------------------------------------------------------------8

2.1.2. የዘፈን ፋይዳ ----------------------------------------------------------------------------11

2.1.3. ወቅታዊ ፖለቲካዊ ዘፈኖችና ተፅዕኗቸው -----------------------------------------13

2.1.4. ዘፈንና ፖለቲካ በኢትዮጵያ -------------------------------------------------------14

2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ማህቀፍ ----------------------------------------------------------------------------17

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ------------------------------------------------------------------------19

**ምዕራፍ ሶስት**

**የጥናቱ ስነ-ዘዴ ----------------------------------------------------------------------------------------------23**

3.1. የጥናቱ ዘዴ --------------------------------------------------------------------------------------------23

3.2. የመረጃ ምንጭ -----------------------------------------------------------------------------------------23

3.3. የናሙና አመራረጥ ------------------------------------------------------------------------------------23

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ----------------------------------------------------------------------------24

3.5. የመረጃ አደረጃጀትና የትንተና ስልት --------------------------------------------------------------24

3.5.1. የመረጃ አደረጃጀት ---------------------------------------------------------------------------------24

3.5.2. የመረጃ ትንተና ስልት -----------------------------------------------------------------------------25

**ምዕራፍ አራት**

**የመረጃ ትንተና ------------------------------------------------------------------------------------26**

4.1. ከ2008-2013 ዓ.ም. የነበረው ፖለቲካዊ ሂደት ባጭሩ -------------------------------------------26

4.1.1. ተቃውሞና የተቃውሞ ዘፈኖች ከመስከረም 2008 እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም ----27

4.1.1.1. የወቅቱ ፖለቲካዊ ሁነትና የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ ----------------------------27

4.1.1.2. የዘፈኖቹ አንድምታ ትንተና ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር --------------34

4.1.2. የመጋቢት 24/2010 ዓ.ም. ለውጥ መገኘት የወለዳቸው ደስታና ተስፋ በወቅቱ ዘፈኖች --------------------------------------------------------------------------38

4.1.2.1. የወቅቱ ፖለቲካዊ ሁነትና የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ ----------------------------38

4.1.2.2. የዘፈኖቹ አንድምታ ትንተና ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ----------------46

4.1.3. በለውጡ ባለመርካት ከ2011-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ ዘፈኖች ---------------------------50

4.1.3.1. የወቅቱ ፖለቲካዊ ሁነትና የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ -----------------------------50

4.1.3.2. የዘፈኖቹ አንድምታ ትንተና ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ----------------63

4.2. የዘፈኖቹ ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ ----------------------------------------------------------66

## ምዕራፍ አምስት

**ማጠቃለያና አስተያየት** -------------------------------------------------------------71

5.1. ማጠቃለያ -------------------------------------------------------------------------------------71

5.2. አስተያየት ------------------------------------------------------------------------------------73

ዋቢዎች ----------------------------------------------------------------------------------------------74

አባሪዎች ---------------------------------------------------------------------------------------------78

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

በዚህ ጥናት ከ2008-2013 ዓ.ም. ባለው የጊዜ ክልል ውስጥ የተዘፈኑ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው የተመረጡ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖች አንድምታ ተተንትኗል፡፡ ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ተደራጅቶ የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ አንድ ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ጥያቄዎች፣ ዓላማዎች፣ ጠቀሜታዎችና የጥናቱ ወሰን ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ስለጥናቱ ርዕሰ-ጉዳይ ግንዛቤ የሚሰጡ ፅንሰ-ሀሳባዊ ብያኔዎች፣ ለትንተናው መሰረት የሚሆኑ ንድፈ-ሀሳባዊ ማህቀፎች እና ለጥናቱ ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ጥናቶች የተከለሱበት ነው፡፡ በሶስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ስነ-ዘዴ ሲቀርብ፤ በውስጡ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ ምንጮች፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የመረጃ አደረጃጀትና የትንተና ስልትን አካቶ ይዟል፡፡ በምዕራፍ አራት መረጃዎቹ ተተንትነው አንድምታቸው የተብራራ ሲሆን፤ በመጨረሻው ምዕራፍ ማጠቃለያና አስተያየት ቀርቧል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

አንድ ማህበረሰብ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያለውን አመለካከትና ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፈላጎቱን ለማወቅ ኪነ-ጥበባዊ ስራዎቹን መረዳት ቀዳሚው ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እነዚህ ስራዎች ከሚታየው ነባራዊ ማህበራዊ ጉዳይ የሚቀዱ ስለሆነ ነው፡፡ ዘፈንም አንዱ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ጥበብ ነው፡፡ ዘፈን ከሰው ልጅ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለውና ማህበረሰቡ ከጥንት ጀምሮ በደስታው፣ በሀዘኑ፣ በሀይማኖታዊ በአሉና በሌሎችም የስራ አጋጣሚዎች ሲገለገልበት የቆየ ጥበብ ነው፡፡

የዘፈንን ጥንተ መነሻ አስመልክቶ ግን በርካታ ሀሳቦች ይነሳሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ከፈጣሪ ለሰው ልጆች የተሰጠ ፀጋ ነው እና ራሳቸው የሰው ልጆች በጋራ መኖር ሲጀምሩ ስሜታቸውን በተለየ መልኩ ለመግለፅና ለማጋራት ያስገኙት ጥበብ ነው የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ተስፋዬ (2010፣20) "በቀደመው ዘመን የነበሩ የሙዚቃ ፈጣሪዎች ገበሬዎች፣ እረኞች፣ ደብተራዎችና ሴቶች እንደነበሩ ይነገራል፡፡ እረኛው ከብት በሚጠብቅበት ጊዜ ድካሙን እንዲያቀልለት፣ ገበሬው በሚያርስበት ወቅት ብርታት እንዲሰጠው፣ ሴቶችም አብዛኛውን የቤት ስራ የሚያከናውኑት እነሱ በመሆናቸው ስራቸው እንዲቀላጠፍላቸው እያንጎራጎሩና እየዘፈኑ

ይሰራሉ።" በማለት ስለዘፋኞቹና ስለዘፈኑባቸው ምክንያቶች ይገልፃሉ። Neguss (2018,1-2) ደግሞ Ashenafi, (1971) Amsalu Akelilu,ን (2002) እና Woube kassaye,ን (1995) ዋቢ በማድረግ ስለኢትዮጵያ አለማዊ ዘፈን አነሳስ ሶስት አይነት ሀሳቦች እንዳሉ ያስረዳሉ።

ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው ከሀሜቶ ሴሜቲክ ሰደተኞች ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ የእነዚህ ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ መግባትና ለተለያዩ አምልኮታዊ ከበራዎቻቸው ያቀርቡ የነበረው ዘፈን ለኢትዮጵያ አለማዊ ዘፈን ጅማሮ እንደሆነ ይገልፃሉ። ሁለተኛው የኢትዮጵያ አለማዊ ዘፈን መነሻና እድገት መሰረት ነው ተብሎ የሚታመነው ሀሳብ ደግሞ ከሀይማኖት ጋር የተያያዘ ሲሆን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን የዜማ አባት ተደርጎ ከሚወሰደው ከቅዱስ ያሬድ ጋር ይገናኛል። በመሆኑም የቅዱስ ያሬድ ሀይማኖታዊ የዜማ ስልት ለአለማዊው ዘፈን መነሻ ሲሆን በአለማዊ የሀገረሰብ ዘፈን ዘፋኞች (አዝማሪዎች) በልፅጎ አለማዊ መልክ እንደያዘ ከላይ የተጠቀሱት ምንጮች ይገልፃሉ።

ምንም እንኳ በቂና የተሟላ መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ ቢገለፅም፣ ሶስተኛው ሀሳብ ከንግስት ሳባ ጋር ተያይዞ ከሚነገር አፈ-ታሪክ ጋር የተገናኘ ነው። ለምሳሌ እንደ ተስፋዬ (2010፣68) ገለፃ ከሆነ ንግስት ሳባ ንጉስ ሰለሞንን በኢየሩሳሌም ጎብኝታ ስትመለስ ዘፋኞችንና በተጨማሪም አንዳንድ የሙዚቃ መሳሪያዎችን አምጥታለች። ሀሳቡ ከንግስት ሳባ ጋር የተያያዘውን ገለፃ ከማጠናከሩም በተጨማሪ በበቂ ማስረጃ ላይ ሳይመሰረት "አንዳንድ የቀድሞ ሰዎች ይናገራሉ" በሚል መገለፁ በሶስተኛው ሀሳብ ላይ በቂ መረጃ አለመኖሩን ጨምሮ የሚገልፅ ነው። ይሁንና በሶስቱም ሀሳቦች ላይ አሁንም ድረስ የጋራ የሆነ አረዳድና ስምምነት እንደሌለ ለዚህ ደግሞ አንዱ ምክንያት የመረጃ እጥረት እንደሆነ ተገልጿል። ስለ ኢትዮጵያ አለማዊ ዘፈን ጅማሮ በትክክል ለማወቅ ከባድ እንደሆነ በመግለፅ ሀሳቡን የሚያጠናክሩት ተስፋዬ (2010፣43) "የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ዝማሬ በፅሁፍና በምልክት ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ስለመጣ የተሟላ መረጃ ያለው ነው። የአለማዊው ሙዚቃ ዘፈን ግን በሀይማኖቱ ክፍል የተጠላና የተወገዘ በመሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የተላለፈው በጣም ጥቂቱ ነው።" በማለት ይገልፃሉ።

በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የኢትዮጵያ አለማዊ ዘፈን የተጀመረው በዚህ ወቅትና ሁኔታ ነው ለማለት ቢያስቸግርም አለማዊ ዘፈኖች ፊት ለፊት መገናኘት ሳያስፈልግ በሸክላ ተቀርፀው መደመጥ የጀመሩበትን ጊዜ ማወቅ እንደሚቻል የተለያዩ አጥኚዎች ይገልፃሉ። ይህንንም ተስፋዬ (2010፣25) ሲገልፁ፤ በ1917 ዓ.ም. በነጋድራስ ተሰማ እሸቴ የሚመሩ አዝማሪዎች

ወደ አውሮፓ በመሄድ በበርሊን ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘፈናቸውን በሸክላ ካሳተሙ በኋላ በዚህ መንገድ የሚቀርቡ ዘፈኖች የነበረውን የዘፈን አቀራረብ እየቀየሩት እንደመጡ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ የአዝማሪ ዘፈኖችም የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አገራዊና ታሪካዊ ሁኔታዎችን በማንሳት እያዝናኑ ሙገሳና ትችት የሚሰጡ ነበሩ፡፡ ቀስ በቀስ ደግሞ በአንድ የሙዚቃ መሳሪያ ታጅበው ከሚዘፈኑ ዘፈኖች በተለየ በተደራጀ መልኩ በተለያዩ ሙዚቃዎች የተቀናበሩ አልበሞች መታተም ጀመሩ፡፡ Neguss (2018,2) Woubeን (1997) ጠቅሰው እንደሚገልፁት፤ በአልበም ደረጃ የመጀመሪያ የሆነው ካሴትም በ1974 እ.ኤ.አ. የታተመው የአለማየሁ እሸቴ አልበም ነው፡፡

እነዚህ በሙዚቃና በዜማ የተቀናበሩ ዘፈኖችም መፅሀፍ ላይ ተፅፈው ከምናነባቸው ግጥሞች በተለየ ስሜትን የመግዛትና የድርሰቱን ሀሳብ በዘፋኙ  አማካይነት እንድንጋራ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ግጥምን መፅሀፍ ላይ ተፅፎ ስናነበው ዜማውን ራሳችን እንደተመቸን አድርገን እንቃኘዋለን፡፡ መድረክ ላይ ሲነበብ ስንሰማው ደግሞ የአንባቢውን ዜማ ተከትለን እንሄዳለን፡፡ ይሁንና ራሳችን ከምናነበው ግጥም ይልቅ ደራሲው ሲያነብ የምንሰማው የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም የአንባቢው ድምፀትና ዜማ የሚነግረን አንዳች ነገር በመኖሩ፡፡ ነገር ግን ከሁለቱ በተሻለ በዘፈን ውስጥ የምንሰማቸው በዜማ፣ በሙዚቃ መሳሪያዎችና በድምፃዊያን የተቀናበሩት ግጥሞች (ዘፈኖች) ለስሜት ቅርብ ናቸው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የሙዚቃ መሳሪያዎቹ ምት፣ የዘፈኖቹ ቅኝት፣ የድምፃዊያኑ አዘፋፈንና ዜማ በራሱ ተፅዕኖ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

ይህንን የዘፈንን ለስሜት ቅርብ የመሆንና ተፅዕኖ የማሳደር ባህሪ በመጠቀምም ሰዎች መግለፅ የፈለጉትን ሀሳብ በጠነከረ መንገድ ለብዙ ዘመናት ገልፀውበታል፡፡ አሁንም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አገራዊ ጉዳዮችን ይገልፁበታል፡፡ በተለይም በተለያዩ የአለም አገራት ላይ የተደረጉ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን ስንመለከት ዘፈኖች የማህበረሰብን አስተሳሰብ ምን ያህል መቀየር እንደሚችሉና ጫና እንደሚያሳድሩ እንረዳለን፡፡ አንድን የፖለቲካ ስርአት ለመቃወምና ለመነቅነቅ የተቃውሞ ዘፈኖች ወሳኝ የመሆናቸውን ያህል ስርአቱን ደግፎ ማህበረሰቡን ለማሳመንም የድጋፍ ዘፈኖች ወሳኝነት ይኖራቸዋል፡፡

በአገራችንም በተለያዩ ፖለቲካዊ ስርአቶች ስርአቱን ተቃውመውና ደግፈው የተዘፈኑ ዘፈኖች በርካታ ናቸው፡፡ ይሁንና ለድጋፍ የሚዘፈኑት ዘፈኖች በቀጥታ ስርአቱን የሚያሞካሹ ሲሆኑ በተቃራኒው ለተቃውሞ የሚዘፈኑት ዘፈኖች ግን በድብቅ ቅኔን በተላበሰ መልኩ የሚዘፈኑ ናቸው፡፡ ይህም ከስርአቱ ጠባቂዎች የሚመጣን ጫና ለመቋቋም የሚደረግ ሲሆን በሌላ በኩል

በግልፅ ተቃውሟቸውን አሰምተው ማህበረሰቡን ለተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያነሳሱ ዘፈኖችም በተለያዩ ጊዜያት ተደምጠዋል፡፡ በእነዚህ ዘፈኖች ላይም ሰፊ ጥናትና ምርምር ተደርጓል ባይባልም በተወሰነ መልኩ በውጭ አገርና በአገር ውስጥ አጥኝዎች የተለያዩ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ አጥኝዋ ያገኘቻቸውና የተመለከተቻቸው ጥናቶች ትኩረት ያደረጉባቸው ጉዳዮች የአንድን ዘፋኝ ዘፈኖች ይዘት በተለያዩ የመመደቢያ መስፈርቶች መመደብ፣ የዘፈኖቹን ቅኝት በመመደብ መተንተን፣ የተለያዩ ዘፈኖችን ከፖለቲካዊና ማህበራዊ ገፅታቸው ጋር በማገናኘት መተንተን፣ የታዋቂ ዘፋኞችን ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ዘፈኖችን በመውሰድ በተለያዩ ጊዜያት የነበሩ ፖለቲካዊ ስርአቶችን እንዴት እንደገለፁ መተንተን ላይ ያተኩሩ ናቸው፡፡

እነዚህ ጥናቶች ትንተናቸውን ሲያከናውኑ ከላይ ከተገለፀው ባለፈ በዘፈኖቹ ውስጥ የተካተቱትን መልዕክቶች በማብራራት በተዘፈኑበት ወቅት ከነበረው አውድ አንፃር አንድምታቸውንና ፋይዳቸውን አልተመለከቱም፡፡ የጥናቶቹ ትኩረት የነበረው ዘፈኖቹን በተለያየ መልኩ መመደብና መተንተን ነው፡፡ ይህም ይህንን ጥናት ለማጥናት ገፊ ምክንያት ሲሆን ለጥናቱ በተመረጠው የጊዜ ክልል ከተከሰቱ አበይት ፖለቲካዊ ክስተቶች ውስጥ ማለትም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እያየለ የመጣውን በመንግስት ላይ የተደረገ ህዝባዊ ተቃውሞ፣ እሱን ተከትሎ የመጣውን የመጋቢት 2010 ዓ.ም ለውጥ እና ከዚያ በኋላ እስከ 2013 ዓ.ም. የተከሰተውን አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ አስመልክተው የተዘፈኑ ዘፈኖችን ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር የነበራቸውን አንድምታ በመመርመር የማህበረሰቡን ስሜት፣ ፖለቲካውን እንዲሁም ወቅቱን እንዴት እንደገለፁትና አንድምታቸው ምን እንደሚመስል በመተንተን የተጠቀመውን ክፍተት ለመሙላት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህን ጥናት ለማጥናት አነሳሽ የሆኑት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የግል ተነሳሽነት ነው፡፡ ተነሳሽነቱ የመነጨውም አጥኝዋ በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ አካላት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚዘፈኑ ዘፈኖች መልዕክት የማህበረሰቡን ማህበረ-ፖለቲካዊ ችግር የሚያነሳ አይደለም የሚል ትችት መስማቷና ከትችቱ በመነሳት ለጥናቱ በተመረጠው የጊዜ ክልል ውስጥ በርካታ ማህበረ-ፖለቲካዊ ሁነቶች የተከሰቱ በመሆናቸው በነዚህ ጊዜያት እውን ማህበረ-ፖለቲካውን የተመለከቱ ዘፈኖች አልተዘፈኑም የሚለውን ማረጋገጥ መፈለጓ ነው፡፡ ከተዘፈኑም ደግሞ አንድምታቸው ምን ይመስል ነበር?፣ ያበረከቱት ጠቀሜታስ ምንድን ነው? የሚሉትን ጉዳዮች አያይዛ ማጥናት መፈለጓ ለጥናቱ መደረግ አንዱ ምክንያት ነው፡፡

ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያት በአካዳሚው የሚስተዋለው ክፍተት ሲሆን፤ በዳራው እንደተገለፀው አጥኝዋ የተመለከተቻቸው በተለያዩ የዘፈን ግጥሞች ላይ የተደረጉ ጥናቶች የግጥሞቹን ይዘት ከተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንፃር በማዛመድ መተንተን፣ መመደብ ወዘተ. ላይ ትኩረት ያደረጉ እንጅ የተደረሱበትን አጠቃላይ አውድ መሰረት በማድረግና አንድምታቸውን በመመርመር ለወቅቱ ማህበረ-ፖለቲካ ያበረከቱትን ጠቀሜታ በሚያሳይ መንገድ የተጠኑ አለመሆናቸው ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ በKristin skare orgeret (2008) “When will the day break come? Popular music and political processes in Ethiopia.” **በሚል ርዕስ በዋናነት** በታዋቂው ዘፋኝ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ፖለቲካዊ ዘፈኖች ላይ የተደረገ ጥናት ሲጠቀስ በጥናቱ ዘፋኙ በዘፈኖቹ የተነሳ የተለያዩ ጫናዎች ቢደርሱበትም የየወቅቱን ፖለቲካዊ ስርአት በመተቸት፣ ይበጃል የሚለውን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ በዘፈኖቹ በማንፀባረቅ (በተለይም ጃ ያስተሰርያል በሚለው ዘፈን) እና የህዝብ ድምፅ በመሆን ስራዎቹን ሲያቀርብ እንደቆየ የተተነተነበት ነው፡፡ ሌላው የናርዶስ (2006) “በቴዲ አፍሮ ዘፈኖች ላይ የይዘት ትንተና” የሚል ጥናት ሲሆን የዘፈኖችን ይዘት መመደብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በNeguss (2018) “Tematic analysis of selected Amharic song lyrics: a sociological approach.” **በሚል** የተደረገው ጥናትም የተመረጡ የአማርኛ ዘፈን ጭብጦችን ከማህበራዊ ገፅታቸው አንፃር የተነተነ ነው፡፡ እነዚህና መሰል በአጥኝዋ የተቃኙ ጥናቶች ደግሞ የዘፈኖቹን ትንተና ከተለያየ ነገር አንፃር ያደረጉ ቢሆንም የዘፈኖቹን አንድምታና ጠቀሜታ የገለፁ አለመሆናቸው ለጥናቱ መደረግ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ግን ርዕሰ ጉዳዩ ወቅታዊ መሆኑና ከወቅታዊነቱ ጋር ተያይዞ በተለይም በተመረጠው የጊዜ ክልል ውስጥ የተካሄዱ ሌሎች ይህን መሰል ጥናቶች ባለመኖራቸው ለዘርፉ አዲስ ነገርን እንደሚያበረክት በአጥኝዋ መታመኑ ለጥናቱ መነሻ የሆኑ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የሚከተሉትን መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

- የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ ምን ይመስላል?
- የዘፈኖቹ አንድምታ ምንድን ነው?
- ዘፈኖቹ የወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነትና ማህበረሰባዊ ስሜት እንዴት ገለፁት?

- የዘፈኖቹ ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ ምንድን ነው? የሚሉት ሲሆኑ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስም የሚከተሉት ዋና እና ንዑሳን ዓላማዎች ተነድፈዋል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከ2008-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ የተመረጡ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖችን አንድምታ መመርመር ነው፡፡ ንዑስ ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ ምን እንደሚመስል መግለፅ፤
- የዘፈኖቹን አንድምታ ማብራራት፤
- ዘፈኖቹ የወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነትና ማህበረሰባዊ ስሜት እንዴት እንደገለፁት መተንተን፤
- የዘፈኖቹን ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ መግለፅ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ዋናው ጠቀሜታ በዳራውና በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የተገለፁትን ክፍተቶች ማለትም አጥኚዋ የተመለከተቻቸው በዘፈኖች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያልተመለከቱትን የፖለቲካዊ ዘፈኖችን አንድምታ ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር በመተንተንና ማህበረ-ፖለቲካዊ ጠቀሜታቸውን በመግለፅ ለዘርፉ አንዳች አስተዋፅኦ ማበርከት ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳዩ ወቅታዊነትና በርዕሰ ጉዳዩ ሌሎች ጥናቶች ካለመደረጋቸው ጋር ተያይዞ ደግሞ የሚከተሉት ተጨማሪ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ እነዚህ ጠቀሜታዎችም በመጀመሪያ አገሪቱ ያለፈችበትን ወቅታዊ ሁኔታና ዘፈኖቹ ያበረከቱትን ፋይዳ ቀርሶ ለማቆየትና ለተተኪው ለማስተላለፍ ይጠቅማል፡፡ እንዲሁም ዘፈኖች አንድን ፖለቲካዊ ስርአት በመተቸትም ሆነ በማሞገስ ለቀጣይነቱም ሆነ ለውድቀቱ የሚኖራቸውን ሚና ለጥናቱ በተጠቀሰው የጊዜ ክልል በተዘፈኑ ፖለቲካዊ ዘፈኖች ማሳያነት ይገልፃል፡፡ በተጨማሪም ርዕሰ ጉዳዩን አስመልክቶ ሰፊ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ የዘርፉ አጥኚዎችና ለሌሎች ተዛማጅ የትምህርት ክፍል አጥኚዎች እንደ ግብአት ሊሆን ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከ2008-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው የተመረጡ የአማርኛ ዘፈኖችን አንድምታ መተንተን ላይ የተገደበ ነው፡፡ ይህም ሲባል በጊዜ በተጠቀሰው ዘመን ውስጥ የተዘፈኑትን የተመረጡ ዘመናዊ ዘፈኖች ሲመለከት በርዕሰ-ጉዳይ ስፋት በአማርኛ ዘፈኖች ላይ ተመስርቶ ከነበሩት ፖለቲካዊ ሁነቶች አንፃር ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እየጠነከረ የመጣውን የለውጥ ፍላጎት፣ ከዚያም በ2010 ዓ.ም መጋቢት ወር የተገኘውን ለውጥ እና 2011 ዓ.ም. በኋላ ስለነበረው አጠቃላይ ፖለቲካዊ ሁኔታ የተዘፈኑትን ዘፈኖች ብቻ አንድምታቸውን በመተንተን ካበረከቱት ፋይዳ ጋር አያይዞ በጥልቀት ያጠናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ በወቅቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ከተዘፈኑ ዘፈኖች ውስጥ በአማርኛ ዘፈኖች ላይ ሲወሰን ይህም የአጥኝዋን የቋንቋ ችሎታና ለጥናቱ ያለውን ጊዜ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ በርዕሰ-ጉዳይ አስር ፖለቲካዊ ዘፈኖች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በዘፈኖቹ ውስጥ የተካተቱ ግጥሞችን እንጅ ምስሉን፣ ቅንብሩን፣ ዜማውን፣ ድምፀቱን፣ወዘተ. እና ከዘፈን ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ጉዳዮችን አይመለከትም፡፡ ጊዜው ከ2008-2013 ዓ.ም. የተመረጠበት ምክንያትም በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በርካታ አገራዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች በመከሰታቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት ርዕሰ ጉዳዮች ቀርበዋል። እነሱም ስለተነሳው ርዕሰ ጉዳይ የተሻለ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ፅንሰ ሀሳቦች፣ ለትንተናው መሰረት የሚሆኑ ንድፈ ሀሳቦች እና ለጥናቱ ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ጥናቶች ናቸው።

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ መነሻ

በዚህ ርዕስ ውስጥ በጥናቱ ትኩረት ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች የተሻለ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔዎች ይቀርቡበታል።

### 2.1.1. የዘፈን ምንነት

በመጀመሪያ የዘፈንን፣ የሙዚቃንና የግጥምን ምንነት፣ ልዩነትና አንድነት ማየት ያስፈልጋል። በአብዛኛው በእነዚህ ፅንሰ-ሀሳቦች ላይ ያለው አረዳድ የተለያየ ነው። ቢሆንም ግን በአብዛኞቹ የዘርፉ ሙሁራን የተሰጡትንና የሚያስማሙትን ሀሳቦች በመመልከት ፅንሰ-ሀሳቦቹን ለመግለፅ ይሞከራል።

ሙዚቃ የሰው ልጆች ከሚያጫውቷቸው የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች በተለያየ መንገድ ተቀናብሮ የሰዎችን ስሜት በሚገዛ መልኩ የሚወጣ ጣፋጭ ድምፅ ነው። ሙዚቃን አስመልክቶ ብርሀኑ (1999፣19) "ሙዚቃ የድምፃዊ ምስሎች ጥበባዊና ስልታዊ ቅንብር ነው።" ካሉ በኋላ ሙዚቃ የጥበባት መሰረት እንደሆነ ገልፀው አንድም ብቻውን ሊቆም (ራሱን ችሎ ሊደመጥ)፣ አንድም ደግሞ ዳንስንና ውዝዋዜን አብሮ ሊያስኬድ፣ በሌላ በኩልም አንደበትን አንቅቶ ዜማዊ ንግግርን ሊያመነጭ ወይም በሚዜሙ ግጥሞች ተቀናብሮ ሊደመጥና ሊታይ እንደሚችል ያብራራሉ። ይህን የሚጋሩት Neguss (2018,19) Meyerን (2012) ጠቅሰው ሙዚቃ የራሱ የሆኑ መገለጫዎች እንዳሉትና ራሱን ችሎ ሊደመጥ እንዲሁም ደግሞ ከዘፈን (ከዘፈን ግጥሞች) ጋር ተቀናብሮ ሊዘጋጅና ሊደመጥ እንደሚችል በመግለፅ ሀሳቡን ያጠናክራሉ።

ዘፈንን ደግሞ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት (1993፣443) "አለማዊ የሆነ ዘፈን፣ ዜማ፣ እንጉርጉሮ" በማለት ይበይነዋል። ዘፈን በሙዚቃና ከሰው ልጅ በሚወጡ

ዜማ ያላቸው ግጥማዊ ቃላት ተቀናብሮ የሚቀርብ ጥበባዊ ውህደት ነው፡፡ በዚህም ዘፈን አንዱ የሙዚቃ አካል እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህን ሀሳብም Masriyah and et al (2019, 172) "a song is a part of the music." በሚል ይገልፁታል፡፡ እንዲሁም ደግሞ Yastanti and Susilawati (2020,142) Guera ን (2015) ጠቅሰው ዘፈን በግጥሞችና በሙዚቃ የተዋቀረ እንደሆነ ግጥሞቹም የሚያስተላልፉት አንድ መልዕክት እንዳለ ይህ መልዕክትም በሰዎች ላይ አንዳች ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ዘፈን የሚለው ቃልና የዘፈን ግጥም የሚለው ሀረግ ተመሳሳይ እንደሆኑ ሲሆን በርካታ ሙሁራንም ይህንኑ ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ Muldoon (2013,168) "The word song is defined as a short poem or other set of words set to music or meant to be sung." በማለት ዘፈን የሚለው ቃል አጭር ግጥም ወይም ሌላ ለሙዚቃና ለመዘፈን የተቀናጁ የቃላት ስብስብ እንደሆኑ በመግለፅ ዘፈንን ባጭሩ ‹አጭር ግጥም› ነው ይሉታል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የዘፈን ግጥም በሌላ አገላለፅ ዘፈን ተብሎ መጠራቱን የሚያሳይ ነው፡፡ በPatria, Rendi, Abdurahman and Nasution (2013,1) የተገለፀው ሀሳብም ዘፈን ግጥሞችን የሚያካትት ሙዚቃዊ ዝግጅት እንደሆነና የሚዘፈኑት ግጥሞች ከሙዚቃ ጋር ተዋህደው የዘፈን ደራሲውን ስሜት እንደሚገልፁ በማስረዳት የላይኛውን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡

በመቀጠል ደግሞ የዘፈንን እና የግጥምን ምንነት፣ ልዩነትና አንድነት እንመልከት፡፡ በስነ-ግጥም ውስጥ ከሚታወቁት ሶስት የስነ-ግጥም አይነቶች ውስጥ አንዱ ሌሪክ (Lyric) ነው፡፡ ብርሀኑ (1999) እንደሚገልፁት ሌሪክ ማለት ስሜት ንክር የዘፈን ግጥም ማለት ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ ተራኪ እና ተውኔታዊ በመባል ይታወቃሉ፡፡ በብዙ ቦታዎችም ከተራኪና ከተውኔታዊ ግጥሞች ውጭ ያሉት በሙሉ ሌሪክ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ ሌሪክ የሚለው ቃል ግሪኮች ‹‹ሌይራ›› በማለት ከሚጠሩት የሙዚቃ መሳሪያ የተገኘ ሲሆን በትርጓሜውም የዘፈን ግጥም የሚለውን ሀሳብ ይይዛል፡፡ ይህን በተመለከተ Neguss (2018,20) Cuddon ን (1999,481) ጠቅሰው ግሪኮች የሚዘፈነውን ግጥም ሌይረ ወይም ሌይራ ከተሰኘ መሳሪያ ጋር ታጅቦ የሚዘመር ዘፈን በማለት እንደሚገልፁት ያስረዳሉ፡፡

ምንም እንኳን ዘፈንን ከሌሎች የግጥም አይነቶች ለመለየት አስቸጋሪ ቢሆንም ልዩ የሚያደርጉት የራሱ ውስን ባህርያት አሉት፡፡ ይህንንም Sheila Davis (1985,6) "በሙያው የተካኑ የዘፈን ደራሲዎች ዘፈኖችን ሌሪክ እንጅ ግጥም በማለት አይገልጿቸውም፡፡ ከሙያው ውጭ ያሉ ሰዎች ግን ብዙውን ጊዜ ሁለቱንም ቃላት እንደተመሳሳይ እያቀያየሩ ይጠቀማሉ፡፡"

በማለት በሙያው የተካኑ ዜማ ደራሲዎች ዘፈኖችን ሌሪክ (ስሜት ንክር የዘፈን ግጥም) በማለት እንደሚጠሯቸው ከሙያው ውጭ የሆኑ ሰዎች ግን ዘፈኖችን ከሌሎች ግጥሞች በተመሳሳይ እንደሚጠቀሙባቸው ይገልፃሉ፡፡

በተጨማሪም ዘፈኖች ከሌሎች ግጥሞች የሚለዩበትን ጉዳይ Sheila Davis (1985,7) ሲያስረዱ ዘፈኖች (የዘፈን ግጥሞች) እንደሌሎቹ ግጥሞች ከተደረሱ በኋላ ስራቸው የሚያልቅ አይደለም፡፡ ይልቁንም ከግጥሙ ድርሰት በኋላ የዜማ ደራሲ፣ ግጥሙን ከሙዚቃ ጋር የሚያዋህድ አቀናባሪ፣ ግጥሙን የሚያዜም ጥሩ ድምፃዊ ወዘተ. ያስፈልጉታል፡፡ ግጥሙ በሚደረስበትም ሆነ በሚዘፈንበት ወቅት ግልፅና ቀጥተኛ መሆን ሲኖርበት ዘፋኙ ሲዘፍንም የማይሰሙ ቃላት መኖር የለባቸውም፡፡ ሌላውና ዋናው ጉዳይ የዘፈን ግጥም ለመዘፈን (ለመዘመር) ተብሎ የሚዘጋጅ የግጥም አይነት ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

በሌላ በኩል ግን ዘፈን ከሌሎች ግጥሞች የሚለይበትን መንገድ ነቅሰን ስናወጣ ሁለቱን ለመለየት አስቸጋሪ የሚያደርግ ተመሳስሎ እንዳላቸው በመዘንጋት አይደለም፡፡ Neguss (2018,20) Wickhamን (2010,7) ጠቅሰው ሁለቱም ጥሩና ደረጃውን የጠበቀ የቋንቋ አጠቃቀም ይፈልጋሉ፣ ሁለቱም አንባቢዎቻቸውንና አድማጮቻቸውን በስሜት ይስባሉ/ያሳትፋሉ፣ ሁለቱም ቃላዊ ድምፆችን በብቃት መጠቀምንና ምትን ይፈልጋሉ ካሉ በኋላ አያይዘው ሁለቱም ዘይቤያዊ አነጋገርን፣ ግጥማዊነትን፣ ሰብአዊነትን ወዘተ. የተላበሱ ናቸው በማለት የሰጡት ማብራሪያም ይህንኑ ተመሳስሏቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የዘፈንን ምንነት ስንመለከት ሌሪክ (የዘፈን ግጥም) አጭርና ዝማሬያዊ የሆነ፣ ከመዝሙርና ከእንጉርጉሮ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው፣ ከገፀሰቡ ይልቅ የራሱ የገጣሚው ድምፅ የሚሰማበት የግጥም አይነት ነው፡፡ ይህም ሲባል ሌሪክ የራሱን የገጣሚውን ገጠመኝ፣ ስሜትና ህይወት ያንፀባርቃል ማለት ነው፡፡ ብርሀኑ (1999፣383) እንደሚገልፁት፡-

> ሌሪክ ግጥሞች ሙዚቃዊ፣ በእጅጉም ዜማዊ ናቸው፡፡ የሌሪክ ግጥሞች ዜማዊነት ስሜት ንክር ከመሆናቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሌሪክ ድምፀቱ ግላዊ፣ ስሜቱም ጥልቅ በመሆኑ ለልዩ ልዩ የእንጉርጉሮና የመዝሙር ስልቶች የቀረበ ነው፡፡ ሌሪክ የሀዘን እንጉርጉሮ፣ የደስታ መዝሙር፣ የፀሎትና የምህላ፣ የፍቅርና የናፍቆት መብሰልሰል ወዘተ ገነው የሚሰሙበት ስሜት ንክር የዜማ ስልት ነው፡፡

ከገለፃው በመነሳት ይህ የግጥም አይነት ለመዜም እንደሚደረስ፣ በተለያዩ የዜማ ስልቶችና በተለያዩ መንፈሳዊ፣ አለማዊ፣ ግላዊና፣ ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገው የተደረሱ ግጥሞችንም እንደሚያካትት መረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ የዘፈን ምንነት በሚለው ርዕስ ከቀረበው ገለፃ መረዳት የሚቻለው የሙዚቃን፣ የዘፈንንና የሌሎችን ግጥሞች ምንነት እንዲሁም በመካከላቸው ያለውን ልዩነትና አንድነት ነው፡፡

### 2.1.2. የዘፈን ፋይዳ

ቀደም ባለው ጊዜ ሀገረሰባዊ ዘፈኖች ጥሩውን ለማወደስ፣ መጥፎውን ለመንቀፍ ሲያገለግሉ ጥሩ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችን እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን ግለሰቦች ያጠናክራሉ፡፡ ወቅታዊ ጉዳዮችንም ለማንፀባረቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በዚህም በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ወቅታዊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ላይ ትችት ለማቅረብ፣ ጫና ለመፍጠር፣ ለቅስቀሳና ድጋፍን ለመግለፅ ወዘተ. ሲያገለግሉ የህዝብን አመለካከትም በቀላሉ ለማንፀባረቅ፣ ለመቀየር፣ ለማስተማር፣ ለማነሳሳት ይጠቅማሉ፡፡ ልክ እንደዚሁ ሁሉ በዘመናዊ መንገድ የሚቀርቡ ባህላዊም ሆኑ ዘመናዊ ዘፈኖች ተመሳሳይ ፋይዳ አላቸው፡፡

የእነዚህን ዘፈኖች ጠቀሜታ አስመልክቶ Hilina (2020,1) Allyn and Baconን (1969) ጠቅሰው ዘፈኖች ደስታን የመፍጠር (የማዝናናት)፣ የአንድ የተወሰነ ባህል መለያ ውክልና የመሆን፣ ማህበራዊ ደንቦችን የማጣጣም፣ ባህልን የማስቀጠልና የማረጋጋት፣ የማህበረሰብን ውህደት የመፍጠርና የአንዱን ስሜት ለአንዱ ለማስተላለፍ የሚያገለግሉ የመግባቢያ መሳሪያዎች ናቸው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ሀሳቡን የሚጋሩት Theodor (1976,39) በበኩላቸው አብዛኛው ሰው የዘፈን ተግባር ማዝናናት ብቻ እንደሆነ ያስባል፡፡ ነገር ግን የዘፈን ተግባር ማዝናናት ብቻ ሳይሆን በርካታ ሰዋዊ ፋይዳዎችን መወጣትም ጭምር ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

እነዚህ ሰዋዊ ፋይዳዎችም ማዝናናት፣ ማስተማር፣ ማነሳሳት፣ ስሜትን መግለፅ፣ ወዘተ. ናቸው፡፡ Masriyah, Aziz, Samad (2019,172-173) Wahyuን (2017) ጠቅሰው ዘፈኖች አድማጮችን ያዝናናሉ፣ ግጥሞቹ ስነ-ምግባራዊና ባህላዊ እሴቶችን ያስተምራሉ፣ በማህበራዊና በግል ህይወት ውስጥ ያለውን ግንኙነት ይቆጣጠራሉ፣ በህዝቦች ውስጥ ያለውን የጋራም ሆነ ግላዊ ስሜት ይገልፃሉ ይላሉ፡፡ ይህን ሀሳብ የሚያጠናክሩት Neguss (2018,18-19) ዘፈኖች የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳሏቸው በማብራራት Mithenን (2006) ጠቅሰው ዘፈኖች ለማህበራዊ

ትስስር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ በዚህም የቡድን ተግባርን ውጤታማነት እንደሚያሳድጉ ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም የስራና የጦርነት ዘፈኖች፣ የየአገራት ብሄራዊ መዝሙሮች ቤተሰባዊ፣ ቡድናዊና አገራዊ አንድነትን ያስተሳስራሉ ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ዘሪሁን (የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን)ን ጠቅሰው በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ገበሬዎች ጠንካራ ሰራተኛን ለማበረታታትና ሰነፍን ለመንቀፍ በዘፈኖች እንደሚጠቀሙ በዚህም አንድ ገበሬ በእርሻ ስራ ያለውን ውጣ ውረድ መቋቋም ካልቻለ በድህነት እንደሚኖር ያስተምራሉ፡፡ ሰነፉ ገበሬም የዘፈኖቹ ትችት ጠንክሮ ለመስራት እንደሚያነሳሳው ይገልፃሉ፡፡ አያይዘውም ኢትዮጵያ በታሪኳ ባሳለፈቻቸው የተለያዩ ጦርነቶች የዘፈኖች ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነና ህዝቡ ጠላትን በጋራ እንዲመክት የማነሳሳትና የማጀገን ጠቀሜታ እንደተወጡ ያነሳሉ፡፡ እንዲሁም Meheret, (2016); Timkehet, (2009); Solomon, (2006); እና Getie,ን (2002) በመጥቀስ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በተለያዩ አስተዳደራዊ ስርአቶች ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ተገድቦ በመቆየቱ ሰዎች የተለያዩ ቅሬታዎቻቸውን ለማሳየት በዘፈን እንደሚጠቀሙ ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ በዘፈኖች የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ተፈጥሯዊ ጉዳዮች ይነሳሉ፡፡ ሰብአዊ ጉዳዮች ይገለጣሉ፡፡ የሰው ልጅን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ነገሮች በሚያዝናና፣ በሚያስተምር፣ ስሜትን በሚገዛ መንገድ ለማቅረብ የዘፈኖች ፋይዳ የጎላ ነው፡፡ ዘፈኖች በአንድ አገር ማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ያለፈን ታሪክ በማሳወቅ፣ ታሪክ ከትውልድ ትውልድ በማስተላለፍ፣ የወደፊት እጣ ፈንታን በመጠቆም ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

ዘፈኖች ከላይ ከተጠቀሱት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አገራዊና ታሪካዊ ፋይዳቸው በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ሀሳብ ማስተላለፊያ በመሆን ተስፋ ማድረግን፣ መነቃቃትን (መነሳሳትን)፣ ስለወደፊት ማለምን፣ ከተከሰተ አንዳች ጉዳይ ለአፍታም ቢሆን ማምለጥን እንደሚያስችሉ Masriyah and et al (2019,167) Haupthን (2016) ጠቅሰው ይገልፃሉ፡፡ ከእነዚህ ዘፈን ለሰው ልጆች ከሚያበረክታቸውና ከሚገልጣቸው ሰዋዊ ሁነቶች ውስጥም የዚህ ጥናት ትኩረት ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው የተመረጡ ዘፈኖችን አንድምታና ለወቅቱ ማህበረ-ፖለቲካዊ ጉዳይ ያበረከቱትን ፋይዳ መተንተን ነው፡፡

## 2.1.3. ወቅታዊ ፖለቲካዊ ዘፈኖችና ተፅዕኗቸው

ኪነ-ጥበብ ምንጊዜም ቢሆን የሰው ልጅ አስተሳሰብ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችል ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ለውጦች እንዲመጡ ትልቅ ድርሻ ነበረው፡፡ በተለይም በተለያዩ የአለም አገራት የተካሄዱ እንቅስቃሴዎችን በመምራትና ለውጥ በማምጣት ረገድ ዘፈኖች ትልቅ ሚና ነበራቸው፡፡ ከነዚህ ዘፈኖች ውስጥም በዋናነት ወቅታዊ የሆኑ የተቃውሞ ዘፈኖች (Topical protest songs) ወቅታዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን መነሻ አድርገው የሚሰሩ ናቸው፡፡ የተቃውሞ ዘፈኖች በአብዛኛው ወቅታዊ ክስተቶችን በማስመልከት ሲዘፈኑ ከማህበረ ፖለቲካዊ ለውጥ እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ዘፈኖቹ ለተለያዩ እንቅስቃሴዎችና ለውጦች መሰረት ሲሆኑ በተለያየ የአቀራረብ ዘውግ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ዘፈኖች ትልቅ አስተዋፅኦ ካደረጉባቸው እንቅስቃሴዎች መካከልም የሴቶች የመምረጥ መብት፣የሰራተኞች ንቅናቄ፣ የሰብአዊ መብት ንቅናቄ፣ የዜጎች መብት ንቅናቄ፣ የአሜሪካ ተወላጆች የመብት ንቅናቄ፣ የፀረ-ጦርነት ንቅናቄ እና የ1960ዎቹ የሴቶች ንቅናቄ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በፖለቲካ ዙሪያ የሚዘፈኑ ወቅታዊ ዘፈኖችም የሚዘፈኑት ለተለያየ አላማ ሲሆን አንድም ስርአትን ለመቃወም አንድም ደግሞ ስርአትን ለመደገፍ በሌላ በኩልም መፍትሄ ለመጠቆም ነው፡፡ ስርአትን የሚቃወሙ ዘፈኖች ማህበረሰብን በማነሳሳት ተግባራቸው ህዝብ ስርአቱን እንዲቃወም በማድረግ አስተዳደራዊ ለውጥን ሲያስከትሉ ለመደገፍ የሚዘፈኑት ደግሞ ስርአቱ በጠንካራ የህዝብ መሰረት ላይ እንዲገነባ የማድረግ ሀይላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ፖለቲካዊ ዘፈን ማለት ህዝብን ለማስተዳደር በስልጣን ላይ ያለን መንግስት ደካማና ጠንካራ ጎኖቹን ለመግለፅ እንዲሁም ማስጠንቀቂያ አዘል መልዕክቶችን አካቶ የሚቀርብ እና ከዚህም ሌላ የሌሎች ተፎካካሪዎችን ድምፅ ለማሰማት የሚያስችል አንዱ የሀሳብ ማንፀባረቂያ መንገድ እንደሆነ Ruth Finnegan (2012,265-290) "Topical and political songs" በሚል ርዕስ ስለአፍሪካ የፖለቲካ ዘፈኖች ባተቱበት ክፍል ይገልፃሉ፡፡ በአገራችንም የየወቅቱን ፖለቲካዊ ስርአት አስመልክተው የተዜሙ ዘፈኖች በርካታ ናቸው፡፡

## 2.1.4. ዘፈንና ፖለቲካ በኢትዮጵያ

በተለያዩ ጊዜያት ይዘታቸውን ማህበረ ፖለቲካዊ ጉዳይ ላይ ያደረጉ ዘፈኖች በተለያዩ ባለሙያዎችና በተለያዩ አገራት ተሰርተዋል፡፡ ዘፈን በየአገራቱ ፖለቲካ የራሱን ሚና የተጫወተ ሲሆን በደቡብ አፍሪካ ፀረ-አፓርታይድ እንዲሁም በመላው አፍሪካ የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል አስመልክቶ ሚና ነበረው፡፡ የነጮች የበላይነትን ለመቃወም በአሜሪካ ሲቪል ራይትስ ሙቭመንት (የሰብአዊ መብት ንቅናቄ) ላይም ዘፈን መሳሪያ ነበር፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያም ዘፈኖች ለበርካታ ፖለቲካዊ ሁነቶች ተሰርተዋል፡፡ እነዚህ ስራዎችም አንዳንድ ጊዜ ስረአተ መንግስቱን አወድሰው ሌላ ጊዜ ደግሞ ተቃውመው የተሰሩ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የሚቀርበው ሀተታም በኢትዮጵያ እንደዚህ አይነት ስራዎች የነበራቸውን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ምህረተ ስላሴ (2009፣4) በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታን ያማከሉ ዘፈኖች በተለያዩ ጊዜያት ሲሰሩ እንደቆዩ ሰፊ ማብራሪያ በመስጠት የሚከተለውን ይገልፃሉ፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታን ያማከሉ ዘፈኖች በተለያዩ ጊዜያት ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ዘፈን መነሻውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እውነታ ያደርጋልና የኢትዮጵያ ዘፈኖችም የየዘመኑ መስታውት ናቸው፡፡ የየወቅቱን ስርአት የሚተቹ ወይም የሚደግፉ ዘፈኖች ተደምጠዋል፡፡ ዘፋኞች ያሉበትን ወቅት ከመግለፅ ባሻገር ለወደፊት ሊሆን የሚችለውን እንደ ርዕይ ያስቀመጡበትም ጊዜ አለ፡፡ ድምፃዊያን በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የህዝብን ድምፅ ያስተጋባሉ፡፡

ዘፈን ህዝብን ለማስተባበር እና አንዳች አቅጣጫ ለማመላከት ይውላል፡፡ ከድምፃዊያን ጀርባ ያሉ የግጥምና ዜማ ደራሲዎችም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በዘፈን መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ ዘፋኞች የግል አቋማቸውንና የህዝቡንም የልብ ትርታ ሲያሰሙ ድጋፍና ተቃውሞም ያገኙባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ አሁንም አሉ፡፡ መወደድና መሞገስ እንዳለ ሁሉ መታሰር መሰደድና መገደልም የደረሰባቸው በርካታ ናቸው፡፡ ባለፉት የተለያዩ ስርአቶች ፖለቲካውና ዘፈኑ ያላቸውን መስተጋብር እንዲሁም ከህዝቡና ከመንግስት የተሰጣቸውን ምላሽ አስመልክቶ ምህረተ ስላሴ (2009፣4) በሙዚቃ ግጥምና ዜማ እንዲሁም በተውኔት ድርሰትና ዝግጅት የሚታወቁት ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) የተናገሩትን በማንሳት በየዘመኑ ፖለቲካና ዘፈን ሲዋሀዱ የሚሰጣቸው ምላሽ ተመሳሳይ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

መንግስታት መተቸት ስለማይፈልጉ ዘፈኑን በተለያየ መንገድ ለመቆጣጠር ሲሞክሩ ይስተዋላል፡፡ በንጉሱ ጊዜ ንጉሱን ከሚያወድሱ ስራዎች ውጭ ያሉት በቅድመ ምርመራ እንዲወድቁ ይደረጋል፡፡ ‹‹ቅድመ ምርመራ አድራጊዎቹ ቅኔ አዋቂዎች በመሆናቸው በወርቅና ሰም መልክም መልዕክት ማስተላለፍ አይቻልም›› ይላሉ ባለሙያው፡፡ ህዝቡን ይቀሰቅሳሉ የሚባሉ ዘፈኖችን የማስቀም ሂደት በፖሊስ ሰራዊት፣ ክብር ዘበኛና የምድር ጦር ሙዚቃ ክፍልም ተመሳሳይ ነበር፡፡

የሶሻሊዝም ርዕዮት በሚራመድበት የደርግ ስርአት ነገሮች ቢሻሻሉም መንግስትን የሚነኩ ዘፈኖች ተቀባይነት አልነበራቸውም፡፡ ‹‹ስርአቱ ህብረተሰቡን ስለሚያቅፍ ሙዚቃው ያደገበት ዘመን ቢሆንም ምንጊዜም ገዢዎች የራሳቸው እድፍ ሲነካ ስለማይወዱ ያኔም ችግር ነበር›› በማለትም በደርግ ስርአት የነበረውን ሁኔታም ጨምረው ያስረዳሉ፡፡

በኢህአዴግ ጊዜም በቀደሙት ጊዜያት የነበረው ቅድመ ምርመራ መልኩን ለውጦ በግምገማ መልክ ቢመጣም፣ ጥቂት ሙዚቃዎች ይህን አልፈው የወጡበት ጊዜ አለ፡፡ በዚህ ወቅት የመናገርና የመፃፍ ነፃነት በህገ-መንግስቱ ቢሰጥም ይዘታቸው የማይፈለግ ዘፈኖች ጫና ይደረግባቸዋል፡፡ ‹‹ጥበብና ፖለቲካ እስከመጨረሻው እየተናቆሩ ይኖራሉ›› የሚሉት ተስፋዬ ዘፋኞች የሚያስተላልፉት መልዕክት መደመጥ እንዳለበት ‹‹መንግስታት ራሳቸውን ለኪነ ጥበብ ማስገዛት አለባቸው›› በማለት በዘፈን የህዝቡን ስሜት ማዳመጥና የለውጥ መሳሪያ ማድረግ እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡

በአንዳንድ ከ1967-1983 ዓ.ም. የነበረውን ፖለቲካዊ ሁኔታና የዘፈኑን ሚና በዳሰሱ ጥናቶች እንደተመለከተው በዘመኑ የፊውዳል ስርአትን የሚቃወሙ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ዘፈኖች በህዝቡ ተወዳጅ እንደነበሩ ነው፡፡ (ምህረተ ስላሴ 2009፣4)፡፡ የህዝብ ጭቆናን የሚቃወሙና የሰርቶ አደሩን ድምፅ የሚያሰሙ ዘፈኖችን መንግስትም ይጠቀምባቸው ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ በቀይ ሽብር ወቅት ገፅታውን ለውጦ ስርአቱን የሚደግፍ ዘፈን ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆኑ ዘፋኞችም የሙዚቃ ባለሙያዎችም ይነጣጠርባቸው ጀመር፡፡ ሌላው በጥናቶቹ የተገለፀው በተለያዩ ህዝባዊ ጦርነቶች ጊዜም ዘፈን የነበረው ሚና ነው፡፡ ለምሳሌ የ1969ኙን ጦርነት ማንሳት ይቻላል፡፡ ጊዜው የኢትዮጵያና ሶማሊያ ጦርነት የነበረበት ወቅት ሲሆን የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊትን የሚያነሳሳ ዘፈን ጦር ግንባር ድረስ ሄደው ካሰሙት ድምፃዊያን መካከልም ጥላሁን ገሰሰ፣ ብዙነሽ በቀለ፣ መሀሙድ አህመድ፣ አለማየሁ እሸቴ እና ታምራት ሞላ ይጠቀሳሉ፡፡

በአገሪቱ ውስጣዊ ሁኔታ ረገድም በህወሓት ንቅናቄ ዘፈን የነበረው ሚና በጥናቶቹ ተመልክቷል፡፡ ኪሮስ አለማየሁ እና ገብረጻድቅ ወልደዮሀንስን የመሰሉ የትግርኛ ዘፋኞች ይጠቀሳሉ፡፡ ኪሮስ በዘፈኖቹ ለእስር ቢዳረግም፣ ቅኔ አዘል የተቃውሞ ዘፈኖቹን ከተፈታ በኋላም ቀጥሏል፡፡ የተቃውሞም ይሁን የድጋፍ ዘፈኖች በተለያዩ ቋንቋዎችም ተሰርተዋል፡፡ የህዝብን ጭቆና በመቃወም ለለውጥ የሚያነሳሱ ዘፈኖች ከሚያቀነቅኑ የኦሮምኛ ዘፋኞች አሊ ቢራ ተጠቃሽ ነው፡፡ ከቀድሞዎቹ ኡስማዩ ሙሳ እና እልፍነሽ ኬኖ አሁን ደግሞ ሀጫሉ ሁንዴሳ፣ ሀዊ ተዘራ እና ጫላ ቡልቱሜን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ድምፃዊያን በተጨማሪ ሌሎችም የአካባቢያቸውን ባህልና እሴት በማንፀባረቅ ቀስቃሽ ዘፈኖችን ያስደምጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ማህበራዊና አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ዘፈኖችም በበርካታ ባለሙያዎች ተደርሰው ለህዝብ ጆሮ የደረሱበት ጊዜ ብዙ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የህዳሴ ግድብ ግንባታን ለመደገፍ፣ የሰንደቅ ዓላማና የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን ለማክበር  የተሰሩ በርካታ ዘፈኖችን ማንሳት ይቻላል፡፡

ፖለቲካዊ ዘፈኖችን አስመልክቶ ምህረተስላሴ (2009፣4) የዘፈን አቀናባሪና ኪቦርዲስት ዳዊት ይፍሩን በመጥቀስ በየዘመኑ የተሰሩትን ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ዘፈኖችን ሁኔታ ሲገልፁ የዘፈኖቹን ሰምና ወርቅ ይዘት ተረድቶ የሚያዳምጥ እንዳለ ሁሉ ዝም ብሎ በደፈናው የሚያዳምጥም እንዳለ በማንሳት እንደ ምሳሌም የጥላሁን ገሰሰ ‹‹አልማዝን አይቼ›› የሚለውን ዘፈን ጠቅሰው ያስረዳሉ፡፡ ሙዚቀኛው አሁን የሚሰሩ ዘፈኖችን ከቀድሞዎቹ ጋር ሲያነፃፅሩ ጥልቅ መልዕክት ያላቸው ስራዎች ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ዘፈኑ ለነባራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ ያለውን አስተዋፅኦ ውስን ያደርገዋል በማለት የቀድሞዎቹ ዘፈኖች ይዘት ካሁኖቹ በተሻለ የየወቅቱን ስርአት መደገፍም ይሁን መንቀፍ ላይ ጠንካራ እንደነበሩ ይገልፃሉ፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን ዘፈን ከአውዱ አንፃር የተመለከቱ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ደግሞ ኪነቶች ዘፈን በፖለቲካው ያለውን ቦታ ከሚያሳዩ ምሳሌዎች መካከል የሚጠቀሱ እንደሆኑ ነው፡፡ በደርግ ወቅት የተስፋፉት ኪነቶች ከሚሰሩት ዘፈን አንፃር በፖለቲካው የነበራቸው ተፈላጊነት ከፍተኛ ነበር፡፡ ‹‹ኪነት ለአብዮት፣ ኪነት ለትግል፣ ኪነት ለንቃት፣ ኪነት የሰፊው ህዝብ መሳሪያ ነው›› የሚሉ መሪ ቃሎችም ለዚህ ማስረጃ ናቸው፡፡ ከጥናቶቹም የመንግስታት መለዋወጥ ለሙዚቀኞች ያለው አስተዋፅኦ እና ተፅዕኖውም በዘፈን እንደሚታይ መረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በዘፈን የየዘመኑ ማህበረ ፖለቲካዊ ሁኔታ ሲገለፅ ቆይቷል፡፡ አሁንም እየተገለፀ ይገኛል፡፡ ለዚህም የቅርብ ጊዜ ትውስታ የሆነውን የ2008 ዓ.ም. የህዝባዊ ፖለቲካዊ ተቃውሞና በወቅቱ ያስተዳድር በነበረው በኢህአዴግ መንግስት ለተቃውሞ በወጣው ህዝብ ላይ የተወሰዱ የሀይል እርምጃዎችን አስመልክቶ የተዘፈኑ ዘፈኖችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ይህ ጥናትም ታዲያ በዚህ ዙሪያ የሚያተኩር ሲሆን ከ2008-2013 ዓ.ም. ድረስ የተዘፈኑ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን የተመረጡ ዘፈኖች አንድምታና ለወቅቱ ማህበረ-ፖለቲካዊ ጉዳይ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ተንትኗል፡፡

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ማህቀፍ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ ጥናቱን የሚመሩና የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን የሚውሉ ንድፈ ሀሳቦች ምንነትና የተመረጡበት ምክንያት ይቀርባል፡፡ ለዚህ ጥናት የሚመረጡትን የዘፈን ግጥሞች ለመተንተን አውዳዊ (Contextual approach) እና ሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሀሳብ (New historicism theory) ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች በዘፈኖቹ የተገለፁትን ሀሳቦች ከተለያየ አቅጣጫ አንፃር ለማየት የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ አውዳዊ መተንተኛ ዘፈኖቹ ከተዘፈኑበት ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ለመተንተን እንደሚያስችል ስለታመነበት አንዱ የመተንተኛ ንድፈ ሀሳብ ተደርጓል፡፡ የዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች እንደሚገልፁት አንድ የኪነ-ጥበብ ስራ ሲተነተን ስራው ብቻ በቂ ስላልሆነ ስራው ከገሀዱ አለም እውነታ አንፃር መተንተን አለበት ይላሉ፡፡ ሁሉም ድርሰቶች የገሀዱ አለም እውነታ ነፀብራቅ በመሆናቸው እነሱን ለመተንተን የገሀዱን አለም ነባራዊ ሁኔታ መረዳት በጣም አስፈላጊ እንደሆነም ያነሳሉ፡፡

በዚህ ንድፈ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ አንድን ስራ የሚተነትን አካልም የድርሰቱ መነሻ የሆነውን አውድ ግምት ውስጥ ያስገባል ማለት ነው፡፡ በአጭሩ አንድን ኪነ-ጥበባዊ ስራ ለመረዳት ስራው የተመሰረተበትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርአት ማወቅ ይገባል ስለሚሉ ተንታኙም በትንታኔው ወቅት ይህን ተጨባጭ እውነታ መገንዘብ አለበት፡፡ ይህን የትንታኔ ንድፈ ሀሳብ አስመልክቶ V.G. kalashnikov (2016, 155-172) እንደሚገልፁት ከሆነ አንድ ኪነ-ጥበባዊ ስራ ወይም ፅሁፍ የሚዘጋጅበት የተወሰነ ታሪካዊና ወቅታዊ ክስተት ይኖረዋል፡፡ ይህን ክስተት አስመልክቶ ሲዘጋጅ ደግሞ ለማህበረሰቡ ማስተላለፍ የሚፈልገው መልዕክት ወይም ዓላማ አለ፡፡ ይህ ዓላማም ተደራሲውን በኪነ-ጥበባዊ ስራው መልዕክት ትኩረቱ እንዲሳብ፣

አመለካከቱ እንዲቀየር፣ ወይም ለተግባራዊ እንቅስቃሴና ድርጊት እንዲነሳ፣ ወዘተ ማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመረዳት ደግሞ ስራው የተዘጋጀበትን (የተፃፈበትን) ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ አውድ በትኩረት ማጤን ያስፈልጋል፡፡

ምክንያቱም ኪነ-ጥበባዊ ስራው የቀረበው እንዴትና ምን ለማስተላለፍ ነው በወቅታዊ ወይም በታሪካዊ ክስተቱ የተደራሲን ትኩረት ለመሳብ ነው?፣ አመለካከቱን እንዲቀይር ለማድረግ ነው? ወይስ ደግሞ በተላለፈው መልዕክት ለተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲነሳሳ? ለማስቻል ነው ወዘተ. የሚሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች ለመመለስ ስለሚያስችል ነው፡፡ እነዚህን ለይቶ ለመረዳትና ጥልቅ ትንታኔ ለመስጠት ደግሞ በአውዳዊ ንድፈ ሀሳብ መመራት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ዘፈኖቹ ለመዘፈናቸው መነሻ የሆነው የዘመኑ ማህበረ-ፖለቲካዊ ሁነት ምን ነበር?፣ ያስተላለፉት መልዕክት አንድምታ ከወቅቱ ሁነት አንፃር እንዴት ይገለፃል?፣ ጠቀሜታቸውና አላማቸውስ ምን ነበር? የሚሉት ጥያቄዎች በንድፈ ሀሳቡ መነሻነት ተተንትነው ምላሽ አግኝተዋል፡፡

ሁለተኛው የመተንተኛ ንድፈ ሀሳብ የሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ Lois tyson (2006,291) እንደሚገልፁት ንድፈ ሀሳቡ በ1970ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ብቅ ያለ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ ትርጓሜ ላይ የሚያተኩር ሲሆን አንድን ኪነ-ጥበባዊ ስራ ለመረዳት ታሪካዊ አውዱን መረዳት የግድ ያስፈልጋል የሚል ነው፡፡ ይህም ሲባል ከኪነ-ጥበባዊ ስራው ውጭ ያሉ የታሪክ ሰነዶችን፣ የዕለት ውሎ ማስታዎሻዎችን፣ መፅሀፍትን፣ መፅሄቶችን፣ መዛግብቶችንና የመሳሰሉትን አብሮ ማንበብ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ እንደ Lois Tyson (2006,285) አገላለፅ ይህ የሆነበት ምክንያት በኪነ-ጥበባዊ ስራው ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ለመረዳት ስራው ብቻ በቂ ስላልሆነና በስራው ለተላለፈው ጉዳይ ሙሉ መረጃን አግኝቶ ማብራራት ስለማይቻል ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት አንድን ኪነ-ጥበባዊ ስራ የሚተነትን አካል የተለያዩ ሰነዶችን በማገላበጥና በስራው ያልተገለጡ ድብቅ የሆኑ ጉዳዮችንም ፈትሾ ለመረዳት ጥረት ያደርጋል፡፡

በንድፈ ሀሳቡ ጥበባዊ ስራዎች የተወሰነ ሁነትን የሚገልፁ ፈጠራዎች ታክለውባቸው በማህበረሰቡ ውስጥ ድርሰቱ በተፃፈበት ወይም ኪነ-ጥበባዊ ስራው በተሰራበት ዘመንና ቦታ ያለውን ዲስኩርና በወቅቱ የሚሰጠውን ትርጓሜ የሚናገሩ ናቸው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ የሀይል ግንኙነት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ሲሆን የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ስራዎች ደግሞ የሀይል ግንኙነቶችን ይገልፃሉ የሚል እምነት አለ፡፡ የሀይል ግንኙነት ሲባልም በመንግስት ፖለቲካ ውስጥ ያለውን ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ፣ በዘር፣ በፆታ፣ ወዘተ. ያለውንም የሚመለከት ነው፡፡

የሀዲስ ታሪካውያን የራሳቸው መገለጫ መርሆች ያሏቸው ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው በየዕለቱ የሚከሰቱ እንቅስቃሴዎች፣ ድርጊቶች ወዘተ. ስለዘመኑ አስተሳሰብ ሰፊ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ የሚለው ነው። ሁለተኛው ደግሞ የትኞቹም ኪነ-ጥበባዊ ስራዎች በዘመን አሻራ መታተማቸው አይቀርም። እነዚህ ስራዎችም የዘመኑን ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ሌሎች አውዳዊ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁና ለመረዳትም የሚያስችሉ ናቸው። በሌላ በኩል ጥበባዊ ስራዎች የህዝብን ፍላጎትና ችግር ማንፀባረቅና የመፍትሔውም አካል መሆን የሚችሉ ናቸው። እንዲሁም ደግሞ አንድን ኪነ-ጥበባዊ ስራ መረዳት የምንችለው ከሌሎች ቴክስቶች ጋር እያዛመድን መተንተን ስንችል ነው። ነገር ግን ከዚህ ውጭ የሚደረግ ትንታኔ ስለስራው በቂ መረጃ መስጠት አያስችልም የሚሉት የንድፈ ሀሳቡ ተጠቃሽ መርሆች ናቸው።

ስለሆነም በዚህ ጥናት የዘፈን ግጥሞቹ የያዙትን ጭብጥ በትክክል ተረድቶ ትንታኔ ለመስጠትና አንድምታቸውን ለመግለፅ በሃዲስ ታሪካዊ ሂስ በመመራት ዘፈኖቹ የተዘፈኑበትን አውድ ብቻ ሳይሆን በግጥሞቹ የተገለጸውን አውድ እንዲሁም ዘፈኖቹ የተደመጡበትን ዘመን አውድ መሰረት አድርጎ ትንታኔ ተሰጥቷል። ምክንያቱም ከላይ እንደተገለፀው ንድፈ ሀሳቡ ኪነ-ጥበባዊ ስራዎችን ከሌሎች ታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ቴክስቶች ጋር አዛምዶ ለመረዳት እና በተለይም ፖለቲካ እና የሃይል ግንኙነት ላይ ለማተኮር ስለሚያስችል ነው። በጥናቱም ዘፈኖቹ የያዙትን ጭብጥና አንድምታ በትክክል ለመረዳትና ትክክለኛ ትርጓሜ ለመስጠት ከዘፈን ግጥሞቹ በተጨማሪ ለጥናቱ በተመረጠው የጊዜ ክልል የወጡ የተለያዩ ሰነዶች፣ መፅሀፍቶች፣ ጋዜጦች፣ መፅሄቶችና ዜናዎች በግብአትነት ውለዋል። በመሆኑም የዘፈኖቹን ይዘት በአንድምታ ለመተንተንና ለመረዳት ዘፈኖቹ የተዘፈኑበትን አጠቃላይ መንፈስ በጥልቀት መረዳት ስለሚጠይቅ በንድፈ ሀሳቡ በመመራት ትንታኔ ተሰጥቷል።

ባጠቃላይ በእነዚህ ሁለት ንድፈ ሀሳቦች መነሻነት ዘፈኖቹ ያላቸው አንድምታ ከተዘፈኑበት አጠቃላይ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ተመርምሯል። እንዲሁም ደግሞ የሚያስተላልፉት የጋራ መልዕክትና ያበረከቱት ጠቀሜታ ተገልጿል።

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ጥናቶች ይቀርባሉ። ነገር ግን አጥኝዋ ባደረገችው ዳሰሳ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የሚዛመዱ ሌሎች ጥናቶችን ማግኘት አልተቻለም። ይሁንና የሀሳብ ተዛምዶ ያላቸውን የቅርብ ጊዜና ቆየት ያሉ የተለያዩ

ስራዎችን ከተለያዩ ድህረ-ገፆች ለማግኘት ተችሏል። እነዚህም የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የተለያዩ ጆርናሎች ናቸው። በመቀጠልም የጥናቶቹ ትኩረት፣ ክፍተት፣ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ተቃርኖ ይቀርባል።

ከተዳሰሱት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች መካከል የናርዶስ ተሻገር (2006) "በቴዲ አፍሮ ዘፈኖች ላይ የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ያቀረበችው ጥናት ነው። በዚህም ድምፃዊው እስከ 2006 ዓ.ም. ድረስ የሰራቸውን ዘፈኖች ይዘት በየፈርጃቸው እየመደበች ትንተና አድርጋለች። በተለይም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ዘፈኖች በአንድ ምድብ በማድረግ ዘፋኙ የሚያተኩርባቸውን መልዕክቶች አላማዋ አድርጋ የተቃራኒ ጾታ ፍቅር፣ ፖለቲካዊ ጉዳይ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ በሚሉ ንዑስ ርዕሶች ከፋፍላ ጥናቷን አቅርባለች።
ይሁንና በጥናቱ ውስጥ ክፍተቶች ይስተዋላሉ። በጥናቱ ዓላማ ላይ የተገለፀው በአጠቃላይ በሙዚቀኛው እስከ 2006 ዓ.ም. የተሰሩ ዘፈኖች ይዘት እንደሚተነተን ነው። ነገር ግን በመረጃ ትንተናው ላይ የተወሰኑት ብቻ ተመርጠው የተተነተኑበት ሁኔታ ይታያል። ይህም በጥናቱ ወሰን ቢገለፅ ካልሆነም በናሙና ምርጫው በግልፅ ተብራርቶ ቢሆን ጥናቱን የተምታታና ዓላማውን የሳተ እንዲሆን አያደርገውም ነበር። ሆኖም ግን በጥናቱ ግኝት ማጠቃለያ ላይ በዘፋኙ የተቀነቀኑ ግጥሞች ይዘት በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በጾታ ፍቅር ላይ የሚያተኩሩ እንደሆኑ ተገልጿል። ጥናቱ የአንድ ሰው ስራ ላይ ማተኮሩ፣ በይዘት ደረጃም ሁሉንም ይዘቶች መዳሰሱ እና የትንተና መንገዱ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት እንዲኖረው ሲያደርግ መነሻ ሀሳቡ ዘፈንን መተንተን ላይ መሆኑ ደግሞ ተመሳስሏቸው ነው።

ሌላው ጥናት አንተነህ መርእድ (1980) "በገበያ ላይ የዋሉ የዘፈን ግጥሞች ይዘት ቅኝት" በሚል ርዕስ ያቀረበው ነው። የአንተነህ ጥናት ዋና አላማ በአገራችን ውስጥ ከጣሊያን ወረራ በፊትና በኋላ የተዘፈኑ ዘፈኖችን በማንሳት ከይዘታቸው አኳያ ምን አይነት ታሪካዊ ለውጥ እንዳመጡ በመተንተን ላይ የተመሰረተ ነው። አጥኚው በጥናት ግኝቱ ከወረራ በፊት የባህል መከለስ እንዳልነበረ በተቃራኒው ከወረራው በኋላ ግን በተለይም ከእርስ በርስ የንግድ ልውውጥ ተፅእኖ የተነሳ የሌሎች አገሮች ባህል በኢትዮጵያ ላይ አሻራውን እያሳረፈ እንደመጣ በዘፈን ግጥሞቹ ይዘት መሰረት በጥሩ ማሳያዎች አቅርቧል።

ነገር ግን ጥናቱ ከርዕሱ እና ከዓላማው አለመጣጣም ጀምሮ ዝብርቅርቅነት ይታይበታል። ምክንያቱም በገበያ ላይ የዋሉ የዘፈን ግጥሞች ይዘት ቅኝት የሚለው ርዕስ መቼ፣ በምን ሁኔታ

እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ርዕሱን የተመለከተ አንባቢ ከርዕሱ የሚጠብቀው እና በትንተናው የሚያገኘው ነገር የተለያየ ይሆንበታል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋርም ከናርዶስ ጥናት የበለጠ ተዛምዶ እንዳለው ታይቷል፡፡ ምክንያቱም የጥናት ዓላማውን ለማሳካት ከተለያዩ ባለሙያዎች ስራ እየጠቀሰ መጠቀሙና የአንድ ዘፋኝ ስራ ላይ ብቻ አለማተኮሩ ያመሳስላቸዋል፡፡ ይሁንና ጥናቶቹ ይዘው የተነሱት ዓላማና ወደ አላማቸው ለመድረስ የተጠቀሙበት ዘዴ የተለያየ ነው፡፡

ሁለቱ ለዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች የዘፈኖችን ይዘት መተንተን ላይ ማተኮራቸው እና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛን መጠቀማቸው ተመሳስሏቸውን ሲገልፅ ከዚህ ጥናት ጋርም በተጠቀሱት ነገሮች ተዛምዶ እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል፡፡ በተለይም የአንተነህ ጥናት የተለያዩ ዘፈኖችን ወስዶ መተንተኑ የበለጠ ቅርበት እንዲኖረው አስችሎታል፡፡

ቀጥሎ የሚቀርበው ጥናት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰራ ሲሆን Hilina Fekadu (2020) "analysis of Ethiopian ‹kignts› used dominantly in popular songs produced as commercial music in the 1960-1980s: the modern recording songs in Addis Ababa." በሚል ርዕስ ከ1960-1980 እንደ ንግድ ሙዚቃ ተዘጋጅተው በወጡ ዘፈኖች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን የኢትዮጵያ ቅኝቶች መግለፅ ነው፡፡ ዓላማውም በዘፈኖቹ አገልግሎት ላይ የዋሉት ቅኝቶች ምን እንደሆኑ መግለፅና መለየት ነው፡፡ ለዚህ መሳካትም መረጃው በሰነድ ፈተሻና በቃለ-መጠይቅ ሲሰበሰብ የተገኘው መረጃም በአይነታዊ መንገድ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በጥናቱ ግኝትም ቅኝቶቹ አምባሰል፣ ባቲ፣ ትዝታና አንቺሆዬ እንደሆኑ ሲጠቀስ ከሱ ጋር ተያይዞም እነዚህ የቅኝት አይነቶች በተለያዩ አካባቢዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተገልጿል፡፡ በምልከታውም ጥናቱ የቀረበበት መንገድ ጥሩ የሚባል ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ዘፈኖች ላይ በመሰራቱ ብቻ ነው፡፡ በትንተናው የታዩት ጉዳዮች ዘፈኖች በምን አይነት ቅኝት እንደቀረቡ የሚያሳይ እንጅ የግጥሞቹን ይዘት መርምሮ ፖለቲካዊ አንድምታቸውንና ፋይዳቸውን አለመመልከቱ ልዩነታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አራተኛው ጥናት ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ በNeguss Yilma (2018) "Thematic analaysis of selected Amharic song lyrics: a sociological approach." በሚል የተጠና ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው በሶስቱ ተከታታይ የአገዛዝ ዘመናት (በቀዳማዊ አፄ ሀይለስላሴ፣ በደርግ እና ኢህአዴግ) የተቀናበሩ የአማርኛ ዘፈኖች ውስጥ የተካተቱ ዋና ዋና ጭብጦችን መመርመር

ነው። በጥናቱ 60 የአማርኛ ዘፈኖች በናሙናነት ሲመረጡ ዘፈኖቹ በሶስት ንድፈ-ሀሳቦች ***ማለትም*** (Functionalism perspective, Conflict perspective, Symbolic interactionism perspective) *መሪነት* በአይነታዊ *መተንተኛ* ዘዴ ተተንትነዋል። በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችም በንጉሰ ነገስቱ ጊዜ የነበሩ ዋና ዋና ጭብጦች የሀገር ፍቅር፣ ትምህርት፣ የሞራል ዝቅጠት (ዝሙትን ሙስናን የተመለከተ) እና ፖለቲካዊ ቅሬታዎች እንደሆኑ ተገልጿል።

በደርግ ዘመንም በዋናነት አብዮታዊ ዘፈኖች እና አብዮታዊ ያልሆኑ ዘፈኖች በሚል ተለይተው ሲቀርቡ አብዮታዊ ዘፈኖቹ የ1974ቱን አብዮት የሚዘክሩ እና ሌሎችም ተግባራት የነበሯቸው እንደሆኑ ሲገልፁ አብዮታዊ ያልሆኑ ዘፈኖች ደግሞ በቁጥር አነስተኛ እንደሆኑና ይዘታቸውም የወቅቱን አገዛዝ መቃወም (ቅሬታን) መግለፅ ላይ ያተኮሩ እንደሆኑ ተገልጿል። በኢህአዴግ ዘመንም የታዩት ዋና ዋና ጭብጦች የፖለቲካ ቅሬታ እና ስደት እንደሆኑ ታይቷል። በሌላ በኩል በሶስቱ ዘመናት የተሰበሰቡ የፍቅር ዘፈኖች የተተነተኑ ሲሆን የፆታ ፍቅር እና የእናት ፍቅር በሚል ምድብ ተመድበው ቀርበዋል። ባጠቃላይ በጥናቱ የዘፈን ግጥሞቹ ጭብጥ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ እንደሆኑና እነዚህን ጉዳዮች ለመግለፅ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደተወጡ ተመላክቷል። በመሆኑም ጥናቱ ከሌሎቹ በተሻለ በርዕሰ-ጉዳይ፣ በጥናት አቅጣጫ፣ በትንተና ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ሲኖረው ልዩነቱ ደግሞ የዘፈኖችን ጭብጥ ከመለየትና ማህበራዊ ጉዳያቸውን ከመዳሰስ በዘለለ የዘፈኖችን ፋይዳ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር አያይዞ አለመግለፁ ይለያቸዋል። በተጨማሪም የንጉስ ጥናት አጠቃላይ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን በተጠቀሰው ጊዜ የተዘፈኑ ፖለቲካዊ ዘፈኖች ላይ ያተኩራል።

በአጠቃላይ ግን ሁሉም ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የራሳቸው የሆነ ተመሳስሎና ልዩነት ቢኖራቸውም በዋናነት ተመሳስሏቸው ዘፈኖችን በተለያየ መልክ መተንተናቸው ሲሆን ዋናው ልዩነታቸው ደግሞ የዘፈኖቹን አንድምታ ከነበረው አውድ አንፃር በማገናኘት ያበረከቱትን ጠቀሜታ አለመግለፃቸው ነው። ይህም ሲባል ሌሎቹ ጥናቶች የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የተመሰረቱ ቢሆንም እንኳን የዘፈኖቹን ጠቀሜታ የገለፁ አይደሉም። ነገር ግን ይህ ጥናት ዘፈኖቹን ከፖለቲካዊ አውዳቸው በተጨማሪ ያበረከቱትን ማህበረ-ፖለቲካዊ ጠቀሜታ መግለፁ ልዩነት እንዲኖራቸው አድርጓል።

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ስነ-ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አጠቃላይ የጥናቱ ሂደት ምን እንደሚመስል ማለትም ለጥናቱ የሚውሉት መረጃዎች አሰባሰብ፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ወዘተ. የሚብራራበት ክፍል ነው፡፡

### 3.1. የጥናቱ ዘዴ

ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተብራርተው በገለፃ መልኩ ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በገላጭ የምርምር አይነት የተካሄደ ሲሆን መረጃዎቹም በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም ለትንታኔ የተመረጡት መረጃዎች የሚቀርቡት በቁጥር መልክ ሳይሆን በገለፃ መልክ በጥልቅ ማዳመጥና ማንበብ የተገኙ በመሆናቸው ነው፡፡ እንደ እነዚህ አይነት መረጃዎችን ደግሞ አብራርቶና ተንትኖ ለማሳየት የተጠቀሰው ዘዴ አመቺና ትክክለኛ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም በአጥኚዋ ስለታመነበት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

### 3.2. የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች ከ2008-2013 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ የተዘፈኑ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖች ሲሆኑ እነዚህ ዘፈኖች ለጥናቱ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ ከእነሱ በተጨማሪ ግን በጊዜው የተዘገቡ የተለያዩ ዜናዎች (ከጋዜጦች፣ ከመፅሄቶች፣ ከተቀረፁ የድምፅና የምስል ክምችቶች ወዘተ.) የተገኙ መረጃዎች እና የወቅቱን አጠቃላይ ፖለቲካዊ ሁኔታ የተመለከቱ የተለያዩ ፅሁፋዊ ስራዎች ትንተናውን እያጣቀሱ ለመተንተን ስለሚያግዙ እንደ ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ ተወስደዋል፡፡

### 3.3. የናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ለሆኑት መረጃዎች የናሙና አመራረጥ የተካሄደው የጥናቱን ዓላማ መሰረት ባደረገ መልኩ በዓላማ ተኮር ናሙና ነው፡፡ ያለው (2006፣132) “በዚህ የንሞና ዘዴ ተመራማሪው ማንን መውሰድ እንዳለበት የሚወስነው ራሱ ነው፡፡” በማለት በዓላማ ተኮር

ናሙና ተመራማሪው እነዚህ ነገሮች ቢካተቱ የበለጠ ጥልቅ መረጃ አገኛለሁ ብሎ የሚያምናቸውን ነገሮች መጠቀም እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከተዘፈኑ ፖለቲካዊ ይዘት ካላቸው ዘፈኖች ውስጥ አጥኝዋ በጥናቷ ዓላማ አድርጋ የተነሳችበትን ጉዳይ የበለጠ ከግብ የሚያደርሱና ጥሩ መረጃዎችን ይዘዋል ተብሎ የታመነባቸው ዘፈኖች ተመርጠዋል፡፡ ዘፈኖቹን ለመምረጥም የተዘፈኑበት ወቅት፣ የወቅቱ ፖለቲካዊ ሁኔታና የዘፈኖቹ ይዘት በመስፈርትነት ተወስዷል፡፡ በዚህም የአምስት ዘፋኞች አስር ዘፈኖች ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለጥናቱ መሳካት የተሰበሰቡት መረጃዎች የአሰባሰብ ዘዴ የሆኑት ሰነድ ፍተሻ (Documentation) እና ጥልቅ ማዳመጥ (Critical Listening) ናቸው፡፡ ስለሆነም በዘፈኖቹ ውስጥ ያሉትን መልዕክቶች ለመረዳት ግጥሞቹን በጥልቀት በማዳመጥ ከተመረጡት ዘፈኖች ላይ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ ምክንያቱም የመረጃ ምንጮቹ እነሱ በመሆናቸውና የሚተነተኑት ሀሳቦች ከዘፈኖቹ ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው ነው፡፡ በመጀመሪያ ግን አጠቃላይ ዘፈኖቹ ከሚገኙበት (ከካሴት ወይም ሲዲ መሸጫ መደብሮችና ከኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች) ተሰብስበው ለአጥኝዋ በሚያመች መንገድ ተቀምጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን እንደሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ የተወሰዱት መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ ተሰብስበዋል፡፡ ምክንያቱም በዘፈኖቹ ሊገለፅ የተፈለገውን ጉዳይና በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ በተጠቀሰው የጊዜ ክልል ውስጥ የተዘገቡ ዜናዎች፣ የተፃፉ መፃህፍት፣ መፅሄቶችና ጋዜጦች ስለተመለከቱትና ለትንተናው የሚሆን የወቅቱን መረጃ መስጠት ስላስቻሉ ነው፡፡

## 3.5. የመረጃ አደረጃጀትና የትንተና ስልት

### 3.5.1. የመረጃ አደረጃጀት

የተሰበሰቡት መረጃዎች ለትንታኔ በሚያመች መልኩ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እና በሶስት ንዑሳን እዲሁም በሌሎች የንዑስ ንዑሳን ክፍሎች ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ከ2008-2013 ዓ.ም. የነበረው አጠቃላይ ፖለቲካዊ ሁኔታ ባጭሩ ከተገለፀ በኋላ በንዑስ ክፍል አንድ ደግሞ ከመስከረም 2008 እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም. የነበረው ፖለቲካዊ ሁነት፣ የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥና የዘፈኖቹ አንድምታ ቀርቧል፡፡ በንዑስ ክፍል ሁለትም የመጋቢት

24/2010 ዓ.ም. ለውጥ መገኘት የወለዳቸው የወቅቱ ደስታና ተስፋ፣ የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥና የዘፈኖቹ አንድምታ ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ተተንትኗል፡፡ በንዑስ ክፍል ሶስት ደግሞ በለውጡ ባለመርካት ከ2011-2013 ዓ.ም. የተዘፈኑ ዘፈኖች የጋራ ጭብጥ፣ የነበረው ፖለቲካዊ ሁነትና የዘፈኖቹ አንድምታ ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ተገልጿል፡፡ በሁለተኛው ዋና ክፍልም በየምድቡ በቀረቡት በሶስቱም የጊዜ ክልሎች የተዘፈኑት ዘፈኖች ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በዚህም ዘፈኖቹ አጠቃላይ የጊዜውን ማህበረ-ፖለቲካዊ ሁነት እንዴት እንደተመለከቱትና በየሁነቱ የነበራቸው ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ ከአውዳቸው አንፃር ተብራርቷል፡፡

### 3.5.2. የመረጃ ትንተና ስልት

ለጥናቱ ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መተንተኛ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ሲሆን መተንተኛው ገለፃና ትንተና ለሚያስፈልጋቸው መረጃዎች የሚያገለግል ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የመረጃ መተንተኛ ለዚህ ጥናት በዘፈኖቹ የተገለፁትን ሀሳቦች አንድምታ ወቅታዊ ፖለቲካዊ አውዳቸውን መነሻ በማድረግ በአውዳዊና በሀዲስ ታሪካዊ መተንተኛ ንድፈ ሀሳቦች ለመተንተን እንደሚያስችል ታምኖበት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

## 4.1. ከ2008-2013 ዓ.ም. የነበረው ፖለቲካዊ ሂደት ባጭሩ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው ጊዜ ከ2008-2013 ዓ.ም ያለው ሲሆን እነዚህ አመታት የተመረጡበት ዋና ምክንያት በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በርካታ ፖለቲካዊ ሁነቶች የተከሰቱ በመሆናቸው ነው። በዋናነትም ለ27 አመት ገደማ ስልጣን ላይ የቆየውን የኢህአዴግ መንግስት ለመቃወም የሚሰሙ ድምፆች በየአካባቢው የተፋፋሙበት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በስፋት በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ይታዩ የነበሩትን ህዝባዊ ተቃውሞዎች ማንሳት ይቻላል።

በእነዚህ ህዝባዊ ተቃውሞዎች ሳቢያ የበርካታ ዜጎች ህይወት የጠፋበትና ንብረት የወደመበት ተቃውሞዎቹም የበለጠ እየተቀጣጠሉ የሄዱበት ጊዜ ነበር። በበርካታ አካባቢዎች በተደረጉ ሰልፎች የህዝቡ አንድነት የታየባቸውና ስርአቱን የሚቃወሙ መፈክሮች የተደመጡባቸውም ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ በጎንደር ከተማ እሁድ ሀምሌ 24 ቀን 2008 ዓ.ም የተደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ስንመለከት ‹‹የህዝቡ የወሰን ጥያቄ መልስ ይሰጠው››፣ ‹‹የፖለቲካ እስረኞች ፍትህ ይገባቸዋል››፣ ‹‹በኦሮሚያ የሚፈሰው ደም የኛም ደም ነው›› የሚሉና ሌሎች በርካታ ድምፆች የተሰሙበት ነበር። (ታምራት ሀይሉ 2008፣4)።

ከዚያ በኋላ ደግሞ በእነዚህ ህዝባዊ ተቃውሞዎችና አመፆች የተገፋው ስርአት እየተዳከመ የሄደበትና የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ በፈቃዳቸው ስልጣናቸውን የመልቀቅ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ የመጋቢት 24/ 2010 ዓ.ም ለውጥ የተካሄደበት ነው። ምንም እንኳን ለውጡ ግልፅ የሆነ የስርአት ለውጥ ያልነበረው ቢሆንም ማለት ነው። ነገር ግን በዚሁ የኢህአዴግ ስርአትና አባላት የተመረጡት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አዳዲስ ሀሳቦችን ያስደመጡበት እንዲሁም በተግባርም ጭምር አንዳንድ ለውጦች የታዩበት በመሆኑ ከነበረው አመራር የተለየ ነው በሚል የህዝቦች ጥያቄ መልስ እንደሚያገኝ ተስፋ የተደረገበት ጊዜ ነበር። ይሁንና እነዚህ ተስፋዎች በተለያዩ ምክንያቶች ያልተተገበሩበትና ህዝቡም ለዳግም ቅሬታ የተዳረገባቸው አመታት የተከተሉበት ነው።

እነዚህን የወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነቶች በማስመልከት ደግሞ በርካታ ዘፈኖች ተዘፍነዋል፡፡ ዘፈኖቹ የወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነትና የማህበረሰቡን ስሜት በመግለፅ ረገድ ከፍተኛ ማህበረ ፖለቲካዊ ፋይዳ ነበራቸው፡፡ በዚህ የጊዜ ክልል ከተዘፈኑት ውስጥ የተመረጡ የአስር ፖለቲካዊ ዘፈኖችን አንድምታ በመመርመር፤ በዘፈኖቹ የተገለፀውን ማህበራዊ ስሜትና የዘፈኖቹን ፋይዳ ከመግለፃችን በፊት በእያንዳንዱ ክፍል ማለትም ከመስከረም 2008 እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም.፣ ከመጋቢት 2010 እስከ መስከረም 2011 ዓ.ም እና ከመስከረም 2011 እስከ 2013 ዓ.ም. በነበሩት ጊዜያት የተዘፈኑት ዘፈኖች ከወቅቱ ፖለቲካዊ ሁነት አንፃር ምን እንደሚመስሉና የጋራ ጭብጣቸው ምን እንደሆነ በመግለፅ እንጀምራለን፡፡ በመጀመሪያ ከ2008 እስከ መጋቢት 24/ 2010 ዓ.ም ድረስ ለውጥን ሽተው ከተዘፈኑና ለለውጡ መሳካት የጎላ ድርሻ ከነበራቸው ዘፈኖች ውስጥ ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡትን ሶስት ዘፈኖች እንመልከት፡፡

### 4.1.1. ተቃውሞና የተቃውሞ ዘፈኖች ከመስከረም 2008 እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም

#### 4.1.1.1. የወቅቱ ፖለቲካዊ ሁነትና የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ

እንደሚታወቀው ከ2008 ዓ.ም መስከረም ወር ጀምሮ የአገራችን የፖለቲካ ውጥረት እየከረረ የመጣበት ነው፡፡ በእርግጥ ከዚያም በፊት በየጊዜው የሚደረጉ ተቃውሞዎች አልነበሩም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ አካባቢዎች በየጊዜው የሚካሄዱ ህዝባዊ ተቃውሞዎችና እነሱን ለማፈን የሚደረጉ መንግስታዊ ጫናዎች ከበፊቱ በላቀ ሁኔታ የተፋፋሙበት ጊዜ ነበር፡፡ ከእነዚህ ፖለቲካዊ ውጥረቶች ውስጥ በዋናነት በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች እንዲሁም በጋምቤላ፣ በሶማሌ፣ በደቡብ ወዘተ. የነበረውን ህዝባዊ ተቃውሞና ፖለቲካዊ ትኩሳት ያስነሳው የእርስ በእርስ ግጭት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ለእነዚህ ህዝባዊ ተቃውሞዎችና ግጭቶች የወቅቱ መንግስት ይወስድ የነበረው ያልተመጣጠነና የዜጎችን ህይወት የሚቀጥፍ እርምጃ ተቃዉሞው እንዲቀለበስ ከማድረግ ይልቅ የበለጠ እንዲጠናከርና በአንዳንድ አካባቢዎች ብቻ የነበረው ትግል ወደሌሎች አካባቢዎች እንዲዛመት አደረገው፡፡ በየሰልፎቹም እስረኞች እንዲለቀቁ፣ ፍትህ እንዲሰፍን፣ መንግስት ዜጎችን መግደል እንዲያቆም፣ ወዘተ. የሚጠይቁ ድምፆች በስፋት ይደመጡ ጀመር፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀጠለው

ህዝባዊ ተቃውሞ ደግሞ የወቅቱን ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝን ጫና ውስጥ ከተታቸው፡፡

በመሆኑም ጠቅላዩ የካቲት 8 ቀን 2010 ዓ.ም በአገሪቱ በሚገኙ መገናኛ ብዙሀኖች ወጥተው ከኢህአዴግ ሊቀመንበርነት እና ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርነት በፈቃዳቸው መልቀቅ እንደሚፈልጉ አሳወቁ፡፡ በወቅቱ አነጋጋሪ የነበረ ጉዳይ ቢሆንም፤ ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆናል? የሚለው የበለጠ አነጋጋሪ ነበር፡፡ በህዝቡ ላይመለስ ቆርጦ መነሳት የደነገጠው መንግስትም በዚያው ወር በርካታ እስረኞችን ለመፍታት ጥረት አደረገ፡፡ ነገር ግን በዚያው አመት መጋቢት 24 ቀን የተደረገውና በርካቶች እንደለውጥ የተቀበሉት ለውጥ እስኪመጣ ህዝቡ ተቃውሞውን አላቋረጠም ነበር፡፡ ስለሆነም በዚህ የጊዜ ክልል የተከናወኑትን ከላይ የተጠቀሱ ፖለቲካዊ ሁነቶች የተመለከቱ ዘፈኖች የተዘፈኑ ሲሆን፤ ለዚህ ጥናት ትንተና የናትናኤል አያሌው (ናቲ ማን) ‹‹አሁን ተነካሁ››፣ የይሁኔ በላይ ‹‹ሰከን በል››፣ የጌትሽ ማሞ ‹‹ተቀበል ሁለት (እንከባበር)›› ፖለቲካዊ ክስተቱን መሰረት በማድረግ በማሳያነት ተመርጠው እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

እነዚህ ከ2008-2010 ዓ.ም መጋቢት ወር የተዘፈኑ ዘፈኖች ለውጥን ሽተው ከመዘፈናቸው ባሻገር በአንድም በሌላም መልኩ ለውጥ መሻታቸውን የሚያጠናክሩበትና የሚያስተላልፉት የጋራ የሆነ መልዕክት አላቸው፡፡ ከዚህ የጋራ ጭብጣቸው ውስጥ በወቅቱ የነበረውን እርስ በእርስ የመገዳደል አስከፊነት፣ የእኩልነትንና የመተባበርን አስፈላጊነት መግለፅና ለውጥ እንዲመጣ ማነሳሳት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ባጭሩ ዋናው ጭብጣቸው የተለያዩ አስተዳደራዊ ህፀፆችን በማስተጋባት ለለውጥ ማነሳሳትና ተቃውሞ ነበር፡፡ እነዚህን መልዕክቶች በዘፈኖቹ ውስጥ ባሉ አስረጅ ግጥሞች ስንቃኝ የናትናኤል አያሌው ዘፈን፡-

‹‹ገዳይ ገዳይ ብሎ ወገን ያዜመለት

አገር አትርፎ እንጅ ጠብቆ ከጠላት

ማንስ ጀግና ሊሆን ወንድሙን ገሎ ጥሎት

ቀረርቶ ሽለላው ፉከራ አያምርበት››

በማለት በወንድም ላይ የሚደረግ ግድያ ሊያስከብርም ሊያስወድስም እንደማይችል በወቅቱ ወታደሩ በህዝብ ላይ ይፈፅም የነበረውን ግድያ በተቃውሞ ይገልፃል፡፡ በጊዜው ህዝቡ ወታደሩን

እንደጠባቂው ሳይሆን እንደባላንጣው የሚመለከትበትና ወታደሩም ህዝቡን ከመጠበቅ ይልቅ የስርአቱ ጠባቂና ታዛዥ በመሆን በህዝብ ላይ ግፍን ያደርስ የነበረበት ነው፡፡ በተለይም ወታደሩ በሰልፈኛው ላይ ይፈፅም የነበረው ግድያ ዘፋኙን ወንድምን ገድሎ መጣል ጀግና አያሰኝም እንዲል አድርጎታል፡፡ ይህንን ለማስታወስ ያህል በወቅቱ በተለያዩ የመንግስትና የተቃዋሚ ድርጅቶች መግለጫ የተገለፀው መረጃ የሚያሳየው ወታደሩ በወሰደው የሀይል እርምጃ በኦሮሚያና በአማራ ክልል የብዙ ዜጎች ህይወት መቀጠፉን ነው፡፡ ሁኔታውን አስመልክቶ በወቅቱ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የሰጠው መግለጫ በመንግስት አካላት ያልተመጣጠነ የሀይል እርምጃ መወሰዱንና የ173 ሰዎች ህይወት ማለፉን የሚገልፅ ነበር፡፡ ይሁንና ይህ ቁጥር ትክክል አለመሆኑንና የሟቾች ቁጥር በኦሮሚያ ክልል ብቻ ከ333 ሰዎች በላይ እንደሆነ በወቅቱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት የነበሩት መድረክና ሰማያዊ ፓርቲ ሰኔ 17 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጡት መግለጫ ገልፀው ነበር፡፡ (የማነ ነጋሽ 2008፣3)፡፡ በመሆኑም ዘፈኑ ወታደሩም ከህዝቡ የወጣ ህዝቡም የወታደሩ አካል መሆኑንና ይህ ተዘንግቶ እየተካሄደ ያለው የእርስ በእርስ መጠፋፋት እንደማይበጅ ይገልፃል፡፡

ይሁኔ ደግሞ፡-

‹‹ኧረ ተው ተው በለው

ተው በለው ተው በለው

ማንነቴን ብሎ አደባባይ ወጥቶ

ባዶ እጁን እያየው ሲያልፍ ለሚያልፍ ቀን

ወንድሙን ወንድሙ አልሞ ገደለው››

በማለት የናትናኤልን ዘፈን መልዕክት ሙሉ በሙሉ በሚጋራ መልኩ የወንድማማች ኢትዮጵያውያንን የእርስ በእርስ መገዳደል ኢ-ተገቢነት ይገልፃል፡፡ ከዚህም ባለፈ በተለይም ወታደሩ ለተቃውሞ በወጣው ህዝብ ላይ ያደርስ የነበረውን በደል፡-

‹‹ሰከን ማለት ነው ጨዋነት

ሰከን ማለት ነው ጀግንነት

ወታደሩ ሰከን በል

አፈሙዙን ሰከን አርገው

ቃታህንም እንዳትስበው

ባዶ እጁን ነው የሚጮኸው

ሰላማዊ ወንድምህ ነው››

በማለት ምክር አዘል ሀሳቡን ይገልፃል፡፡ ሰራዊቱን ለማጥቃት ሳይሆን ድምፁን አሰምቶ ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት የወጣ ህዝብ ላይ ቃታ ከመሳብ በፊት ቆም ብሎ ማሰብ የሚገባ መሆኑን የሚገልፅ መልዕክትንም ያስተላልፋል፡፡

በሌላ በኩል እኩልነትና መተባበር ለአንዲት አገር እንደሚያስፈልግ አገራችንም በህዝቦቿ ትብብር ፀንታ እንደቆየች የሚገልፀው ጌትሽ፡-

‹‹ለኔ እንዳልተፈጠረ ሰው ያላንች ምድር ላይ

ልብሽ ከፍቅር እርቆ ለቤቱ ሆነሽ የበላይ

የቤቱ ምሰሶ ጣሪያው ግርግዳው

ባንቺ ብቻ አይደለም ፀንቶ ያየሽው

የልብሽን ዙፋን መንበር ባልታደል

እኔ አላንስም ለቤቱ፣ ለቤቱ እንከባበር››

በማለት እኩልነትና መተባበር ሳይኖር የአንድ አካል የበላይነት በሰፈነበት ሁኔታ አንድ ቤት ሊመራ እንደማይችልና ቤቱ የተገነባውም ሆነ መመራት የሚገባው በእኩልነትና በመተባበር ሊሆን እንደሚገባ በባልና ሚስት መካከል ሊኖር በሚገባው ግንኙነት አስታኮ በኢህአዴግ መስራች ፓርቲዎች መካከል የነበረውን የስልጣን እኩል አለመሆን ኢ-ተገቢነት ይገልፃል፡፡ በወቅቱ የነበረው ነባራዊ ፖለቲካዊ እውነታም የገዥው ፓርቲ ቁንጮ የነበረው አካል እኔን ብቻ ስሙኝ የሚልበትና የችግሩን መፍትሄም እኔ በነደፍኩት መንገድ አመጣለሁ የሚባልበት ወቅት

ነበር፡፡ ይህ ልክ እንዳልሆና ብዙ እርቀት ሊያስጉዝ እንደማይችል ደግሞ ዘፋኙ እንከባበር! በሚል የቁጣ ቅላፄ ይገልፃል፡፡

ይህን የጌትሽን መልዕክት ይሁኔም በሚከተለው መንገድ ተጋርቶት እናገኛለን፡-

‹‹አንዱ ካንዱ ሳይበልጥ አንዱ ካንዱ ሳያንስ

አንዱ አንዱን ሳይገለው ደምም ሳይፋሰስ

በወላጁ ጥፋት ልጁ ሳይወቀስ

ተባብሮ ተፋቅሮ በአንድነት መኖሩ

ይጠቅመናል እንጅ ምንድን ነው ችግሩ

ድር እንኳን ቀጭኑ ድር እንኳን ለስላሳው

ሲያብር ሲተባበር ይበልጣል ከአንበሳው

ስማኝ በጥሞና ልንገርህ ወገኔ

መለያየት ሞት ነው ላንተም ሆነ ለኔ››

የድር ገመድ አንድ ላይ ተሰብስቦ አንበሳን ከጣለ እኛም ብንተባበርና በቋንቋ፣ በዘር፣ በሀይማኖት ባንለያይ፤ በእኛ እንሻላለን ቅኝት በመለያየታችን ስልጣናቸውን ለማራዘም የሚሰሩትን ለማሸነፍ እንደሚቻል በምክር ቃና ይገልፃል፡፡ በአጭሩ በዘፈኑ በወቅቱ የነበረው መከፋፈል ነገሮችን የሞት ያህል እንዳከበዳቸው በመረዳትና ይህን ማህበራዊ ችግር በማጤን ልዩነታችንን እንተውና ለኢትዮጵያዊነታችንና ለህልውናችን እንተባበር የሚል መልዕክት ተላልፎበታል፡፡

ሌላው የዘፈኖቹ የጋራ መልዕክት ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች አፅንኦት በመስጠት ህዝቡ በጋራ ለለውጥ እንዲነሳሳ መገፋፋት ነው፡፡ ይህም በናትናኤል ዘፈን ውስጥ፡-

‹‹የኔ ቤት ሲንኳኳ ካንተ ቤት ይዘልቃል

አፍንጫ ሲነካ አይንኮ ያነባል

ሰብስቦ ያቆየን ይህ ነበር ወጋችን

ዛሬም በአንድ ይሁን ሀዘንም ደስታችን››

ዘፈኑ አንዱ ጋር ያለ ሀዘንም ሆነ ደስታ በአንድም በሌላም መልኩ ወደ ሌላኛው ወገን መድረሱ እንደማይቀር ያስረዳል፡፡ ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ደግሞ በአንዳንድ አካባቢዎች ይደረግ በነበረው ህዝባዊ ተቃውሞ ሁሉም እንዲሳተፍና በጋራ እንዲታገል የሚያነሳሳ ነው፡፡ በጊዜውም በአንዳንድ አካባቢዎች ብቻ ይደረጉ የነበሩ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በሌሎች አካባቢዎችም እንዲቀጣጠሉ ጥረት የተደረገበት ነበር፡፡ ለምሳሌም በየክልሉ በተናጠል ይካሄዱ የነበሩ የተቃውሞ ሰልፎች በሌላ አካባቢ ከሚደረገው በተመሳሳይ አንድ አይነት የተቃውሞ ጥያቄ በማንሳት በጎንደር፣ በባህር ዳር፣ በአምቦ፣ ወዘተ. የተካሄዱበት ነበር፡፡

ይሁኔም፡-

‹‹የወገን ጥያቄው ክብሩ ተመልሶ

በሰላም ለመኖር መግባባቱ ነግሶ

በስደት ያለውም ወደ አገሩ ገብቶ

በነፃነት ሊኖር እንደልቡ ገብቶ

እንደልቡ ወጥቶ

ተማምሏል ህዝቧ ላንዴና ለሁሌ

እልል እልል በሉ እንዲፈታ ህልሜ››

በማለት ተስፋ ያደረገው የህዝብ ጥያቄ መልስ አግኝቶ ህዝቡ በነፃነት መኖር እንዲጀምር ያለውን ጉጉት ሲገልፅ እልል እልል በሉ እንዲፈታ ህልሜ በማለት ነው፡፡ ‹‹እልል እልል በሉ›› የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የሁሉም ዜጋ ተስፋና ምኞት የሆነው ነፃነት፣ ሰላምና እኩልነት እንዲሰምር ህዝቡ በጋራ ለለውጥ እንዲነሳና ተባብሮ እንዲታገል ነው፡፡

ጌትሽ ደግሞ፡-

‹‹አድምጭኝ …

አዳም ቢፈጠርም ያለአማራጭ

እኔ አለኝ አቋራጭ

የኔን ነገር በክፋት ሁል ጊዜ እያየሽው

ተይ ብል የርሜን ብናገር ታመሽ አይቻለሁ››

በማለት ምንም እንኳን አዳም አማራጭ ስላልነበረው ከሄዋን ጋር መኖር ግዴታው ቢሆንም እኔ ግን ከአንቺ ውጭ ሌሎች ስላሉ የአቋራጭ መንገድ ተጠቅሜ ልቀይርሽ እችላለሁ በሚል የባል መካሪ ቃና ቀደም ሲል ያነሳነውን የአንድ ድርጅት የበላይነት በሌሎች ድርጅቶች የመተካት አማራጭ መኖር በምክር ቃና ይገልፃል፡፡ የማደርጋቸው ሰላማዊ ንግግሮች ሊያሳምኑሽ አይገባም በማለት ተከባብረን እንኑር ይህ ካልሆነ ግን አቋራጩን መንገድ መጠቀም ግድ ይሆንብኛል ሲል እኔ አለሁ ባዩን ድርጅት ያስጠነቅቃል፡፡ ይህንን ሲገልፅም ዘፈን ከተጠያቂነት የማምለጫ አንዱ መንገድ እንደመሆኑ የወቅቱን ጫና አገር ውስጥ ሆኖ መግለፅ ከባድ የነበረበት ጊዜ በመሆኑ ለሚስት የተነገረ በማስመሰል ነው፡፡ ይህንንም የዘፈኑ ግጥሞች በአንክሮ ሲመረመሩ የሚገልፁት ከመሆኑ ባሻገር ድምፃዊው ከለውጥ በኋላ በተለያዩ ሚዲያዎች ቀርቦ ካደረጋቸው ቃለ-ምልልሶች መረዳት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሚተላለፈው ካሌብ ሾው በተሰኘ ፕሮግራም ላይ እሁድ ግንቦት 4/ 2011 ዓ.ም ከጠያቂው ለቀረበለት "ግን ከዘፈኑ ጀርባ ትልቅ መልዕክት ምታስተላልፈው መልዕክት ነበረና ከሱ ጋር ተያይዞ ያጋጠመህስ ነገር?" የሚል ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ፤ "ብዙ ችግር ደርሶብኛል፡፡ አንዳንዶቹ ያስፈራሩኛል፣ አንዳንዶቹ ጠርሙስ ይወረውሩብኝ ነበር፣ ማስፈራሪያዎች በስልኬም ጭምር ይደርሱኝ ነበር፡፡" ይላል፡፡ አክሎም "እንከባበርን የዘፈንኩት የመጀመሪያው …እእእ… ተቀበል ያው ግጥሞቹን ስታስበው የነበሩት ነገሮች እነሱም ጤነኛ እንዳልነበሩ ታመው እንደነበረ እኛም ታመን እንደነበረ ያው በዛ ጊዜ እንትን ያልኩት የዘፈንኩት ነው፡፡ ከዛ በኋላ እንከባበር ደግሞ ሰውን መምታት ጀመሩ፣ መግደል ጀመሩ ምናምን ሰውም ደግሞ ገፍቶ መውጣት ጀመረ፡፡" ካለ በኋላ አገሪቱ ኢህአዴግ ቢወድቅ ማን ይመራታል የሚል አስተሳሰብ ላላቸው አገራችን ሌሎች ልጆችም አሏት ስለዚህ ዘፈኑን የዘፈንኩት ለዚህ ነው በማለት ይመልሳል፡፡

ባጠቃላይ የዚህ ወቅት ዘፈኖች የጊዜውን ፖለቲካዊ ሁነት መሰረት አድርገው የተዘፈኑ ሲሆኑ በወቅቱ ለነበረው ስርአት ማህበረሰቡ የነበረውን ስሜትም ያንፀባረቁ ናቸው፡፡ በሁሉም ዘፈኖች ውስጥ በጋራ የተገለፁት ሀሳቦች እንዳሉ ሆነው የዘፈኖቹ ዋናው ትኩረት የወቅቱን መንግስት

የተለያዩ አስተዳደራዊ ጉድለቶች እያነሱ ተቃውሟቸውን የገለፁ ነበሩ፡፡ ማህበረሰቡ በአንድም በሌላም መልኩ ያነሳቸው የነበሩ የተቃውሞ ሀሳቦች በዘፈኖቹ የተተኮረባቸው ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር በማህበረሰቡ ዘንድ የነበረው የዘረኝነትና የመከፋፈል አደጋ እንዲያከትምና የፖለቲካው አለመረጋጋት ለፈጠራቸው ለእነዚህ አደጋዎች ህዝብ እጅ ሳይሰጥ አገዛዙን በቁርጠኝነት እንዲቃወም ያነሳሱም ነበሩ፡፡ እነዚህ የወቅቱ ማህበረሰባዊ ስሜት የተንፀባረቀባቸው የተቃውሞ ዘፈኖች የመጋቢት 24/ 2014 ዓ.ም ለውጥ እንዲመጣ በተለያየ መልኩ ያበረከቱት የራሳቸው ድርሻ እንደነበራቸው ከላይ ከቀረበው ገለፃ መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.1.1.2. የዘፈኖቹ አንድምታ ትንተና ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር

ከላይ የዘፈኖቹን የጋራ ጭብጥና የወቅቱን ዋና ዋና ፖለቲካዊ ክስተቶች በተመለከትንበት ክፍል እንደተገለፀው ለውጥን ሽተው የተዘፈኑት ዘፈኖች ለ27 አመታት ስልጣን ላይ የቆየውን የኢህአዴግ መንግስት ለመጣል የተደረገውን ትግል እና የወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነት የሚቃኙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ በርካታ ዘፈኖች ውስጥም ለትንታኔ የተመረጡትን ‹‹አሁን ተነካሁ››፣ ‹‹ሰከን በል›› እና ‹‹ተቀበል ሁለት (እንከባበር)›› የተሰኙ ሶስት ዘፈኖች አንድምታ ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ለመተንተን ይሞከራል፡፡ ዘፈኖቹ በዋናነት ለውጥን ሽተውና የነበረውን ስርአት ተቃውመው የተዘፈኑ ናቸው፡፡

በጊዜው ከተዘፈኑና በአንድ በኩል ተቃውሞን በአንድ በኩል ደግሞ የህዝብ አንድነትን ከገለፁ ዘፈኖች መካከል በናትናኤል ‹‹አሁን ተነካሁ›› ዘፈን ውስጥ የምናገኛቸው፡-

‹‹የኔ ቤት ሲንኳኳ ካንተ ቤት ይዘልቃል

አፍንጫ ሲነካ አይንኮ ያነባል

ሰብስቦ ያቆየን ይህ ነበር ወጋችን

ዛሬም በአንድ ይሁን ሀዘንም ደስታችን››

የሚሉ ግጥሞች ከነበረው ወቅታዊ ፖለቲካዊ ሁነት አንፃር በተለያየ መልኩ አንድምታቸው ይታያል፡፡ በዘፈኑ የአንዱ ቤት መነካት የሌላውም መነካት እንደሆነ ከአፍንጫና አይን አለመነጣጠል እኩል የተገለፀበት መንገድ ከነበረው ወቅታዊ ሁነት አንፃር አንድም በተደጋጋሚ እንደተገለፀው ቀደም ሲል ከነበረው በበለጠ የ27 አመቱን የኢህአዴግ አገዛዝ የመቃወም

እንቅስቃሴ ከ2008-2010 ዓ.ም መጋቢት ወር የነበረው ህዝባዊ ትግል ትልቁን ድርሻ የሚሰጠው ነው፡፡ ጊዜው አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ብቻ የነበረው ተቃውሞ ቀስ በቀስ በርካታ አካባቢዎችን አዳርሶ የወቅቱ መንግስት ላይ ጫና ማሳረፉ ህዝብ የትኛውንም መሳሪያ ከታጠቀና ሀይል ካለው አካል እንደሚበልጥ የታየበትም ነው፡፡

አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያሳዩትም በብአዴን እና በኦህዴድ (የቀድሞ የኢህአዴግ አባል ድርጅት የነበሩ) እንዲሁም በሌሎች ለውጥ ፈላጊ አካላት ይመሩ የነበሩት ቄሮ እና ፋኖ ለለውጥ ቆርጠው የተነሱበት ነው፡፡ እነዚህ ሀይሎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በመንግስት ላይ ድምፃቸውን በማሰማት ተቃውሟቸውን ይገልፁ የነበሩበት ነው፡፡ ሰላማዊ የህዝብ ድምፅን ሰምቶ ችግርን በውይይት መፍታት ያለመደው የኢትዮጵያ ፖለቲካና መሪዎቹ ደግሞ ህዝቡን በያገኙበት የሚያስሩበት፣ አለፍ ሲልም በጥይት ደብድበው የሚገድሉበት፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች በየጊዜው በሚለቀቁ ዜናዎች የሞት ዜና ሳይሰማ የማያድርበት ጊዜ ነበር፡፡

እንዲሁም ደግሞ የእርስ በእርስ ግጭቱ በተለያዩ ሀይላት ቆስቋሽነት እያመረቀዘ የበርካታ ንፁሀን ዜጎች ህይወት ያለፈበትም ነው፡፡ በመሆኑም ናትናኤል ከላይ በተጠቀሱት ስንኞች አማካይነት አንድም እንደ አገራችን አኗኗር የጎረቤታችን ደስታና ሀዘን እኛንም በአንድም በሌላም መልኩ መንካቱ እንደማይቀር ይህ የሆነውም አኗኗራችን በሙሉ ከማህበር ያልተለየ ከመሆኑ የተነሳ እንደሆነ አፍንጫ እና አይን ካላቸው የአፈጣጠር ቅርበት እኩል በመግለፅ የእርስ በእርስ ግጭታችን መለያችን ሊሆን አይገባም የሚል ትምህርታዊ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡

ምክንያቱም  በፖለቲካ ትኩሳቱ የተነሳ በተለያዩ አካባቢዎች የእርስ በእርስ ግጭቶች ተፈጥረው የበርካቶች ህይወት ያለፈበት ጊዜ ነበር፡፡ ለምሳሌ በአማራ ክልል የአሁኑ ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አካባቢ የቅማንት ብሄረሰብና የአማራ ግጭት፣ በአሁኑ የሲዳማ ክልልና በወላይታ፣ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልል ዜጎች ወዘተ. የተነሱት ብሄር ተኮር ጥቃቶች ስንመለከት አፍንጫ ሲነካ አይን ካለቀሰ፤ የአንዱ ቤት ሲንኳኳ ሌላውን ከነካ እንዴትና ለምን እርስ በእርስ ተጋደልን፤ ኢትዮጵያዊ ባህላችንም ወጋችንም በግለኝነት የተመሰረተ ሳይሆን ሀዘኑም ደስታውም በማህበር የሚከወንበት ነው በማለት መነካጠል አለመቻላችንን በአፍንጫ እና በአይን መስሎ ያቀርባል፡፡ አንድም ደግሞ ወቅቱ ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው የተነሳ ታፍሰው የሚታሰሩበት፣ በእስር ቆይታቸውም ግፍና በደል ይደርስባቸው የነበረበት (የለውጡ ሰሞን ተጎጅዎች በተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ቀርበው የደረሰባቸውን ግፍ የተናገሩትን ማስታዎስ ይቻላል)፣ ለሰልፍ

ከወጡ ዜጎች በተጨማሪ መንገደኞች ሁሉ የተገደሉበት ጊዜ በመሆኑ አፈናውና ግድያው በተወሰኑ ሰዎች መታሰርና መሞት ብቻ እንደማያበቃ ይገልፃል፡፡ በተለይም ተቃውሞ ይሰማ የነበረባቸው አካባቢዎች በ2008 መጀመሪያ ሰሞን የተወሰኑ የአማራና የኦሮሚያ አካባቢዎች ብቻ መሆናቸውና በሌሎች አካባቢዎችና ክልሎች የሚገኙ ማህበረሰቦችን የሌሎች ግፍና በደል እናንተንም ሊያሳስባችሁና ልትታገሉ ይገባል የሚል የሚያነሳሳ መልዕክት አለው፡፡

ስለሆነም በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊ የሆን ሁሉ ደስታችንም ሀዘናችንም አብረን እያሳለፍን እንደመምጣታችን ዛሬም በተወሰኑ አካባቢዎች ዋጋ ለሚከፍለው ዜጋ ድምፅ እንሁን ተባብረን አፈናውንና ግድያውን እንቃወም የሚል አንድምታ አለው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመሳሳይ የሚገልፀው ሌላኛው ዘፋኝ ይሁኔም ‹‹ድር ቢያብር አንበሳ ያስር›› የሚለውን ንግግር ጠቅሶ በዘርና በሀይማኖት ሳይለያዩ መተባበር ያለውን ጠቃሚነትና መለያየቱ ደግሞ ለሞትና ለውድቀት ትልቁ ምክንያት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ቀጥሎም ዘፋኙ፡-

‹‹የወገን ጥያቄው ክብሩ ተመልሶ

በሰላም ለመኖር መግባባቱ ነግሶ

በስደት ያለውም ወደ አገሩ ገብቶ

በነፃነት ሊኖር እንደልቡ ገብቶ

እንደልቡ ወጥቶ

ተማምኗል ህዝቧ ላንዴና ለሁሌ

እልል እልል በሉ እንዲፈታ ህልሜ››

በሚል የገለፀው ሀሳብ አንድም ከነበረው ፖለቲካዊ ውጥረት አንፃር የህዝብ ጥያቄ እንዲመለስ፣ አንድነትና ሰላም እንዲሰፍን፣ ስደተኞች ወደአገራቸው እንዲገቡ ወዘተ. በመታገል ላይ ነኝ፤ ስለሆነም እነዚህ ጥያቄዎች የእናንተም ምኞት ከሆኑ እልል ብላችሁ ህልሜ እንዲሰምር በደስታ አብሮ በመሆን ግለፁ ማለቱ ነው፡፡

አንድም ደግሞ ‹‹እልል እልል በሉ›› ማለቱ እነዚህ ለህዝብ ዋጋ የተከፈለላቸው ተስፋዎች እንዲሳኩ በአንድ ላይ መውጣትና መታገል አለብን እንዲህ ሲሆን የተጠቀሱት ህልሞቻችን

አንድ ቀን እውን ይሆናሉ የሚል ነው፡፡ እንደተባለውም ህዝቡ ቢጋራ በመቆሙ ባመጣው ለውጥና በለውጡ ሰሞን በነበረው ሂደት ሰላም፣ እርቅ፣ ነፃነት እና ሌሎች የተወሰኑ ጥያቄዎች ተግባራዊ ሆነው ታይተዋል፡፡

የአገዛዙን ብልሹ አሰራርና መብት ረገጣ በመቃዎምና ለውጥ በመሻት በተዘፈነው የጌትሽ ማሞ ‹‹ተቀበል ሁለት እንከባበር›› ዘፈን ውስጥ በተካተቱና፡-

‹‹አንቺ ግፍ አትፈሪም በኔ ቤት ሆነሽ

ዳንቴል ትሰሪያለሽ ለዚያኛው ቤትሽ

ፍቅርሽ ቢያሳንሰኝ አንገት ቢያስደፋኝ

መቸ ከፋኝ አልኩኝ ስትከፊብኝ

አንቺን ተመርኩዘው ጊዜን ቢታደሉ

አለቃ ሆኑብኝ ዘመዶችሽ ሁሉ››

በሚሉ ስንኞች መግለፅ የተፈለገው ሀሳብ በአንድ በኩል በግፈኛ ሚስት የተመሰሉትን የወቅቱ ባለስልጣናት በገዛ አገሩ በሚኖር ዜጋ ላይ ያደርሱ የነበረውንና ከላይ የተጠቀሰውን በደል ያሳያል፡፡ በደሎቹ በናትናኤል ዘፈን ትንተና የተዳሰሱትና የፍትህ ስርአቱን እንደፈለጉ መዘወርን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ይህንንም ይሁን ብዬ ዝም አልኩ፤ የኔም ጭምር በሆነች አገር ላይ ስልጣን ነሽም ሰጭም አንቺ በመሆንሽ ያንችም የዘመዶችሽም አለቅነት አለቅጥ በዛ፡፡ በተቃራኒው እኔ ግን እንኳን ማዘዝ ይቅርና በነፃነት መኖር አልቻልኩም ይላል፡፡ በዚህም በገዛ አገሩ እኩል የስልጣን ተካፋይ ያልሆነውንና በነፃነት መኖር ያልቻለውን ዜጋ ብሶት ገልፆበታል፡፡ በሌላ በኩልም በኢህአዴግ ስርአት ውስጥ በነበሩት አራት ድርጅቶችና ሌሎች አጋር በሚል የተሰየሙ ድርጅቶች መካከል የነበረው ስልጣን ለደንቡ እንጅ አለቃውና የበላዩ ህወሀት እንደነበር የሚገልፅም ጭምር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

አንድም ደግሞ ‹‹ዳንቴል ትሰሪያለሽ ለዚያኛው ቤትሽ›› በማለት የተገለፀው ሀሳብ በዘፈኑ ስንኝ በቤት ከተመሰለችው አገርና ከድሀ ህዝቧ ላይ ለ27 አመታት ስልጣን ላይ የቆዩት የህወሀት ባለስልጣናት ለቅንጡ ኑሯቸው በተለያዩ አገራት ባንኮች ያስቀምጡ የነበረውን በግፍ የተሰረቀ ገንዘብ የሚገልፅ ነው፡፡ በተለያዩ አለማቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ እንደሚገለፀው

ኢትዮጵያ የከፋ ድህነት ውስጥ ካሉ አገሮች አንዷ ናት። ነገር ግን ለድህነቷ አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት በሙስናና በአስተዳደር ብልሹነት ከአገር በህገወጥ መንገድ የሚወጣው ገንዘብና በብድርና እርዳታ ስም የሚገባው ገንዘብ ለተፈለገው አላማ ሳይውል በባለስልጣናት እጅ መቅረቱ ነው። ኢህአዴግ ስልጣን ላይ በነበረባቸው 27 አመታት ብቻ ከኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መልኩ ተዘርፎ ለወጣው 36 ቢሊዮን ዶላር በቀጥታም በተዘዋዋሪም የባለስልጣናት ረጅም እጅ እንዳለበት ይታወቃል። (ታምራት ሀይሉ 2011፣3)። በዘፈኑ ለመግለፅ የተሞከረውም ይህንኑ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ስልጣን የያዙ ሰሞን ከከፍተኛ የመንግስት አካላት ጋር ባደረጉት የውይይት ፕሮግራም ላይ በውጭ አገር የባንክ ሂሳብ ከፍተው ገንዘብ በዶላር ባስቀመጡ ባለስልጣናት ላይ ምርመራ መጀመሩንና ገንዘቡ ተመላሽ እንደሚደረግ መግለፃቸውም ለዚሁ ነው። ይህም አንዱ በዘፈኑ ስንኞች ለመግለፅ የተሞከረ ጉዳይ ሲሆን በወቅቱ እነዚህንና ሌሎችን በደሎች መታገስ ያቃተው ህዝብ ስሜትም ተገልፆበታል።

## 4.1.2. የመጋቢት 24/ 2010 ዓ.ም ለውጥ መገኘት የወለዳቸው ደስታና ተስፋ በወቅቱ ዘፈኖች

### 4.1.2.1. የወቅቱ ፖለቲካዊ ሁነትና የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ

ከላይ በተመለከትናቸው ዘፈኖች በዋናነት ሲቀነቀን የነበረው በተለያዩ ቅሬታዎች ላይ የተመሰረተው የለውጥ ፍላጎትና ትግል ግብ መትቶ አዲሱና የለውጥ መንግስት መሪ የተባሉት የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር አብይ አህመድ በ2010 ዓ.ም መጋቢት 24 ቀን በይፋ ስልጣኑን ተረከቡ። በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣኑን ከተረከቡ በኋላ በበአለ ሲመታቸው ቀንና በተለያዩ ቦታዎች ለህዝብ ካደረጓቸው ንግግሮችና ከገቧቸው ቃሎች ባሻገር በጊዜው የፈፀሟቸው ተግባራት የህዝቡን ቀልብ መግዛት መቻላቸው ምንም እንኳን መሪው ከኢህአዴግ ቢመጡም በብዙዎቹ ዘንድ እንደአዲስና እንደለውጥ መሪ አስቆጠራቸው። ሚኒስትሩ ካደረጓቸው ንግግሮች ስለዘረኝነትና ክፋቱ፣ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፣ ለዜጎች ስለሚገባቸው ነፃነትና ዲሞክራሲ ከብዙ በጥቂቱ ይጠቀሳሉ። ከዚህ ባሻገር በዚያው በ2010 ዓ.ም ከመጋቢት እስከ ሀምሌ ባሉት ተከታታይ ወራት የለውጡ መንግስት በተግባር ያከናወናቸው በርካታ ተግባራት ነበሩ።

ከእነዚህ ውስጥም ግንቦት 17 ቀን እና በተከታታይ ቀናት በፖለቲካ አመለካከታቸው የታሰሩ እስረኞች አንዳርጋቸው ፅጌን ጨምሮ ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ተፈቱ፣ መጋቢት 28 ቀን

የማዕከላዊ እስር ቤት በይፋ ተዘጋ፣ ሰኔ 4 ቀን ወደአገራቸው የተመለሱትን የግብፅ እስረኞችን ጨምሮ በሌሎችም ቀናት በተለያዩ የባዕድ አገራት ታስረው የነበሩ ዜጎች ተፈትተው ወደ አገራቸው እንዲገቡ ተደረገ፣ በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ የተለያዩ ከተሞች ከዚህ ቀደም ባልተለመደ መልኩ ህዝባዊ መድረኮች ተዘጋጅተው ውይይቶች ተካሄዱ (ለምሳሌ በአገር ውስጥ ሰኔ 20 ከኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ጋር፣ መጋቢት 29 ህዝባዊ መድረክ በጅግጅጋ፣ ሚያዚያ 3 በአንቦ፣ ሚያዚያ 5 በመቀሌ፣ ሚያዚያ 7 አዲስ አበባ በሚሊኒየም አዳራሽ፣ ሚያዚያ 12 በጎንደር፣ ሚያዚያ 13 በባህር ዳር፣ ሚያዚያ 18 በአዋሳ፣ ሚያዚያ 23 በአሶሳ፣ ሚያዚያ 27 በባሌ፣ ግንቦት 12 በወለጋ፣ ግንቦት 13 በጋምቤላ፣ ወዘተ.) በዚህም የህዝቡን የልብ ትርታ ለማዳመጥ ጥረት ተደረገ፣ በውጭ አገራት የነበሩና ወደ አገር ቤት እንዳይገቡ እገዳ የተጣለባቸው የተለያዩ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ወደ አገራቸው እንዲገቡ ጥሪ ተደረገ (በጥሪውም ግንቦት 15 የቀድሞ የኦነግ አመራር የነበሩት ሌንጮ ለታና የፓርቲው አመራሮች ወደ አገር ገቡ፣ ሰኔ 14 ግንቦት ሰባት የተቃዋሚ ድርጅት የሰላም ጥሪውን ተቀበለ፣ ሰኔ 24 የኦነግ አመራር ጀነራል ከማል ገልቹ አዲስ አበባ ገቡ…)፡፡ እንዲሁም ሰኔ 23 ቀን በአሸባሪነት ተከሰው የነበሩት ፓርቲዎችና የመገናኛ ብዙሀን (ግንቦት ሰባት፣ ኢሳትና ኦ.ኤም.ኤን) ክሳቸው ተነሳ፣ ሀምሌ 2 ቀን ከኤርትራ ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት ጋር የነበረው አለመግባባት መቋጫ አግኝቶ እርቀ ሰላም ወረደ፣ በተለያየ ምክንያት ግጭት ውስጥ የቆዩ የተለያዩ የሀይማኖት ተቋማት ወደ አንድነትና ሰላም እንዲመጡ ጥረት ተደረገ (በኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሁለቱ ሲኖዶሶች፣ በእስልምና ሰኔ 26 የተካሄደው የሙስሊሙና የመጅሊሱ) እነዚህን የመሳሰሉና በርካታ ተግባራት በወራቶች ውስጥ ተከናወኑ፡፡ (ሙሃባው ገድፍ 2011፣174-180)፡፡

በመሆኑም እነዚህ ጉዳዮች በጠቅላላ የህዝቡን ቀልብ መግዛታቸው አዲሱን የለውጥ መንግስት እንደለውጥ እንዲቆጠርና ተቀባይነት እንዲያገኝ አስቻሉ፡፡ በእነዚህ ንግግሮችና ተግባሮች መነሻነት ሌሎችን በንግግር ደረጃ የተሰሙ ሰላም፣ ደህንነት፣ ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲ ወዘተ. እንደሚተገበሩ ተስፋ በማድረግ የለውጡን መንግስት እስከ መሪዎቹ የሚያወድሱ በርካታ የጥበብ ስራዎች ተሰሩ፡፡ ከእነዚህ ስራዎች መካከል ደግሞ ዘፈኖች ሲጠቀሱ የአዲስ ሙላት ‹‹አገሬን››፣ የአቡሽ ዘለቀ ‹‹አነቃን››፣ የጌትሽ ማሞ ‹‹ተቀበል አራት›› የወቅቱን ፖለቲካዊ ክስተት መሰረት በማድረግ ለዚህ ጥናት የተመረጡ ናቸው፡፡ ዘፈኖቹ ከላይ የተገለፁትን ሁሉንም ሁነቶች የሚያስቃኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ለማሳያነት የተመረጡ ሶስት

ዘፈኖች የያዙትን የጋራ መልዕክት ቀጥሎ ከዘፈን ግጥሞቹ ውስጥ በማሳያነት እየወሰድን እንመለከታለን፡፡

የእነዚህ ሶስት ‹‹አገሬን››፣ ‹‹አነቃን››፣ ‹‹ተቀበል አራት›› የተሰኙ ዘፈኖች ዋናው የጋራ ጭብጣቸው ሙገሳ፣ ያለፈውን ስርአት ትችት፣ የዘረኝነትን አላስፈላጊነትና ተስፋን መግለፅ ነው፡፡ ድምፃዊ አዲስ ሙላት የለውጡን መንግስትና መሪዎቹን ባሞገሰበት ‹‹አገሬን›› በተሰኘው ዘፈኑ፡-

‹‹ለማ ለማ ሲሉኝ አረሙን መስሎኛል

ለካስ ጤናአዳም ነው መድሀኒት ሆኖኛል

አብይ አብይ ሲሉ ያው ያሙን ነው ብዬ

ሰውም አብይ አለው ኸረ እናንተ ሆዬ

እንዴት አድሯል አባይ ያ ፈለገ ጣና

ገዱን ያመጣልኝ አድርጎ ባለዝና››

በማለት የለውጡን መንግስትና የመሪዎችን ስም እየጠራ ሲያሞግስ፤ ያለፈውን ስርአትና የስርአቱን መሪዎች ደግሞ፡-

‹‹ሲነዳን ኖሮ ስንቱ እንከፍ ጋሬጣ

ይገዛኛል ያልኩት አባት ሆኖኝ መጣ

ወንድም ሆኖኝ መጣ››

በማለት አዲሱን አሞግሶ የነበረውን ይተቻል፡፡ ስለነበረው የዘረኝነት መንፈስ እና በአዲሱ መንግስት በወቅቱ ይቀነቀን ስለነበረው የኢትዮጵያዊነት ስሜትም እንዲህ ሲል ይገልፃል፡፡

‹‹አይከፋፈልም አገር እንደ ቅርጫ

አንከፋፈልም በመደብ በቅርጫ

መደመር ብቻ ነው ያለን አንድ ምርጫ››

ይህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካደረጓቸው ንግግሮች ውስጥ ስለኢትዮጵያዊነትና ስለአብሮነት ከተናገሩት የተቀዳ ሲሆን ዘፋኙም በንግግሩ ያለውን ደስታና ተስፋ ገልፆበታል፡፡ በዘፈኑ የተገለፀው ሀሳብ በተለያዩ ወቅቶች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተናገሯቸው የህዝብን ቀልብ ከሳቡ ንግግሮች ውስጥ፡-

> ይሄ አገር የወረስነው አገር አይደለም፡፡ ከአባትና ከእናቶቻችን የወረስነው ሳይሆን ከልጆቻችን የተዋስነው አገር ነው፡፡ ውርስ ሊሸጥ ሊለወጥ ይችላል፡፡ ውሰት ግን ታጥቦና ተፀድቶ የሚመለስ ነው፡፡ አሳምረን ማሸጋገር አለብን… መጠፋፋት ለማንም ጤነኛ ሰው ምርጫ ሊሆን አይችልም፡፡ ያለን ምርጫ መደመር ብቻ ነው፡፡ ያለን ምርጫ አንድ መሆን ብቻ ነው፡፡ መተጋገዝ መደጋገፍ ብቻ ሳይሆን በጋራ ለመኖር መደመር ነው፡፡ (ታምራት ሀይሉ 2010፣4)፡፡

ያሉትን መሰረት ያደረገ እና ይህንኑ የሚገልፅ ነው፡፡ ይህ በንግግር ደረጃ የተሰማ መደመርና አንድነት እንደማይቀለበስ ያለውን ተስፋም በሌላ መልኩ፡-

‹‹እኔን ከፋኝ ብልስ አገሬን መች ከፋው

ወገኔን መች ከፋው

ፍቅር አበቀለ ጥላቻ እማይገፋው››

ሲል ይገልፃል፡፡ ይህን ሲገልፅ የተዘራው የዘረኝነት ስሜት አዲስ እየተዘራ ባለው የመደመር ሀሳብ ኮስምኖና በምትኩ ጥላቻ ሊገፋው የማይችል ፍቅር እንደሚበቅል በመተማመን ነው፡፡

እነዚህ ሀሳቦች ደግሞ በሌላኛው ዘፋኝ አቡሽ ዘለቀ ‹‹አነቃን›› የዘፈን ግጥሞች ውስጥ በሚከተለው መልኩ ተገልፀዋል፡፡ አቡሽ ከዘፈኑ ርዕስ ጀምሮ አነቃን በማለት የለውጡን መንግስት ሲያሞግስ፡-

‹‹አነቃን አንዱ ካንዱ ሳያንስ አንዱ ካንዱ ሳይበልጥ

ከኔ ወንዝ አይደለህ ከኔ ወንዝ አይደለሽ

ብለን ሳንጣላ ብለን ሳንለያይ

አገር ማለት እኛ እኛ ማለት አገር ብሎ አበሰረን

ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ ነን››

በማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለእኩልነት፣ ስለአገር ፍቅር ወዘተ. የተናገሯቸውን አባባሎች በማንሳት ነው፡፡ በተቃራኒው ከለውጡ በፊት የነበረውን መንግስት ከለውጡ ጋር በማነፃፀር ሙገሳውን በማጉላት ላለፈው ስርአት ትችቱን የገለፀበት መንገድ ነባሩንና አዲሱን መንግስት በትይዩ በማንሳት ነው፡፡ ነባሩን ከአሁኑ ሲያነፃፅር ደግሞ ከአርበኞቹ ሀውልት በታች ከሚገኘው ሰፊ ቤተ-መንግስት ከክፉት እንራቅና ተዋደን በይቅርታ እንኑር የሚል ጀግና መሪ ባለፉት 27 አመታት ውስጥ አላየንም፤ ዛሬ ግን ይህን ብስራት የያዘ ጀግና መጣልን በማለት ነው፡፡ ይህ ስሜትም በወቅቱ የበርካታው ህዝብ ስሜት ነበር፡፡ ይህንንም፡-

‹‹አነቃን ከአርበኞቹ ሀውልት ትንሽ ዝቅ ብሎ

ከዛ ሰፊ ግቢ ሰው ከማይደርስበት

አዲስ ነገር ሰማን ሰምተን ማናውቀውን

ደስታችን ወደር አጣ ፍቅር ያሸንፋል

ከክፉት እንራቅ ከበቀል እንፅዳ

ተዋደን እንኑር የሚል ጀግና መጣ›› ሲል ይገልፀዋል፡፡

ከግጥሙ እንደምንረዳው የለውጡ መንግስት አዳዲስ ሀሳቦች በዘፈኑ የአራት ኪሎ ግቢ በሚል ከተገለፀው ቤተ-መንግስት ከዚህ ቀደም ተሰምተው እንደማይታወቁ በመግለፅ የለውጡን መንግስትና መሪ ሲያሞካሽ በወቅቱ መሪው ያደርጉ በነበረው ንግግር ደስታው ወደር ያልነበረውን ህዝብ ስሜትም ጭምር በማካተት ነው፡፡

መሪው ስልጣን ከያዙበት ቀን ጀምሮ ከአፋቸው ያልጠፋውን ኢትዮጵያዊነትና አንድነት ጨምሮ በተደጋጋሚ ከተናገሯቸው ንግግሮች ውስጥ “ወቅቱ ከስህተታችን ተምረን አገራችንን የምንክስበት ወቅት ነው፣ ማንነታችን እንዳይለያይ ሆኖ የተሰናሰለ፤ እንዳይነጣጠልም ሆኖ የተገመደ፤ የተዋደደና የተዋሀደ ነው፣ ኢትዮጵያ የሁላችን አገር የሁላችን ቤት ናት፣ እኛ ኢትዮጵያዊያን ዲሞክራሲና ነፃነት ያስፈልገናል፤ ይገባናልም፣ መጭው ጊዜ በኢትዮጵያ የፍቅርና የይቅርታ ጊዜ ነው፡፡” (ጌትነት አዳሙ 2010፣26)፡፡ የሚሉት የመሪው ንግግሮች በወቅቱ ይህን መሰል ንግግር ከባለስልጣናት መስማት ብርቅ የሆነበትን ዜጋ ለድጋፍ ያነሳሱ

ነበሩ። እንደ ታምራት ሀይሉ (2010፣5) መረጃ ከሆነ በማኔጅመንትና በማህበራዊ ጥናትና ምርምሮች አማካሪነት የሚሰራው ዋስ ኢንተርናሽናል የተሰኘ ተቋም ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከተውጣጡ 1505 ሰዎች ላይ ባካሄደው ጥናት "84 በመቶ ያህሉ ኢትዮጵያውያን በዶ.ር አብይ ደስተኞች መሆናቸውን ጠቁሟል።" ይላል። በመሆኑም በዘፈኑ በወቅቱ የነበረው የአብዛኛው ማህበረሰብ ስሜት ተገልፆበታል። በሌላ በኩል ተዋዶ በእኩልነት መኖር እንደሚያስፈልግና የዘረኝነትን አላስፈላጊነት ሲያስረግጥም፡-

‹‹አነቃን አስተውለን ካየን ታሪክ ሳንረሳ

የአብሮነቱን ገመድ ቋጠሮን ሳንፈታ

የሚያግባባን ብዙ የሚያስማማን ብዙ

ሰፊውን በር ዘግተን ጠባቡን አናንኳኳ

ኢትዮጵያዊነቱ ነው ያስተሳሰረን ጎልቶ ይታይ በቃ!››

በማለት ነው። በዚህም አብሮ መኖር እንድንችል የሚያደርግ ብዙ ትውፊት እያለን አንድ ልዩነት እየፈለግን ኢትዮጵያዊነታችንን አንርሳ የሚል መልዕክትን ያስተላልፋል። በተጨማሪም ክፉ ደግ ባየንባትና ደስታዋ ደስታችን ሀዘኗ ሀዘናችን በሆነች አገራችን በሰላም መኖር የሚቻልበት ጊዜ መምጣቱንና ስለወደፊቷ የሚታየውን የተስፋ ብርሀን፡-

‹‹ባንቺ ሰማይ ጥላ ስር ክፉ ደጉንም አይተናል

ሌላ እናት ሀገር የለንም ሲከፋሽም ይከፋናል

ባንቺ ሰማይ ጥላ ስር የተስፋ ብርሀን ይታየናል

ሌላ እናት ሀገር የለንም ደስ ሲልሽ ደስ ይለናል››

ብሎ ሲገልፅ ይህን የተስፋ ብርሀንና የፍቅር ጉዞ የሚቀለብሰው እንደማይኖር ያለውን ተስፋና ምኞትም በሚከተለው መልኩ ያስደምጣል።

‹‹ማነው ማነው ማነው

ማነው ሚመልሰን?

ማነው ማነው ማነው

ከዚህ ቀና መንገድ?

ማነው ማነው ማነው

ከዚህ የፍቅር ጉዞ?

ማነው ማነው ማነው

ወደፊት ነው እንጅ?

ማነው ማነው ማነው

እጅ ለእጅ ተያይዞ?››

በሁለቱ ዘፈኖች በአዲስ እና በአቡሽ የተነሱት ሀሳቦች በጌትሽ ማሞ ዘፈን ውስጥም የሚገኙ ናቸው፡፡ ጌትሽ በ‹‹ተቀበል አራት›› ዘፈኑ የለውጡን መንግስትና መሪዎች ሲያሞግስ፡-

‹‹እስኪ ላወድሰው ላወዳድሰው

ከነሙሉ ክብሯ ስሚን ለጠራው

ይኼን ጀግና እስቲ ልጥራው

ቄሮ ፋኖ ስማ አንተ የአገር አርማ

ልጥራው ልጥራው

ቄሮ ፋኖ ስማ አንተ የአገር አርማ››

በማለት ጀምሮ በርካታ የለውጡን መሪዎች ስምና ተግባር በማንሳት ያሞካሸ ሲሆን ለለውጡ መምጣት ግንባር ቀደም የነበሩትንና ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉትን የኦሮሞ ቄሮ እና የአማራ ፋኖ በማወደስም ነው፡፡ ነባሩን መንግስት ከአሁኑ ጋር በማነፃፀር ሲተችም፡-

‹‹ካሰገደደው ናና ይዞ ምንሽር

ለኔ ይልቃል ናና የያዘ ፍቅር››

ይላል፡፡ በዚህም በነባሩ መንግስት የነበረውን በወታደርና በመሳሪያ ጉልበት ተማምኖ የህዝብን ጥያቄ ማፈን በመተቸት የሚከበረውም የሚበልጠውም ፍቅር ይዞ የመጣው እንደሆነ ይገልፃል፡፡ እንዲሁም ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያዊነትን የሚያስበልጥ መሪና ስርአት እንደሚያስፈልግና በወቅቱም ይህ መሪ እንደመጣ ሲገልፅ፡-

‹‹አወይ ጊዜ ደጉ አወይ ጊዜ ዳኛው

ስንቱን አሳለፍነው ከፍተን እኛው በእኛው

አያመጣው የለ ይኄው ቀን ከሌት

ይንቆለጳጰሳል ኢትዮጵያዊነት››

በማለት በወቅቱ በባለስልጣናት ተደጋግሞ ይነገር የነበረውን የዘረኝነት አላስፈላጊነት እንዲሁም በኢትዮጵያዊነት አንድ የመሆንን ሀሳብ ያንፀባርቃል፡፡ በወቅቱ ስልጣን የያዙት አዳዲስ አመራሮች ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ደጋግመው ይናገሩ የነበረበት ጊዜ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ በባህር ዳር ከተማ በተካሄደ መድረክ የለውጡ ዋና አመራር የነበሩት አቶ ለማ መገርሳ በወቅቱ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚከተለውን ማለታቸው የሚታወስ ነው፡፡

> ለሁላችንም ብዥ ብሎብን የነበረው ኢትዮጵያዊነት ምን እየሆነ ነው? የሚለው በብዙዎቻችን አዕምሮ ውስጥ ግርታን ሳይፈጥር የቀረ አይመስለኝም፡፡ ምናልባትም ለብዙዎቻችንም ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ፡፡ ለኔም በእውነት ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆነ ዛሬ ባየነው ትዕይንት እዚህ መድረክ ላይ ባየነው ትዕይንት በሚገባ ተገልጦልኛል ለኔ፡፡ ኢትዮጵያዊነት ስሙ ባያምርም ሞክሬው ባላውቅም ሀሺሽ ነው፤ ሱስ ነው ኢትዮጵያዊነት፡፡ (ታምራት ሀይሉ 2011፣6)፡፡

ዘፋኙ በዘፈኑ ‹‹ይንቆለጳጰሳል ኢትዮጵያዊነት›› በማለት የገለፀው ይህንኑ እና መሰል ሌሎች የባለስልጣናትን ንግግሮች ለመደገፍና የወቅቱን የኢትዮጵያዊነት ስሜት ለማንፀባረቅ ነው፡፡ ይሄ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዳይጠፋና ባለስልጣናቱም ህዝቡም ወደነበሩበት እልቂት፣ ዘረኝነትና መከፋፈል እንዳይመለሱ ያለውን ተስፋና ምኞትም፡-

‹‹እንግዲህ ካደለን የምህረቱን አመት

እንግዲህ ከታደልን የምህረቱን አመት

ተዋዶ መኖሩን በይ እንወቅበት›› ሲል ይገልፃል፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ወቅት የተዘፈኑት ዘፈኖች ከላይ እደተገለፀው ለውጡንና የለውጡን መሪዎች ማሞገስ፣ ያለፈውን መተቸት፣ የዘረኝነትን አላስፈላጊነትና በለውጡ ላይ ያላቸውን ተስፋ መግለፅ ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ የሙገሳቸው መነሻም የህዝብ ስሜትና የለውጡ አመራሮች ስለኢትዮጵያዊነትና አንድነት የተናገሯቸው ንግግሮች እንዲሁም በተግባር የታዩ ከላይ የተጠቀሱት አንዳንድ ለውጦች ናቸው፡፡ ይሁንና ብዙም ሳይቆይ እነዚህን በተስፋ የተዘመረላቸውን ንግግሮችና አንዳንድ ተጨባጭ ለውጦች የሚያደናቅፉ ክስተቶች መከሰት ጀመሩ፡፡ የእነዚህ ክስተቶች መነሻ የተለያየ ቢሆንም ህዝብ የናፈቃቸውና በደስታ የዘመረላቸው ኢትዮጵያዊነት፣ አንድነት፣ ሰላም፣ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ነፃነት፣ ወዘተ. እየተሸረሸሩ ወደ ቀደመው ሁኔታ ተመለሱ፡፡

የዜጎች በማንነት መገፋትና መገደል፣ የተበዳዮች ፍትህ ማጣት፣ የሰላማዊ ዜጎች በሰላም ወጥቶ አለመግባት፣ የመንግስት ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የጎደለው አሰራር ከቀደመው ስርአት ከፍቶ ቀጠለ፡፡ በዚህም አብዛኛው የለውጡ ደጋፊ የነበረ ህዝብ በለውጡ ላይ የነበረው ተስፋና ትዕግስት እየተሟጠጠ ሄደ፡፡ ከዚህ የተነሳ በዚህ የጊዜ ክልል መድበን የተመለከትናቸውና ለውጡን አሞግሰው የዘፈኑት ሶስቱም ዘፋኞች መልሰው የህዝቡን ስሜትና ተስፋ መቀማት ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ማቀንቀን ጀመሩ፡፡

## 4.1.2.2. የዘፈኖቹ አንድምታ ትንተና ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር

ከዚህ በፊት እንደተገለፀው እነዚህ ከመጋቢት 24 ቀን 2010-2011 ዓ.ም የተዘፈኑ ዘፈኖች በዋናነት የሚገልፁት ሙገሳን፣ ተስፋንና የአንድነትን አስፈላጊነት ነው፡፡ በጊዜው የተዘፈኑ ዘፈኖች እንደሌሎቹ ሁሉ የወቅቱን ማህበረ ፖለቲካዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ በዘፈኖቹ የተላለፉት መልዕክቶች አንድምታ ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ሲተነተን ምን እንደሚመስል ለመመልከት እንሞክር፡፡

አዲስ ሙላት ለውጥ በመገኘቱ ደግፎ፣ ያለፈውን አስተዳደር ተችቶና የአንድነትን አስፈላጊነት ገለፆ ለወደፊት በለውጡ መንግስት ላይ ያለውን ተስፋ ባካተተበት ‹‹አገሬን›› የተሰኘ ዘፈኑ፡-

‹‹ለቆረጡት ስጋ ላፈሰሱት ጠጅ

ከፋዩ አንተ ነህ በርትተህ ስራ እንጅ››

በሚል የተገለፁት ስንኞች የተለያየ አንድምታ ያላቸው ናቸው፡፡ ወቅቱ ለውጥ የመጣበትና የመጣው ለውጥም ከነባሩ ስርአት በመምጣቱ ህዝቡ እንዳዲስ ለውጥ መቀበል ስለሚያስቸግረው በርትቶ መስራትን እንደሚጠይቅና ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል ህዝብም ለደረሰበት እንግልት ሁሉ ካሳ እንደሚያስፈልገው የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ሲባል አንድም በእስር ቆይታው ዋጋ ለከፈለው፣ ከቀዬው ተፈናቅሎ ሀብትና ንብረቱ ለወደመበት፣ በጥይት ደሙ ለፈሰሰው ሁሉ እንደምትክስ ተስፋ አድርገናል በርትተህ በመስራት ፍትህ፣ ሰላምና እኩልነት አስፍን የሚል መልዕክትን ለአዲሱ መሪ የሚነግር ነው፡፡ ይህ በዘፈኑ አንድምታ የተገለፀው መልዕክትም አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣኑን በተረከቡበት 2010 ዓ.ም መጋቢት 24 ቀን ለ35 ደቂቃዎች በቆየ ንግግራቸው ውስጥ ካደረጓቸው ንግግሮች አንዱ ነበር፡፡

በወቅቱ ሚኒስትሩ "በተለያየ ጊዜ መስዋዕትነት ለከፈሉ የመብት ተከራካሪዎች፣ ፖለቲከኞች፣ በቅጡ ሳይቦርቁ ህይወታቸው ለተቀጠፈ ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች፣ ለስነልቦናዊና አካላዊ ቀውስ ለተዳረጉ ቤተሰቦችና ግለሰቦች ከልብ የመነጨ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡" (ታምራት ሀይሉ 2010፣ 6)፡፡ በማለት የተናገሩት ንግግር በዘፈኑ ለመግለፅ የተሞከረው ሀሳብ ነው፡፡ በእርግጥ ሚኒስትሩ ይህንን ያሉት እሳቸውም በአመራር የነበሩበት መንግስት ጥፋቱን በመፈፀሙ ከተጠያቂነት ለመዳንና በይቅርታ ለማለፍ ሊሆን ይችላል፡፡ በዘፈኑ ‹‹ከፋዩ አንተ ነህ›› በሚል መገለፁ ደግሞ ሀላፊነት ከመውሰዳቸውና ይቅርታ ከመጠየቃቸው የመነጨ ነው፡፡ ለዚህም ነው የተቆረጠው ስጋና የፈሰሰው ጠጅ በየእስር ቤቱ ለተሰቃዩትና በየሰልፉ ደማቸው ለፈሰሰው ምሳሌነት ተወስዶ በአንድምታ መታየቱ፡፡

አንድም ደግሞ ባለስልጣናቱ ለቅንጦት ህይወታቸው ከድሀ ኢትዮጵያውያን ለመዘበሩትና አገሪቱ ለተዘፈቀችበት እዳ የምትከፍለው አንተና አንተ የምትመራው መንግስት ነው የሚል ነው፡፡ እንደሚታወሰው ሚኒስትሩ ስልጣን በያዙ ሰሞን አገሪቱ ከፍተኛ የእዳ ቁልል ስላለባት እሱን ለማስተካከል እየተሰራ መሆኑንና ከአበዳሪ ድርጅቶች የእዳ ስረዛ እንዲደረግላቸው ያደረጉትን ጥረት፣ ከአረብ አገራትና ከተለያዩ አገራት በእርዳታ ያገኙትን ድጎማ በተለያዩ መገናኛ ብዙሀን ሰምተናል፡፡ እንዲሁም በ2010 ዓ.ም ሚያዚያ 8 ቀን በአገር ውስጥ ካሉ ባለሀብቶች ጋር በተወያዩበት ወቅት አገሪቱ ከፍተኛ የዶላር እጥረት እንዳለባት ጠቅሰው ሁሉም በዱባይ ያስቀመጠውን ቢያስገባ ያሉበት ንግግራቸው እና ሌሎችም ንግግሮቻቸው አገሪቱን ከእዳ ጫና ለማላቀቅና በራሷ እግር እንድትቆም የሚለፉ መሪ እንደሆኑ እምነት ስለተጣለባቸው በዘፈኑም

ሌሎች ላጠፉት ጥፋት ሁሉ እየሰራህ ያለኸው አንተ ነህ አሁንም በርትተህ ስራ በሚል ለመሞካሸታቸው ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ሌላው በዚህ ዘፈን ግጥም ውስጥ፡-

‹‹ለማ ለማ ሲሉኝ አረሙን መስሎኛል

ለካስ ጤና አዳም ነው መድሀኒት ሆኖኛል››

በሚል የተጠቀሱት ስንኞች አንድም ለውጥ መጣ ሲባል ከቀደመው ስርአት የመጣ ለውጥ ለውጥ ነው ብዬ አምኜ ለመቀበል ተቸግሬ ነበር፤ ምክንያቱም ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም ነውና ነገሩ ለውጡ የሰው እንጅ የስርአት ባለመሆኑ ለውጥ ሲሉኝ አልተቀበልኩትም፡፡ ነገር ግን ተስፋ ሰጭ ንግግሮችንና አንዳንድ ተግባሮችን ስመለከት ለውጡ እውነተኛ እንደሆነ አመንኩ የሚል ሲሆን የወቅቱን የተዘበራረቀ የህዝብ ስሜትም ጭምር የሚገልፅ ነው፡፡ አንድም ደግሞ ለውጡን ለማምጣት ቀዳሚ ስፍራ አላቸው የሚባልላቸውን አቶ ለማ መገርሳን ለታመምኩት የፖለቲካ ህመም መድሀኒት ሆነውኛል በማለት የሚያወድስ ነው፡፡

ቀጥሎ ደግሞ፡-

‹‹አምናም ፆመን ነበር ዘንድሮም እንደዛው

ዘንድሮስ ፈሰክን የምንፈታው በዛ

ጳጳስ ቄስ አልጠፋ በሀገር በቤቱ

ስብሀት እያሉ ምነው የማይፈቱ››

በሚል የተገለፀው ግጥም አንድም አምናም ታች አምናም ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ባጠቃላይ ለውጥ ለማምጣት ታግለናል ትግላችን ፍሬ ያፈራው ግን ዘንድሮ ነው የሚል ነው፡፡ ዘንድሮ በመጣው ለውጥ ነፃነት የተጠሙ ነፃነትን፣ በእስር ቤት ያሉ ፍትህን አግኝተው ተፈቱ፤ የዘንድሮ ፆማችን ለብስራትና ለእውነተኛ ፋሲካ ሆነ ይላል፡፡ ይህንን ለማለት ያስቻለውም ወቅቱ የፆም ወቅት መሆኑና በርካታ እስረኞችም ከእስራት የተፈቱበት በመሆኑ ነው፡፡

አንድም ደግሞ በፊት የነበሩ ባለስልጣናት የመጡበት አካባቢ የሀይማኖት አገር እየተባለ ይጠራል፡፡ ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ እንኳን ስብሀት እያሉ ነው እንደዚህ ከሆነ ለጥሩ ስራ

እንዴት ቅንነት አነሳቸው የሚል ነው፡፡ በዚህም መጠሪያ ስማቸውም ሆነ አካባቢያቸው አይገልፃቸውም ስምና ተግባራቸው ለየቅል ነው በማለት በትችት ይገልፃል፡፡

ጌትሽ ማሞም ተቀበል አራት በተሰኘ ዘፈኑ፡-

‹‹ደመቀ አገሩ ገዱ ቢቀናቸው

የለማ ሆነና አብይ ጉዳያቸው››

ሲል ባዜመበት ክፍል በአንድ በኩል በወቅቱ የነበረውን ወደር የሌለው የህዝብ ደስታና የድጋፍ ድምፅ ሲገልፅ አንድም ደግሞ ለለውጡ ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው ከሚባሉት ውስጥ የአራቱን ማለትም የደመቀ መኮንን፣ የገዱ አንዳርጋቸውን፣ የለማ መገርሳንና የአብይ አህመድን ስም በመጥራት ያሞገሰበት ነው፡፡ በወቅቱ ህዝቡም እነዚህንና ሌሎችን በርካታ ለለውጡ ዋጋ የከፈሉ ሰዎችን በየማህበራዊ ሚዲያው ሲቀባበላቸውና ሲያወድሳቸው የነበሩ ናቸው፡፡

በወቅቱ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከለውጡ መሪዎች ተደጋግሞ የሚነገርና ህዝቡን ወደ አንድነት ያመጣ ነበር፡፡ በወቅቱ ለለውጡ መሪዎች ድጋፍ ለመስጠት በሚደረጉ ሰልፎች የሚደመጡ መፈክሮችም ‹‹ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ ነን››፣ ‹‹ያለን አንድ አማራጭ አንድነትና መደመር ብቻ ነው››፣ ‹‹ኢትዮጵያዊነት ከዘር በላይ ነው››፣ ወዘተ. የሚሉ የኢትዮጵያዊነትን ስሜት ከፍ የሚያደርጉ ከመሪዎች የተወሰዱ መፈክሮች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጊዜያት የተደመጡ ዘፈኖችም ይህን የህዝብ ደስታና የኢትዮጵያዊነት ስሜት ያንፀባረቁ ነበሩ፡፡

አቡሽ አነቃን በተሰኘ ዘፈኑ፡-

‹‹አነቃን አስተውለን ካየን ታሪክ ሳንረሳ

የአብሮነቱን ገመድ ቋጠሮን ሳንፈታ

የሚያግባባን ብዙ የሚያስማማን ብዙ

ሰፊውን በር ዘግተን ጠባቡን አናንኳኳ

ኢትዮጵያዊነቱ ነው ያስተሳሰረን ጎልቶ ይታይ በቃ!››

በማለት ሲገልፅ አንድም አነቃን ማለቱ የለውጡን መሪ በማወደስ መሪያችን የዘረኝነት ጉንፋን በየጊዜው እያገረሸ ኢትዮጵያዊነት ኮስሶ በዘራችን እንጅ በኢትዮጵያዊነታችን ማሰብ ባቆምንበት ሰአት ስለኢትዮጵያዊነትና መደመር ሰብኮ ከመንገዳችን መለሰን ማለቱ ነው፡፡ ከለውጡ መሪ የተሰሙ ትልቁ ማንነታችን ኢትዮጵያዊነታችን ሆኖ እያለ አንዳንድ የቆየ ቂም እያነሳን፣ በጠባብ መንገድ እየሄድን ኢትዮጰያዊነታችን ዘንግተናል፣ ኢትዮጰያዊነታችን ከዘር በላይ ነው የሚሉ ንግግሮች ደስታችን ወደር እንዲያጣና ከዘረኝነት እንቅልፋችን እንድንነቃ አድርገውናል የሚል አንድምታ አለው፡፡

አንድም ደግሞ ህዝቡ በመንግስት በኩል ይደረጉ ከነበሩ ጫናዎች አንፃር ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ ፈታኝ እንደሆነ፣ ለውጥ እንደማይመጣና በልዩነት የሚደርስ ጥቃት እንደማያቆም ተስፋ ቆርጦ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደ ህልም ይታይ የነበረው ለውጥ እውን ሆነ ማለቱ ነው፡፡ ጌትሽም በተቀበል አራት በተሰኘ ዘፈኑ ይህንን የወቅቱን የኢትዮጰያዊነትና የአንድነት ስሜት በሚከተለው መልኩ ገልፆት ነበር፡፡

‹‹አወይ ጊዜ ደጉ አወይ ጊዜ ዳኛው

ስንቱን አሳለፍነው ከፍተን እኛው በእኛው

አያመጣው የለ እሄው ቀን ከሌት

ይንቆለጳጰሳል ኢትዮጰያዊነት››

ከግጥሙ እንደምንረዳው ጌትሽ የወቅቱ የኢትዮጰያዊነት ስሜት ለውጡ ያመጣው እንደሆነ ጊዜ ደግ ነው፤ ኢትዮጰያዊነታችን ደምቆ እንዲታይና በልዩነታችን ሳንከፋፈል ኢትዮጰያዊነታችን እንዲሰበክ አደረገ በማለት የወቅቱን ማህበረ ፖለቲካዊ ድባብ በወቅቱ የለውጥ መሪዎች ንግግር መነሻነት ይገልፃል፡፡

### 4.1.3. በለውጡ ባለመርካት ከ2011-2013 ዓ.ም የተዘፈኑ ዘፈኖች

#### 4.1.3.1. የወቅቱ ፖለቲካዊ ሁነትና የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ

የ2010 ዓ.ም ለውጥ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት የነበረውና ከላይ እንዳየነው የአብዛኛውን ማህበረሰብ የደስታ ስሜት የሚገልፁ የድጋፍ ዘፈኖች የወጡበት ነበር፡፡ ነገር ግን በጊዜ ሂደት

የተጠበቁትና በዘፈኖቹ የተቀነቀነላቸው ተስፋዎች መሬት ላይ ሳይወርዱ ቀሩ፡፡ በለውጡ መንግስት እንደሚተገበሩ ቃል የተገባላቸውና በህዝቡ ዘንድም ተስፋ የተጣለባቸው ጉዳዮች የህዝቦች ሰላምና ደህንነት መጠበቅ፣ የነፃነትና ዲሞክራሲ መስፈን፣ ኢትዮጵያዊነትና አብሮነት ተጠብቆ መቀጠል የሚሉት ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

ነገር ግን በለውጡ መንግስት ደስተኛ ባልሆኑ የተወሰኑ ቡድኖች፣ ለውጡ በመደመር ሀሳብ አግበስብሶ በደመራቸው ቡድኖችና ግለሰቦች የተነሳ በድጋሚ የንፁሀን ዜጎች ህይወትና ንብረት መጥፋት ጀመረ፡፡ የዘረኝነት እሳቱ ካለፈው ብሶ ቀጠለ፡፡ ሰዎች በየአካባቢው በዘራቸው፣ በሀይማኖታቸው በአጠቃላይ በማንነታቸው ተጨፈጨፉ፡፡ እነዚህ ተግባራት መፈፀም የጀመሩት ከ2010 ዓ.ም የመጨረሻ ወራት ጀምሮ ቢሆንም መልካቸውን እየቀያየሩ አሰቃቂ ግፎች የቀጠሉት ግን ከ2011 ዓ.ም አንስቶ ነው፡፡

የ2011 ዓ.ም አዲስ አመት ገና ከመግባቱ በኦሮሚያ ክልል አዲስ አበባ ዙሪያ አሸዋ ሜዳ፣ ከታ፣ ቡራዩ በተፈፀሙ ብሄር ተኮር የተባሉ ጥቃቶች በርካቶች ሲሞቱ በርካቶችም መፈናቀላቸው ይታወሳል፡፡ (ታምራት ሀይሉ 2011፣5)፡፡ እነዚህ ጥቃቶች ለተከታታይ ቀናት የቀጠሉ እንጅ በቶሎ መፍትሄ የተበጀላቸው አልነበሩም፡፡ እነዚህንና በመስከረም ወር ብቻ የተፈፀሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ ጥቃቶቹ ሲፈፀሙ በውጭ አገር የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱና ተፈናቃይና የሟች ቤተሰቦችን ከጎበኙ በኋላ ባስተላለፉት መልዕክት "እንዲህ አይነት ድርጊት ቀጣይነት የለውም፤ የዚህ ድርጊት ፈፃሚዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ መንግስት ጠንካራ እርምጃ ይወስዳል፡፡" በማለት ሲገልፁ እንዲሁም ደግሞ በኦህዴድ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ባሰሙት ንግግር "መደመር እንደዚህ አይደለም፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ወላዋዮችን ይጠየፋል፡፡ ከጠላት ጋር ሆናችሁ ትግላችንን ወደኋላ ለመመለስ ያሰባችሁ ካላችሁ ከጠላት ለይተን አናያችሁም፡፡ ኢትዮጵያን እንገነባለን፣ አፍሪካን እንገነባለን፣ ማንም ሀይል ደግሞ ከዚህ ሊያስቆመን አይችልም፡፡" (ታምራት ሀይሉ 2011፣6)፡፡ በማለት ጠንከር ያሉ ንግግሮችን አሰምተው ነበር፡፡ ነገር ግን ጥቃቶቹ እየቀጠሉ መንግስት አስከብራለሁ ያለው ህግና ስርአትም የውሀ ሽታ እየሆነ ሄደ፡፡

በወቅቱ በተለይም በቀድሞ ህወሀት ኢህአዴግ መሪዎችና በአሁኑ ብልፅግና በዚያ ጊዜ ስሙ የለውጡ ኢህአዴግ አመራሮች መካከል የነበረው ውጥረት እየከረረ በመሄዱ አገሪቱ ውጥረት ውስጥ ገባች፡፡ እነዚህ ውጥረቶች ደግሞ የበርካታ ንፁሀን ዜጎች ህይወት ለመቀጠፉ ዋነኛ ምክንያቶች እንደሚሆኑ መገመት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የለውጡ መንግስት የመፍትሄ አካል

ከመሆን ይልቅ በየአካባቢው የሚሞቱ ዜጎችን አስመልክቶ ያወጣ የነበረው መግለጫ ከአሁን በኋላ የህግ ጥሰትና የስርአት አልበኝነት ባህሪ ያላቸው ድርጊቶችን መንግስት አይታገስም፤ ይህንን የሚፈፅሙ ቡድኖችን በሆደ ሰፊነት እስካሁን ታግሰናል ከዚህ በኋላ ትዕግስት አይኖረንም ከማለት የዘለለ የህዝቡን እምባ በዘላቂነት የሚያብስ አልነበረም፡፡

በወቅቱ ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎችና በሌሎችም ጭምር የተፈፀሙትን ጥቃቶች አስመልክቶ በጊዜው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት የነበሩት አቶ ለማ መገርሳ በጥቃቶቹ ጥልቅ ሀዘን እንደተሰማቸው በመግለፅ የክልሉ መንግስት ተፈናቃዮችን ወደ ቀያቸው ለመመለስና መልሶ ለማቋቋም ሙሉ ሀላፊነት ይወስዳል ሲሉ ተደምጠው ነበር፡፡ እንዲሁም በወቅቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የነበሩት ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል "ከአሁን በኋላ የህግ ጥሰትና የስርአት አልበኝነት ባህሪ ያላቸው ድርጊቶችን መንግስት አይታገስም፡፡…ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ተጎጅዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ መቀጠል ባለበት ሁኔታ ላይ እራሱን የቻለ ኮሚቴ ተዋቅሮ ጉዳዩን በፍጥነት ለመቅረፍና መልሶ ለማቋቋም እየተሰራ ነው፡፡" (ታምራት ሀይሉ 2011፤6)፡፡ የሚል ንግግር ማሰማታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ይሁንና ጥቃቶቹ እየቀጠሉ እንደነዚህ አይነት ንግግሮችና መግለጫዎችም ተደጋግመው እየተደመጡ የመንግስት ተግባር መግለጫ ማውጣት ብቻ እስኪመስለው ድረስ ህዝቡን ለተስፋ መቁረጥ ዳረጉት፡፡

ከዚህ የተነሳ ዘፋኞችም ያንን ተስፋና ድጋፍ ባስተጋቡበት ድምፅ ተስፋ መቁረጣቸውንና የህዝቡንም መከፋት መልሰው ማቀንቀን ጀመሩ፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ታዲያ የለውጡን መምጣት አስመልክቶ ለውጡን አሞካሽተው የዘፈኑት አዲስ ሙላት፣ አቡሽ ዘለቀና ጌትሽ ማሞ ይገኙበታል፡፡ ዘፋኞቹ የማህበረሰቡን ስሜት ተከትለው ለመዝፈናቸው ከለውጡ የተጠበቀው ተስፋ ባለመገኘቱ የዘፈኗቸው ዘፈኖች ማሳያ ናቸው፡፡ እነዚህ የዘፋኞቹ ስራዎችም የአዲስ ሙላት ‹‹አገሬን ቁጥር ሁለት››፣ የአቡሽ ዘለቀ ‹‹ታመናል››፣ የጌትሽ ማሞ ‹‹ተቀበል ቁጥር አምስት (ሳቢው)›› እና ‹‹ዙፋኑ ነው መሰል›› የተሰኙት ዘፈኖች ናቸው፡፡ በእነዚህ ዘፈኖች ውስጥ የተካተቱት ግጥሞች በተለያየ መንገድ ከላይ የተጠቀሱትን ፖለቲካዊ ሁነቶች የሚዳስሱ ናቸው፡፡ በዘፈኖቹ የተካተቱትን መልዕክቶች አንድምታ ከመፈከራችን በፊት በመጀመሪያ የጋራ ጭብጣቸውን ጠቅለል አድርገን ለማየት እንሞክር፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ‹‹አገሬን ቁጥር ሁለት››፣ ‹‹ታመናል››፣ ‹‹ተቀበል ቁጥር አምስት (ሳቢው)›› እና ‹‹ዙፋኑ ነው መሰል›› የተሰኙ አራት ዘፈኖች የጋራ ጭብጥ በለውጡ ተስፋ መቁረጥን፣ ትዝብትንና ምክርን፣ እንዲሁም ያልተመለሰ ጥያቄን መግለፅ ነው፡፡ አዲስ ‹‹አገሬን ቁጥር

ሁለት›› በተሰኘ ዘፈኑ በለውጡ ተስፋ መቁረጡን፣ ትዝብቱንና ያልተመለሰ ጥያቄውን እንዲህ ሲል ያስደምጣል፡፡

‹‹ቃኘሁ ጠረጠርኩት የፈጣሪን መምጫ

ሲበለት እያየሁ ሀገር እንደ ቅርጫ››

በማለት ከዚህ ዘፈኑ በፊት በለውጡ ሰሞን ባወጣው ‹‹አገሬን›› የተሰኘ ዘፈኑ ተስፋ ያደረገበት የዘረኝነትና የመከፋፈል አባዜ ከበፊቱ የበለጠ ከፍቶ ማየቱን ይገልፃል፡፡ እርስ በእርስ የመከፋፈሉን ከፍተኛነት ሲገልፅም በመፅሃፍ የጌታ ምፅአት ሲደርስ አንዱ በአንዱ ላይ ይነሳል ተብሎ ከተፃፈው ጋር በማገናኘት ነው፡፡ በለውጡ ሰሞን ባለስልጣናት ይናገሩ የነበሩትን መልካም ነገሮች በማስታወስም፡-

‹‹አጀብ አዝመራየን ምን ጳጳስ ጎበኘው

እንዴት ያለ ፀበል ምን እምነት አገኘው

ደምቆ ተንዠርጎ ተበላ ስመኘው››

በማለት ያንን የተመኘውንና ተስፋ ያደረገበትን ሁሉ እንዳጣና ይልቁንም ያ የተስፋ አዝመራውን እንደተመኘው ፍሬውን ሳይበላ መቅረቱን ይገልፃል፡፡ በዚህም በወቅቱ ማህበረሰቡን ለድጋፍ ያነሳሳውንና ተስፋ የሰነቀበትን የለውጥ ሰሞኑን የአንድነት፣ የፍትህ፣ የሰላም፣ የፍቅርና የይቅርታ ወዘተ.  ንግግር በተግባር ለማየት ያልታደለውን ህዝብ ስሜት ገልፆበታል፡፡ አክሎም በለውጡ ሰሞን ባለስልጣናቱ ቃል የገቧቸውን ጉዳዮች ተግባር ላይ አለማዋላቸውን ሲያስብና ትዝብቱን ሲገልፅ፡-

‹‹ቃላባይ ወንዝ ነው ሲከዳን የኖረ

ዛሬ በጋ መቶ አባይ ተሸበረ››

በማለት ነው፡፡ በዚህም ውሸታሞችን ጊዜ እንዳጋለጣቸው ያሳያል፡፡ ዘፋኙ ከትዝብቱ ባሻገር ግራ የተጋባበትንና ያልተመለሰ ጥያቄውንም፡-

‹‹እንዴት ነሽ ልበልሽ እንደምን ከርመሻል

አንቺ ምስኪን ሀገር ኧረ እንዴት ይዞሻል?

እስከዛሬ ድረስ ስትበይ ኖረሻል

የአባቶችን ፀሎት አምላክ ሰምቶልሻል

ጨለማው ተገፎ ዛሬስ ነግቶልሻል?››

ብሎ ሲገልፅ የአገሩን ሰላም መክረምና የእናቶችም ሆነ የአባቶች ፀሎት ተሰምቶ ጨለማው ተገፎ መንጋቱን ከጠየቀ በኋላ በአገሩ ጉዳይ ማንን ማመንና ማንን መጠየቅ እንዳለበት ግራ በመጋባት፡-

‹‹ጠበቃሽ ማን ይሆን?

እማኝሽ ማን ይሆን?

ዋስሽስ ማን ይሆን?

እማኝሽ ማን ይሆን?

የነበረሽ ሁሉ እንዳልነበር ሲሆን››

በማለት በርካታ ያልተመለሱ ጥያቄዎቹን ያከታትላል፡፡ ከእነዚህ ስንኞች እንደምንረዳው ዘፋኙ የአገሩን ጠበቃና ዋስ ሲጠይቅ በሌላ መልኩም ባለስልጣናቱ ለተናገሩት ነገር ግን በተግባር ላልታየውና ህዝቡን ተስፋ ላስቆረጠው ጉዳይ ጠበቃቸውና ዋሳቸው ምንይል ይሆን የነበራቸው ንግግር ከተግባር ሲለይና በሌላ ሲተካ የሚል መልስ የሌለው ጥያቄ ይጠይቃል፡፡ እነዚህ ከወቅቱ ባለስልጣናት አፍ የማይጠፉ ንግግሮች በተቃራኒው ሲሆኑ ለምሳሌ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተናገሯቸው ዋና ዋና ነገሮች ውስጥ ያለን ምርጫ አንድ መሆን፤ መደመር ብቻ ነው፣ ቅድሚያ የምንሰጠው ለዜጎቻችን ክብር ነው፣ ከእንግዲህ ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚደበቅ ነገር አይኖርም (ሙሀባው ገድፍ 2011፣15 እና ታምራት ሀይሉ 2010፣5) የሚሉትን ማንሳት ይቻላል፡፡

ነገር ግን የአንድነቱ ሀሳብ ከተግባር እርቆ ብዙዎች ሲከፋፈሉ፤ የመደመሩ ሀሳብም ብዙዎችን እስከወዲያኛው ሲቀንስ፣ የዜግነት ክብሩ ቀርቶ ሰዎች በየአካባቢው እንደዜጋ ሳይቆጠሩ በማንነት ሲገደሉ፣ እንዴት እልቂቱን ማስቆም አልቻለም፣ ተጠያቂውስ ማነው?፣ ለምንስ ለህግ

አይቀርብም? ወዘተ. ለሚሉ የህዝብ ጥያቄዎች ግልፅ የሆነ ምላሽ መስጠት አለመቻሉ ዘፋኙ ግራ ተጋብቶ "የነበረሽ ሁሉ እንዳልነበር ሲሆን" ጠበቃሽና ዋስሽ ማን ይሆን ለማለት ያበቁት ጥቂቶቹ ምክንያቶች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

ሌላኛው ይህን ሀሳብ የሚጋራው ዘፋኝ አቡሽ ደግሞ ተስፋ መቁረጡን፣ ትዝብቱንና ምክሩን፣ እንዲሁም ያልተመለሰ ጥያቄውን በሚከተለው መልኩ ይገልፃል፡፡ ዘፋኙ ተስፋ ባደረገበት የለውጥ መንግስት ተስፋ መቁረጡን ‹‹ታመናል›› ከሚለው የዘፈኑ ርዕስ በመጀመርና፡-

‹‹*ታመናል ታመናል*

*ታመናል* በጣሙን››

በማለት ካለፈው ስርአት የባሰ ሁኔታ ላይ መሆናችንን ሲገልፅ ከዚህ ቀደም በተመለከትነው ‹‹*አነቃን*›› የተሰኘ ዘፈኑ ላይ በተስፋ ለመሪው ካሞገሰው ሙገሳ በተቃራኒ በመቆምም ስለፍቅር፣ ስለይቅርታ፣ ስለጦርነት አስከፊነትና ስለ ዘረኝነት በሰበካችሁ ማግስት ያንኑ አትድገሙት የሚል መልዕክትን እንደሚከተለው ያስተላልፋል፡፡

‹‹የማን ዘር ነው ከእሳት ከመብረቅ የተሰራ

የማን ዘር ነው ከጭድ ከሰበዝ የተሰራ?

አንዱን እያሳነስክ አንዱን አታግዝፈው

ሆዱ አምላኩ አትሁን ፍቅር ስበክ አንተ ሰው››

በለውጡ ላይ የነበረው ተስፋ መሟጠጡንና ለትዝብት መዳረጉንም ከምክር ጋር እንዲህ በሚል ሲገልፅ፡-

‹‹ሀያ ሰላሳ አመት ፊደል ቆጥረን አውቀን

የተሻለ ሀሳብ እንዴት ማምጣት አቃተን

ዛሬም የዘር ሀረግ ገመድ የሚጠልፈን?››

በእነዚህ ስንኞች ለሀያ እና ሰላሳ አመት የመጣንበት መንገድ እንዴት እንዳላስተማረንና ወደነበርንበት አዙሪት ምን እንደመለሰን በትዝብት ተገልጿል፡፡ ስለግጭቱ መብዛትና ስለዘረኝነቱ መባባስ የታዘበውንም፡-

‹‹ምክንያት እየፈለግን ሰበብ እየፈጠርን

በትንሽ ትልቁ ጦር እየተማዘዝን

አይደለም እሚበጀን አይደለም እሚተርፈን

በቀን ሶስቴ እንኳን መብላት እያቃተን››

በማለት ምክርም ጭምር ይለግሳል፡፡ በሌላ መልኩ ግራ መጋባቱንና ያልተመለሰ ጥያቄውንም፡-

‹‹ሁሉም የየራሱን ገንብቶ ካጠረ

ሁሉም የየራሱን ዘር ከመለመለ

የአብሮነትን ካባ ማን ሊያለብሰን መልሶ

ለሩብ ክፍለ ዘመን የበረደን መች አንሶ››

ተስፋ በጣልንበትና ስለመደመር፣ ስለእኩልነት፣ ስለኢትዮጵያዊነት በሰበክነው ልክ ሳይሆን በተግባር ሲታይ ከበፊቱ ባልተሻለ ሁኔታ የየራሳችን ዘር ከቆጠርን እንደገና የአብሮነቱን ካባ ማን ያለብሰን ይሆን? የሚል ጥያቄ ሲጠይቅ ግራ በተጋባ ቅላፄ ነው፡፡ በዘፈኑ ይህን መግለፅ ያስፈለገውም ዘፋኙ ከዚህ ቀደም "አነቃን" በሚል ርዕስ የዘፈነለትና በለውጡ ሰሞን የነበረው ተስፋ የተደረገበት ነገር በተለያየ ምክንያት እየተሸረሸረ የመጣበት ጊዜና በየቦታው ልዩነት እየተሰበከ የነበረበት ወቅት በመሆኑ ነው፡፡

ቀጥሎ የምናያቸው የጌትሽ ማሞ ‹‹ተቀበል አምስት (ሳቢው)›› እና ‹‹ዙፋኑ ነው መሰል›› የተሰኙ ሁለት ዘፈኖችም ከላይኞቹ የሚመሳሰል ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ጌትሽ በተቀበል አምስት (ሳቢው) ዘፈኑ ተስፋ መቁረጡን፣ ትዝብቱንና ምክሩን እንዲሁም ያልተመለሰ ጥያቄውን እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡ ዘፋኙ ከዚህ ቀደም የለውጡ ሰሞን ባወጣው ዘፈኑ ተስፋ ያደረጋቸው ነገሮች ባለመሳካታቸው ለምሳሌ በ‹‹ተቀበል አራት›› ለውጡንና መሪዎቹን ባወደሰበት ዘፈኑ፡-

‹‹እንግዲህ ካደለን የምህረቱን አመት

እንግዲህ ከታደልን የምህረቱን አመት

ተዋዶ መኖሩን በይ እንወቅበት›› ባለ ማግስት የባለስልጣናቱን ለህዝብ ግልፅ ያልነበረ ሽኩቻና ለውጡን ለማምጣት ቀዳሚ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆኑትን የአቶ ለማ መገርሳን (በወቅቱ የመከላከያ ሚኒስቴር የነበሩ) ከሚዲያ መጥፋት ቀጥሎም ከስልጣን መውረድና ተስማምቶ መቀጠል አለመቻል ሲታዘብ በ‹‹ተቀበል አምስት›› ዘፈኑ፡-

‹‹አብረን ፀሎት ይዘን ወደ አምላካችን

በዛ በመከራ ተጨንቃ ነፍሳችን

ቢፈርስ እያረኮ የክፋቱ ግንብ

ተለያይቶ አደረ የኔም ያንችም ልብ››

በማለት ተዋዶ የመኖር ተስፋውን እንደተቀማ ይገልፃል፡፡ ይህ ሁኔታ በወቅቱ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ሲዘገብና ሲዘዋወር እንደነበረው ማህበረሰቡንም ብዙ ጥያቄ እንዲጠይቅና ግራ እንዲጋባ ያደረገ ነበር፡፡ ሁኔታውን አስመልክቶ ፕሮፌሰር መስፍን (2013፣55) "…ዶ.ር ዓቢይ ወደ ስልጣን ሲመጣ አብሮት በጎኑ ቆሞ የነበረው ለማ መገርሳ ዛሬ የት ነው? የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳወረደው አልሰማሁም…" በማለት የወቅቱን ፖለቲካና ባለስልጣናቱ ተስማምተው መቀጠል አለመቻላቸውን እንዲሁም እንደቀደመው ጊዜ ሹም ሽር የሚያደርጉት ህዝብ ሳያውቅና እነሱ በፈለጉ ጊዜ እንደሆነ የታዘቡትን ወቅታዊ ጉዳይ ይገልፃሉ፡፡

አክሎም በለውጡ የኑሮውና የሰላሙ ጉዳይ ይሻሻላል የሚል ተስፋ የነበረ ቢሆንም በተግባር የታየው ሌላ እንደሆነ ሲገልፅ፡-

‹‹እኔ ትሻል ብዬ ስም ባወጣልሽ

ሰማሁ ትብስ ብለው ሰዎች ሲጠሩሽ

ኧረ ተይ አይሆንም ባንችም ከደገመኝ

እናቴም ልጅ የላት እኔም ወንድም የለኝ›› በሚል ነው፡፡

በዚህም የማህበረሰቡን ስሜት በመጋራት የወቅቱ ፖለቲካ ከቀደመው የባሰ ሁኔታ ላይ መሆኑን ተስፋ በቆረጠና ሽሙጥ ባጀበው ስሜት ይገልፃል፡፡ በዘፈኑ ለመግለፅ እንደተሞከረው ማህበረሰቡ ለውጡን በሁለት ጎራ ተመልክቶት እንደነበር ነው፡፡ በአንድ በኩል ለውጥ የለም ድሮም አሁንም እራሱ ኢህአዴግ ነው የሰው ለውጥ እንጅ ግልፅ የሆነ የስርአት ለውጥ አልተደረገም የሚል ነው፡፡ ይህን ሀሳብ የሚያነሱ ሰዎች የዚህን ማሳያ ሲገልፁ በሞት ከስልጣን የወረዱትን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ተክተው ስልጣን ላይ የወጡትን ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ የተሻለ የህዝብ አስተዳደር ያመጣሉ የሚል እሳቤ በህዝቡ ዘንድ የነበረ ቢሆንም ሚኒስትሩ ስልጣን ከተረከቡ በኂላ በነበራቸው ንግግር በአንድ ወቅት "እኔ የማስቀጥለው የመለስን ሌጋሲ ነው፡፡" (ታምራት ሀይሉ 2010፣5) ማለታቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ስለሆነም አሁንም በስርአት ለውጥ እንጅ በግለሰብ ለውጥ የሚለወጥ ነገር የለም ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ማሳያዎችን በማንሳት ለውጥ እንዳለና ካለፈው የተሻለ የህዝብ አስተዳደርና መሪ መኖሩን ይሞግታሉ፡፡ ለዚህ ማሳያዎችን ሲያነሱም በፖለቲካ አመለካከታቸው የታሰሩ እስረኞች መፈታታቸውን፣ ከኤርትራ መንግስት ጋር የነበረው አለመግባባት መቋጫ ማግኘቱን፣ ኢትዮጵያዊነት እንደአዲስ መሰበኩን፣ በምርጫ ቦርድ ላይ የተደረገውን ማሻሻያ፣ የፀረ ሽብርና የሲቪል ማህበራት ህጎችን ማሻሻያ ወዘተ. ባጠቃላይ በ2010 ዓ.ም በሰሞነ መጋቢት 24 የነበሩትን በጎ በጎ ተግባራት በማንሳት አንዳንድ ችግሮችና ጥፋቶች ቢኖሩም መንግስት የዲሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት ሆደ-ሰፊ በመሆኑ የተከሰቱ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ የተነሳም ለውጥ መምጣቱን ለመግለፅ ብልፅግና ራሱን ብልፅግና ብሎ አልሰየመም ነበርና ለውጥ መጥቷል የሚሉ አካላት የአብይ ኢህአዴግ እና የመለስ ኢህአዴግ በማለት ለውጡን ስም አውጥተውለት እንደነበር አንዳንድ ፅሁፎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሙሃባው ገድፍ (2011፣ 55) ህወሀት ኢህአዴግ የምሁራንን እና የአገር ሽማግሌዎችን ምክረ ሀሳብ ቢቀበል ኖሮ ስልጣን ላይ የመቆየት እድል እንደነበረው ባሳዩበት ሀተታ የለውጡን ኢህአዴግ ከነባሩ ለመለየት የመለስ እና የአብይ ኢህአዴግ በማለት የገለፁበትን መንገድ ማንሳት ይቻላል፡፡

ይህንንም ዘፋኙ በዘፈኑ ሲገልፀው እኔ ትሻል ብዬ ሌላ ስም አወጣሁልሽ ሌሎች ደግሞ አትሻልም ትብሳለች ሲሉሽ ሰማሁ ትሻል ያልኩት ስህተት ከሆነ እናቴም ልጅ የሌላት እኔም ወንድም የሌለኝ ያህል ተስፋ አጣለሁ ይላል፡፡ በዚህም ከፍተኛ ቁጥር የነበረውን የለውጡን ደጋፊ ስሜት ገልፆበታል፡፡

በተጨማሪም ከለውጡ የጠበቀውን ባለማግኘቱ ለትዝብት መዳረጉን፡-

‹‹ላንች የቀለለሽ ለኔ ከባድ ነው ከባድ ነው

ይሄ ነው እንግዲህ እወቂው

ፍቅር ያለቦታው ቢውል ከአፍሽ ከአፍሽ

ከበደኝ ልኖር አብሬሽ

ሳቢው ሳቢው ኧረ ሳቢው

ሳቢው ሳቢው እስኪ ሳቢው

ሳቢው ሳቢው ኧረ ሳቢው

ፍቅርን ሳቢው ወደ ልብሽ ሳቢው››

በማለት ከምክር ጋር ይገልፃል፡፡ በዚህም ባለስልጣናቱ ከልባቸው ሳይውል ከአፋቸው ብቻ የሚደመጥ የፍቅር ቃል ዘፋኙን ለትዝብት እደዳረገው በለውጡ ሰሞን ለውጡን እንደደገፈ ሁሉ ይህንን ልባዊ ያልሆነ ንግግር ተቀብሎ አብሮ ለመቀጠል እንደተቸገረ ሲገልፅ በወቅቱ ለለውጡ ጀርባቸውን ያዞሩትን ግለሰቦችና ቡድኖች ያስታውሰናል፡፡ በወቅቱ በዋናነት ለውጡን መቀበልና አብሮ መቀጠል ካቃተው ህወሀት ባሻገር የተለያዩ የለውጡ ደጋፊ የነበሩ ግለሰቦች በተለያየ ምክንያት ለውጡን መደገፍና አብሮ መቀጠል ያቆሙበት ጊዜ ነበር፡፡ የአንዳንዶቹ ምክንያት ደግሞ መሬት ያልወረደው ንግግር ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ይህ ስሜትም በዘፈኑ ስንኞች በሚገባ ተገልጿል፡፡ ቀጥሎም በየጊዜው የሚደረጉ አሳዛኝ ነገሮች ለምን እንዳላቆሙ ያልተመለሰለትን ጥያቄና ግራ የተጋባበትን ጉዳይ፡-

‹‹አሜን የአሜን ልጅ አሜን የወለደው

የዘራው ይፀድቃል ያድጋል የወለደው

አሜን ብዬ ነበር እባክህ እርዳኝ ጓዴ

የአባቶች ምርቃት እርግማን ነው እንዴ?››

በማለት በለውጡ ወቅት በነበረው የሰዎች ደስታና ምርቃት አሜን ብዬ ነበር ነገር ግን አሜን ማለቴ ለበጎ አልሆነልኝም ምርቃት እርግማን ይሆንን? የሚል ጥያቄ ይጠይቃል፡፡ በዚህም ለውጡ ከተደረገበት 2010 መጋቢት 24 ቀን ጀምሮ በጣት ለሚቆጠሩ ወራት የቆየውና የተሰበከው የዜጎች ነፃነትና ዲሞክራሲ፣ ይቅርታና እርቅ፣ አንድነትና መደመር እየተኮላሸ በለውጡና ለውጡን ባልፈለጉ የቀድሞ የኢህአዴግ አመራሮች በተለይም በህወሀት በኩል የነበረው ፍጥጫ እየከረረ እዚህም እዚያም የንፁሀን ዜጎች ሞትና ንብረት መውደም ቀጠለ፡፡ ሚች እና ተፈናቃይ እየበዛ ገዳይ እና አፈናቃይ ደብዛው እየጠፋ በርካታ ቀናትና ወራት ተቆጠሩ፡፡ በተለይም ከ2010 ዓ.ም መገባደጃ አንስቶ መልኩን እየቀያየረ ለአገር ትልቅ ባለውለታ ከሆኑ ግለሰቦች ጀምሮ የሌሎች በርካታ ሰዎችን ህይወት የቀጠፈውና ከ2011 ዓ.ም በኋላ ደግሞ እየተባባሰ የሄደው ፖለቲካዊ ውጥረት የማይዘነጋ ነው፡፡ በዘፈኑ ለመግለፅ የተሞከረውም ይህንኑ ሀሳብ ነው፡፡

በዚህ የለውጥ ወቅት በነበረው የማህበረሰቡ ደስታና የአባቶች ምርቃት አለመሳካትና ወደ እርግማን መቀየር ግራ መጋባቱን ከገለፀ በኋላ ቀጥሎ ደግሞ፡-

‹‹ቆመን ባደባባይ ሲሰማ ድምፃችን

ተዋህዶ እንዳልኖረ አንድ ላይ ደማችን

እንዳልመሰከርን ደርሰን ቀኑ ላይ

አይዘልቁም እንዳሉት ላንዘልቅ ነው ወይ?››

በማለት በለውጡ ማግስት የኦህዴዱን (የቀድሞ የኢህአዴግ አባል ድርጅት) አቶ ለማ መገርሳን ጨምሮ ሌሎች ግለሰቦችንና ቡድኖችን ከለውጡ ጋር መቀጠል አለመቻልና እንዲሁም በለውጡ ሰሞን የለውጡ መንግስት ጥሪ አቅርቦላቸው አገር ቤት የገቡ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ከለውጡ ጋር የነበራቸው አንድነት እየደበዘዘ መሄድና ተስማምቶ አለመቀጠልን በማንሳት አብረን መቆየት እንዴት አቃተን? ሲል ይጠይቃል፡፡

በሌላኛው የጌትሽ ማሞ ‹‹ዙፋኑ ነው መሰል›› ዘፈን ውስጥ የምናገኛቸው ጭብጦችም ተስፋ መቁረጥ፣ ትዝብትና ምክር፣ ያልተመለሰ ጥያቄ ናቸው፡፡ ዘፋኙ ትዝብቱንና ምክሩን በሚከተሉት ስንኞች ሲገልፅ፡-

‹‹ትላንትም ትልቅ ዛሬም ትልቅ ነች

ኢትዮጵያ እኮ ነች

አዲስ አይደለም ለሷ መከራ

ያልፋል አትፍራ››

በማለት ኢትዮጵያ ሁሌም ትልቅ እንደሆነች ማንም ቢመጣና ቢሄድ ክብሯን ሊያሳጣት እንደማይችል ቢሆንም ግን በታሪኳ ብዙ ጊዜ ተፈትና እንዳልወደቀች በመምከርም ጭምር ይገልፃል፡፡ ቀጥሎም፡-

‹‹ታገስ ያገሬ ሰው መታገስ ይሻላል

ጨለማን ያለፈ ብርሀንን ያያል››

በማለት ትዕግስት ከተደረገ በጨለማ የተመሰለውን ፖለቲካ አልፎ የተሻለውን ማምጣት እንደሚቻል ይመክራል፡፡ ተስፋ በተቀረጠበት ተስፋ መሰነቁ ከትልቅ ጨለማ በኋላ ታላቅ ብርሀን አለ እንደሚባለው ጨለማን ያለፈ ብርሀንን ያያል ማለቱ ህዝብ ከታላቅ ምሬት በኋላ የሚያደርገውን የበቃኝ ትግል በመረዳትና የቅርብ ጊዜ ትውስታ የሆነውን የኢህአዴግ ውድቀት ለማስታወስ እንደሆነ ከግጥሙ መረዳት ይቻላል፡፡ አያይዞም መልስ ያጣለትን ጥያቄውን፡-

‹‹ዙፋኑ ነው መሰል ያለበት አባዜ

እንዳይሆን ያረገው ሁሉም ባለጊዜ››

በማለት ችግሩ ምን አልባት ከዙፋኑ ይሆን ወይ? በማለት ግምቱን ይጠይቃል፡፡ ሁሉም ወደ ዙፋኑ ሲወጣ ቃል ይገባል ሲቀይ ቃሉ በተግባር አይገለፅም ይባስ ብሎ ዜጎች እኩልነት ተሰምቷቸው አብረው እንዲኖሩና በፍቅር እንዲተዳደሩ ከማድረግ ይልቅ የበታችነትና የበላይነት ይሰበካል ይላል፡፡ ይህ ሁኔታ በለውጡ መንግስት መደገሙ ደግሞ በለውጡ ላይ ተስፋ እንዳስቆረጠው፡-

‹‹እውነት ከኛ እርቆ ጠፍቶ መነጋገር

ሳይኖር ለምስኪኑ ጠብ ያለለት ነገር

በጎጥ እያሰቡ በእንብላው መንፈስ

ዛሬም ሊቆምሩ በድሀ ልጅ ነፍስ

ቆርጠው ተነስተዋል ሚያጠፉን መስሏቸው

ገድለውን ሊያበዙን እንደልማዳቸው››

በማለት ይገልፃል፡፡ ከግጥሙ የምንረዳው ዛሬም ከመነጋገር ይልቅ መግደል እና ማስገደል እንደቀጠለና አሁንም ችግሩ እንዳልተፈታ ነው፡፡ ቀጥሎም በለውጡ ተስፋ መቁረጡንና ከለውጡ የጠበቀው ሁሉ ባይሳካ እንኳን የሰላሙ ጉዳይ ብቻ እንዲጠበቅ በሚገልፅና በሚያስጠነቅቅ ቅላፄ እንዲህ ሲል ይገልፃል፡-

‹‹ዛሬም አንሰስትም እነሆድ አምላኩ

ሰላም ስጡንና ያሻችሁን እንኩ

ዞሮ መግቢያየን ግን ኢትዮጵያን አትንኩ››

እነዚህ ስንኞች የሚገልፁት ዛሬም የተሻለ አዲስ ነገር እንደሌለ ነው፡፡ መከፋፈሉ እንደባሰና ተስፋ የተደረገበት የፍቅር ጉዞ እንዳልተሳካ ስለሆነም ይህንንም መንግስት መታገል እንደሚያስፈልግ በሚያነሳሳ ቅላፄ ሲያሳስብም፡-

‹‹በዘር በሀይማኖት ከፍሎ በጎሳ

ቆጥሮ ሊሸጠኝ ቆርጦ ሲነሳ

አባቴ ይሙት! እጋፈጣለሁ

ኢትዮጵያ ትቅደም ብዬ እሞታለሁ››

በማለት ለተቃውሞ በሚያነሳሳ ግጥምና ቅላፄ ነው፡፡ ይህንን ለማጠንከርና ሌሎችንም ወደፊት መጥተው እንዲታገሉ ለማድረግ፡-

‹‹ካልኩ ወደኋላ በአገሬ ጉዳይ

የጀግኖች አጥንት እሾህ ሆኖ ይውጋኝ

እኔም በእናቱ ጠርቼሀለሁ

ብትዘገይ እንኳን እቀየማለሁ››

እኔ ለአገሬ እስከሞት ድረስ ዋጋ ልከፍል ተዘጋጅቻለሁ፡፡ ይህን ባላደርግ የጀግኖች አጥንት እንደእሾህ ይሁንብኝ ግን አንተንም ለትግል ስጠራህ መቅረትህ አይደለም መዘግየትህ እንኳን ያስከፋኛል በማለት ሌላውንም የሚያነሳሳ መልዕክት በግጥሙ መጨረሻ ያስደምጣል፡፡

ባጠቃላይ የዚህ ወቅት ዘፈኖች ዳግም ቅሬታንና በለውጡ አለመርካትን የተመለከቱ ሲሆኑ የህዝብን ቅሬታም ያንፀባረቁ ናቸው፡፡ ከላይ ከቀረበው ትንታኔ ለመግለፅ እንደተሞከረው ወቅቱ ህዝብ ከለውጡ የጠበቃቸውንና የታገለላቸውን ጥያቄዎች በመነፈጉ ድጋፉን የቀነሰበት ነበር፡፡ መንግስትም ቃል የገባቸውን ንግግሮች ወደ ተግባር መቀየር ሲሳነው የታየበት ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳም በዚህ ወቅት በተዘፈኑ ዘፈኖች እነዚህ ጉዳዮች በስፋት ተስተውለውባቸዋል፡፡

## 4.1.3.2. የዘፈኖቹ አንድምታ ትንተና ከወቅቱ ፖለቲካዊ አውድ አንፃር

በለውጡ ብዙ ተስፋ ሰንቆ የነበረው በርካታው ህዝብ ከ2011-2013 ዓ.ም በነበሩት ጊዜያት በተለያየ ምክንያት የጠበቀውን ባለማግኘቱ ለዳግም ቅሬታ የተዳረገበት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የተከሰቱትን ፖለቲካዊ ሁነቶችና ማህበረሰቡን ለዳግም ቅሬታ የዳረጉትን ጉዳዮች የሚዳስሱ በርካታ ዘፈኖች ተዘፍነዋል፡፡ ለጥናቱ የተመረጡትን ስራዎች ቀጥለን ከወቅታዊ ፖለቲካዊ አውዳቸው አንፃር እንመልከት፡፡

በወቅቱ የነበረውን ፖለቲካ አስመልክቶ ከተዘፈኑት ውስጥ የአዲስ ሙላት ‹‹አገሬን ቁጥር ሁለት›› አንዱ ሲሆን በዘፈኑ ብዙ ቅሬታዎች የተነሱበት ነው፡፡ በዘፈኑ ከተካተቱ ግጥሞች ውስጥም፡-

‹‹እንዴት ነሽ ልበልሽ እንደምን ከርመሻል

የአባቶችን ፀሎት አምላክ ሰምቶልሻል

ጨለማው ተገፎ ዛሬ ነግቶልሻል

እንዴት ነሽ ልበልሽ እንደምን ከርመሻል

የእናቶችን ፀሎት አምላክ ሰምቶልሻል

ጨለማው ተገፎ ዛሬስ ነግቶልሻል?››

በሚሉት ስንኞች አንድም አገሬ የአባቶችና የእናቶች ፀሎት ተሰምቶ የነበረው ጨለማ ነግቶልሻል፤ ንጋትሽን ለነገም ቀጣይነት እንዲኖረው አድርጊ የሚል ነው። አንድም ደግሞ ወቅታዊ የነበረውን የህዝቡን ግራ መጋባት ሲገልፅ አገሩን እንዴት እንደከረመች ህዝቦቿ ተስፋ ያደረጉትና የታገሉለት አላማ ከግብ መድረሱን በመጠየቅ ነው። ይህንንም እውነት ትግሉ ፍሬ አፍርቶ ከነበርሽበት የእልቂት ዘመን እፎይ ብለሽ ይሆንን? በማለት ይገልፃል። የጥያቄው መነሻ ደግሞ በወቅቱ ከለውጡ ማግስት የተከሰቱት ፖለቲካዊ ውጥረቶችና ያላባሩ የህዝብ እልቂቶች ናቸው።

በተጨማሪም፡-

‹‹አጀብ አዝመራየን ምን ጳጳስ ጎበኘው

እንዴት ያለ ፀበል ምን እምነት አገኘው

ደምቆ ተንዥርጎ ተበላ ስመኘው››

በሚሉት ስንኞች የተላለፈው መልዕክት በአንድ በኩል በጥሩ ሁኔታ በአፈራ አዝመራ የተመሰለው የለውጡ ሰሞን ንግግር ነው። ማለትም እነዚያ መልካምና የህዝቡን ቀልብ የገዙ የሰሞን ተግባራትና ንግግሮች በምን ምክንያት ወደ ኋላ እንደተመለሱ የሚጠይቅ ነው። በዘፈኑ የተገለፀውን ሀሳብ ለመረዳት ከ2011-2013 ዓ.ም በነበሩት አመታት የተከሰቱ ሁነቶችን ብቻ ማጤን በቂ ነው።

እነዚህ ተስፋ ያደረገን ህዝብ መልሰው ተስፋ ያስቆረጡ የወቅቱ ሁነቶችም የዜጎች መሞት፣ መፈናቀል፣ በወጡበት መቅረት (በ2012 ህዳር ወር የታገቱ የደምቢዶሎ ተማሪዎችና ሌሎችም)፣ ለአንዱ የሚሰራው ግዴታና መብት ላንዱ አለመስራቱ ወዘተ. የለውጡ መንግስት እንከኖች በለውጡ ብዙ ተስፋ ለነበረው ህዝብ ተስፋው መቀማቱን የሚያሳዩ ናቸው። በዘፈኑ የተገለፀውም ይህንኑ ነው። አንድም ደግሞ ሀምሌ 19 ቀን 2010 ዓ.ም በገዛ መኪናቸው ውስጥ ስለተገደሉት ኢንጅነር ስመኘው የሚናገር ሲሆን ምን አገኛቸው በሚል አሳዛኝ የነበረውን የኢንጅነሩን ሞት ይጠይቃል። በወቅቱ ይህ ጥያቄ የበርካታ ህዝብ ጥያቄ የነበረ ነው።

አቡሽ ‹‹ታመናል›› በሚል ርዕስ በዘፈነው ዘፈን፡-

‹‹ሀያ ሰላሳ አመት ፊደል ቆጥረን አውቀን

የተሻለ ሀሳብ እንዴት ማምጣት አቃተን

ዛሬም የዘር ሀረግ ገመድ የሚጠልፈን››

ሲል አንድም መማር ማለት የባህሪ ለውጥ ማምጣት ነው እንደሚባለው በእድሜያችን በርካታ አመታትን በትምህርት አሳልፈን እያለ አስተሳሰባችን መቀየር አለመቻሉን የሚገልፅ ነው፡፡ አንድም ደግሞ ያሳለፍነው 27 አመት የዘር ፖለቲካ ነበር፤ ነገር ግን ያስከተለው እልቂት ከፍተኛ መሆኑ እየታወቀ አሁንም እነዚያ አመታት ሳያስተምሩን የዘር ፖለቲካ መንገዱን መርጠነዋል የሚል ነው፡፡ ለዚህ ማሳያውም በተለያዩ በዘራቸው በተቧደኑ ቡድኖችና በአገሪቱ መንግስት መካከል የነበረው ውጥረትና አንዳንዴም በራሱ በመንግስት ውስጥ ባሉ አመራሮች ሲነገር የሚሰማው አስደንጋጭ ንግግር ነው፡፡ እነዚህ ከአንዳንድ ባለስልጣናትና ልሂቃን ይሰሙ የነበሩ ኢ-ፍትሀዊነት የሚስተዋልባቸው ንግግሮች ደግሞ ህዝቡ በለውጡ ላይ የነበረው ተስፋ እንዲመነምን ያደረጉ ናቸው፡፡

ጌትሽ ማሞም ‹‹ዙፋኑ ነው መሰል›› በተሰኘ በለውጡ ወቅት የነበረውን ተስፋ የተቀማውን ህዝብ ስሜት በገለፀበት ዘፈኑ፡-

‹‹ዙፋኑ ነው መሰል ያለበት አባዜ

እንዳይሆን ያረገው ሁሉም ባለጊዜ››

ሲል አንድም ዙፋኑ ላይ የተቀመጠና ጊዜ የሰጠው ባለስልጣን ሁሉ ቃሉን በተግባር ሲፈፅም አይስተዋልም ማለቱ ነው፡፡ ይህም ምናልባት ዙፋኑን ላለመልቀቅና የስልጣን ጥማት ሳይሆን አይቀርም ሁሉንም ጊዜ ወደ ስልጣን ያመጣቸውን ባለጊዜዎች (መሪዎች) እንዳይሆኑ ወይም መልካም እንዳይሰሩ ያላስቻላቸው የሚል ነው፡፡

አንድም ደግሞ ዙፋኑ ላይ የሚቀመጠው መሪ ሁሉም ዜጎች ባለጊዜ እንዲሆኑ (የእኩልነት ስሜት እንዲሰማቸው) ማድረግ እንዳይችል ያደረገው ስልጣኑን እያሰበ ወደዘረኝነቱ መግባቱ ይሆንን የሚል ጥያቄ ነው፡፡ ስልጣንን ለማስጠበቅ ባይሆን ኖሮ ሁሉም ዜጋ ለእኔም እኩል የሚያስብልኝ መንግስትና አስተዳደር መጣልኝ ብሎ እኩልነት እንዲሰማው ይሆን ነበር የሚል አንድምታ አለው፡፡ ለዚህም የጊዜውን ወቅታዊ ሁነት ስንመለከተው የአንዳንድ አካባቢ ዜጎች

ለጥፋታቸው አፋጣኝ እርምጃ ሲወሰድባቸው የአንዳንድ አካባቢ ዜጎች ደግሞ ከተጠያቂነት ሲድኑ ይታይ የነበረበት አስተዛዛቢ ወቅት ነበር፡፡

ለምሳሌ ያህል በዋናነት የ2011 ዓ.ም የሰኔ 15ቱን ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው የተጠረጠሩትና በአፋጣኝ የተገደሉት አሳምነው ፅጌ ላይ፣ አገር ላይ ግፍና በደል ፈፅመዋል በሚል የሚጠረጠሩት የቀድሞ ደህንነት ጌታቸው አሰፋ ላይ፣ የእርስ በእርስ ጦርነት አስነስተዋል ሀይማኖትን ከሀይማኖት አጋጭተዋል በሚል የተጠረጠሩት ጀዋር መሀመድ ላይ፣ ወዘተ. እና በየአካባቢው ለሚሞተው እንዲሁም ለሚፈናቀለው ህዝብ የሚደረጉ ኢ-ፍትሀዊነቶች ከለውጡ መንግስት ያልተጠበቁ ነበሩ፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ቦታ ያለ ተፈናቃይና ሟች ዜጋ ነው፣ ሁሉም ቦታ ያለ ወንጀለኛም ወንጀለኛ ነው፤ ነገር ግን ለአንዱ ፍርድ ሰጥቶ አንዱን በይቅርታና የዲሞክራሲ ምህዳር ለማስፋት በሚል መተው በግልፅ በመንግስት ደረጃ የሚታይ ኢ-ፍትሀዊነት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ደግሞ በዘፈኑ እንደተገለፀው ስልጣንን ላለማጣት የሚደረግና ከስልጣን ፍቅር የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ በወቅቱ ለስልጣንም ይሁን ለሌላ ጉዳይ ይደረጉ የነበሩ በተለያየ መልኩ የሚገለፁ ኢ-ፍትሀዊነቶች ደግሞ ህዝቡ በመንግስት ላይ ተስፋ እንዲቆርጥና የየኔነት ስሜት እንዳይሰማው አድርገዋል፡፡

## 4.2. የዘፈኖቹ ማህበረ ፖለቲካዊ ፋይዳ

በክለሳ ድርሳናቱ ላይ እንደተገለፀው ዘፈን በርካታ ፋይዳዎች አሉት፡፡ ከእነዚህ ፋይዳዎቹ ውስጥ ደግሞ ለፖለቲካዊ አላማ በመዋል ህዝብ አንድን ፖለቲካዊ ስርአት እንዲደግፍና እንዲቃወም ማነሳሳት አንዱ ነው፡፡ ስለ አንድ ወቅታዊ ሁኔታ ግለሰቦች ወይም ማህበረሰቦች ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ አመለካከት ለሌሎች ለማጋራትም ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ እንዲሁም ደግሞ የመናገር ነፃነት በሌለበትና ህዝብ መተንፈሻ ባጣበት ሁኔታ ዘፈኖች ስለህዝብ ድምፅ ሆነው ይወጣሉ፡፡ ከዘፈን ፋይዳዎች ውስጥ ፖለቲካዊ ፋይዳውን የተመለከተውን ጥቂቱን አነሳን እንጅ ዘፈን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ጥበብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥበብ በአገራችን ከ2008-2013 ዓ.ም በነበሩ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ውጥረቶች ውስጥ የዘፈኖች ማህበረ ፖለቲካዊ ተግባር እንዴት ይታያል የሚለውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

በእነዚህ ጊዜያት የተዘፈኑና ለጥናቱ ተመርጠው ትንታኔ የተሰጠባቸው ዘፈኖች እንደ ፖለቲካዊ ሁነቱ ጭብጣቸው የተለያየ ነበር፡፡ በመጀመሪያዎቹና ለውጥ እንዲመጣ ህዝብ ከፍተኛ ተቃውሞና ትግል ባደረገባቸው ከ2008-2010 መጋቢት ወር ድረስ በነበሩት ጊዜያት የተዘፈኑ

ዘፈኖች የወቅቱን ፖለቲካዊ አውድ መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ በዋናነት የነበረውን የህዝብ የተቃውሞ ድምፅ አጉልተው ያሰሙ ናቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ የአንድነትንና የመተባበርን ጥቅም ለህዝብ የሰበኩም ነበሩ፡፡ በተጨማሪም በመንግስት በኩል ይደረግ የነበረውን የሰብአዊ መብት ጥሰትና የሀይል እርምጃ በማስተጋባት ለመንግስት አካላት ማስጠንቀቂያ አዘል መልዕክቶች የተደመጡባቸውም ናቸው፡፡

ይህን መሰል ተግባር የተወጡ ዘፈኖች በርካታ ቢሆኑም ለጥናቱ እንደማሳያ የተወሰዱት ሶስቱ ዘፈኖች ማለትም የናትናኤል ‹‹አሁን ተነካሁ››፣ የይሁኔ ‹‹ሰከን በል››፣ የጌትሽ ‹‹ተቀበል ሁለት (እንክባበር)›› ሲሆኑ ዘፈኖቹ ከርዕሳቸው ጀምሮ የያዙት የግጥም መልዕክት ጠንከር ያለ ነው፡፡ የናትናኤል አሁን ተነካሁ ዘፈን ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በሁሉም አካባቢ ያለ የአገሬ ዜጋ ሲነካ እኔም እንደተነካሁ ይሰማኛል፣ ህመሙ እኔንም ያመኛል፤ ስለሆነም አብሬ እታገላለሁ የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡ በዚህም እናንተም እንደኔ እኛን አይመለከትም ሳትሉ ተጋግዘንና የሌላውን ህመም እኩል ታመን ነፃ እንውጣ፣ አፈናውን፣ ግድያውን፣ ባጠቃላይ የሰብአዊ መብት ጥሰቱን እንቃዎም በማለት የማነሳሳት ተግባር ተወጥቷል፡፡ ተቃውሞውን በዘፈኑ ስንኞች ሲገልፅም በወቅቱ መንግስት በዜጎች ላይ ያደርስ የነበረውን በደል ወንድሙን ገድሎ ጀግና የሚሆን የለም፤ ነገር ግን ወንድሙን ሚገድል ገዳይ ታዟል ይህን ገዳይ ደግሞ ተባብረን እንመክት፤ የሌላው ቤት ሲንኳኳ እያየን ዝም አንበል ወዘተ. በማለት ነው፡፡ በተጨማሪም በወቅቱ ይታይ ለነበረውና የፖለቲካው ቀውስ ለፈጠረው ዘረኝነትና ማህበራዊ ችግር አንድነትና ትብብር ወሳኝ እንደሆነም አጠንክሮ ይሰብካል፡፡

የይሁኔ ሰከን በል ዘፈንም በወቅቱ ቆም ብሎ ማሰብና እየሄደበት ያለው መንገድ ትክክል እንዳልሆነ መረዳት ያቃተውን መንግስትና ታዛዥ ወታደሩ በህዝብ ላይ ስለሚያደርጉት ሁሉ ሰከን ብለው እንዲያስቡ የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ ዘፈን ህዝቤን አትግደሉ፣ ድምፁን ስሙ፣ ጥያቄውን መልሱ የሚሉና ሌሎች የህዝብ ድምፆች ተደምጠውበታል፡፡ በወቅቱ በተለያዩ አካባቢዎች የነበረውን ዘረኝነትና መከፋፈል አስመልክቶም በዘፈኑ ዘረኝነት ከሞት የበለጠ እንደሚጎዳ ትምህርት ተሰቶበታል፡፡

በተመሳሳይ የጌትሽ ማሞ እንከባበር ዘፈንም ለተቃውሞና የህዝብን ድምፅ ለማሰማት ተግባር ሲውል ዘፈኑ እንከባበር ከሚለው ርዕሱ ጀምሮ የመንግስትን ደካማ ጎኖች ነቅሶ በማውጣትና ህፀፆቹን በሰም ለበስ ቅኔ በመንገር በደላችሁ በዝቷል፣ ተከባብረን እንኑር እና ሰዎችን እየገደሉ ስልጣንን ማስጠበቅ ከባድ ነው የሚሉ መልዕክቶችን ሲያስተላልፍ ባጠቃላይ መንግስትን

እንከባበር የሚል ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነው፡፡ በአጠቃላይ የዚህ ወቅት ዘፈኖች የህዝቡን ድምፅ ለማሰማት፣ ህዝቡን ለማነሳሳትና የሚደረገውን ጭቆና ለመቃዎም የተዘፈኑና የህዝቡ የተናጠል ትግል በመደጋገፍና በመናበብ እንዲሄድ የመምራት አንድምታ ያላቸው ናቸው፡፡ ይህንን በይዘቶቻቸው በጋራ ያቀነቀኑትን ይዘት ለተግባር ያበቁ መሆናቸውን ተከትሎ ከመጣው የለውጥ ብልጭታ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የምንመለከታቸው ዘፈኖች ከ2010 መጋቢት ወር እስከ 2011 ዓ.ም የነበሩትን ፖለቲካዊ ሁነቶች አስመልክተው የተዘፈኑትን ነው፡፡ በእነዚህ ወራት የተዘፈኑ ዘፈኖች የወቅቱን ማህበረ ፖለቲካዊ ድባብ የሚገልፁና በጊዜው የተደረገውን ለውጥ የሚያወድሱ ነበሩ፡፡ ዘፈኖቹ የወቅቱን ማህበራዊ ስሜት ከመግለፅ አንፃርም በርካታው ህዝብ ለውጡን በመደገፉ የህዝቡን የደስታ ስሜትም አካተው ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህዝቡ ከለውጡ ስለሚፈልገው ሰላም፣ ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነፃነት፣ አንድነት፣ ወዘተ. ገልፀዋል፡፡ እነዚህ በወቅቱ የነበረውን የህዝብ ደስታ በመግለፅና ለውጡን በማሞካሸት ከለውጡ ህዝብ የሰነቀውን ተስፋ አስመልክተው የተዘፈኑ ዘፈኖች የአዲስ ‹‹አገሬን››፣ የአቡሽ ‹‹አነቃን››፣ የጌትሽ ‹‹ተቀበል አራት›› ናቸው፡፡ ዘፈኖቹ በ2010 መጋቢት 24 ቀን መቋጫ ያገኘ ስለመሰለው የህዝብ ጥያቄና ስለተገኘው ለውጥ፤ እንዲሁም በለውጡ መሪዎች በዚያ ወቅት ይፈፀማሉ ተብለው ሊታሰቡ ስለማይችሉ አስደናቂ ተግባራትና ንግግሮች፣ ደስታውን በየሰልፉ ይገልፅ ስለነበረው ህዝብ ስሜት፣ ወዘተ. ብዙ የሚገልፁት ሀሳብ አላቸው፡፡ ባጠቃላይ የዚህ ወቅት ዘፈኖች የማወደስ፣ የመደገፍና የወደፊት ተስፋን የመግለፅ ተግባር የተወጡ ናቸው፡፡

እነዚህ ዘፈኖች ለለውጥ በተካሄደው ተቃውሞና ትግል መስዋዕትነት የከፈሉትን ደም ከንቱ አለመቅረት፣ ስቃይና እንግልት የደረሰባቸውን ለውጤት መብቃት፣ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው የታገሉትን ለድል መብቃት የሚያመሰግኑና የሚያበረታቱ ስለሆኑ፣ በጭቆናና አንባገነንነት ላይ ለሚደረጉ ትግሎች አርዐያ የመሆንና ተከታይ የማፍራት አንድምታ አላቸው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የምንመለከተው በለውጡ አለመርካትንና ቅሬታን በድጋሜ ያስተጋቡትን ከ2011-2013 ዓ.ም የተዘፈኑትንና የማህበረሰቡን ወቅታዊ ስሜት የገለፁትን በአዲስ ሙላት፣ በአቡሽ ዘለቀና በጌትሽ ማሞ የተዘፈኑ ዘፈኖችን ፋይዳ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ዘፈኖቹ የህዝብን ስሜት ለመግለፅ፣ በፖለቲካዊ ሂደቱ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለማሰማትና ለመተቸት ፋይዳ ውለዋል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት የተዘፈኑት ዘፈኖች የወቅቱን ፖለቲካዊ አውድ እና ማህበራዊ ስሜት በአንክሮ ያጤኑ እንደሆኑ ከግጥሞቹ እንረዳለን፡፡ ዘፈኖቹ የቀረቡበት ወቅት ከለውጡ

የተጠበቀው መልካም ነገር እየራቀና ያልተጠበቀው እዚህም እዚያም ይታይ የነበረ ግጭት የተከሰተበት በመሆኑ፤ ማህበረሰቡ በለውጡ ላይ ያሳደረው ተስፋ እየመነመነ የሄደበት ነበር፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በለውጡ ሰሞን ህዝቡ ተስፋ ያደረገባቸውና በለውጡ ወቅት በተዘፈኑ ዘፈኖችም የተቀነቀነላቸው ጉዳዮች ወደ ኋላ ተመልሰዋል የሚል እሳቤ ነው፡፡

ለዚህ ምክንያቱ በርካታ ቢሆንም በዋናነት ግን የመንግስት የቁርጠኝነትና ህግን የማስከበር እንዲሁም ፍትህን ለሁሉም ዜጋ እኩል ያለማስፈን ችግር ይጠቀሳል፡፡ በዚህ ክፍተት ምክንያት በጊዜው የሚፈፀሙ ወንጀሎች መልካቸውን እየቀያየሩና ውስብስብ እየሆኑ ካለፈው በባሰ ሁኔታ በርካታ የጭካኔ ተግባራት መፈፀም የዕለት ተዕለት ተግባር ሆነ፡፡ በእነዚህ ተግባራት ህይወቱን የሚያጣው ዜጋም ከመንግስት ግልፅ የሆነ ምላሽ ሲፈልግና ገዳዮች እንዲጠየቁ ሲማፀን ጊዜያት ተቆጠሩ፡፡ እነዚህን እያዩ የህዝብ ድምፅ አለመሆን የከበዳቸው ሶስቱም ለውጡን ደግፈውና አወድሰው የዘፈኑ ዘፋኞች መልሰው ቅሬታቸውንና የህዝቡን ድምፅ ‹‹ተቀበል አምስት (ሳቢው)፣ ዙፋኑ ነው መሰል፣ ታመናል፣ አገሬን ቁጥር ሁለት›› በተሰኙ ዘፈኖቻቸው አሰሙ፡፡

አዲስ በአገሬን ቁጥር ሁለት ዘፈኑ የወቅቱን የህዝብ ቅሬታ፤ አገሬ የነበረሽ ሁሉ እንዳልነበር ሆነ፣ የተገባልሽ ቃል ሳይተገበር ሲቀር ጠበቃና ዋስሽ ማን ይሆን፣ የዋሹሽ በጊዜ ሂደት ተጋለጡ ወዘተ. በማለት ቅሬታውን ገለፀ፡፡ አቡሽ ደግሞ በታመናል ዘፈኑ ዛሬም በዘረኝነት ገመድ መጠለፋችንንና የመጣው ለውጥ የአንድነትን ካባ አለበሰን ስንል ለውጡም ከከሸፈ ተስፋችን ምንድን ነው? ከተጓዝነው የዘረኝነት መንገድ መማር ለምን አቃተን? በማለት ቅሬታውን ይገልፃል፡፡ ጌትሽም ሳቢው እና ዙፋኑ ነው መሰል በተሰኙ ስራዎቹ ባለስልጣናቱን ንግግራችሁ በተግባር ይታይ፣ በመጣው ለውጥ ያገኘነውን አንድነት ሳናጣጥም መልሳችሁ ለያያችሁን፣ ከህዝብ ይልቅ ስልጣን በለጠባችሁ፣ ወዘተ. በማለት ሲተች ህዝብን ለዳግም ተቃውሞ በማነሳሳትም ጭምር፡-

‹‹ካልኩ ወደ ኋላ በአገሬ ጉዳይ

የጀግኖች አጥንት እሾህ ሆኖ ይውጋኝ

እኔም በእናቱ ጠርቼሀለሁ

ብትዘገይ እንኳን እቀየማለሁ›› በማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ለጥናቱ በተመረጡ ጊዜያት የተዘፈኑት የተመረጡ ዘፈኖች የወቅቱን ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ በዋናነት የትችት፣ የተቃውሞና የውዳሴ ተግባር ነበራቸው፡፡ ያወደሱት የ2010 ዓ.ም ለውጥን ሲሆን የተቃወሙትና የተቹትም ዘረኝነትን፣ ኢ-ፍትሀዊነትን፣ የሰብአዊ መብት ጥሰትን፣ ሙስናን፣ የመሪዎችን ገደብ የሌለው የስልጣን ፍቅር ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

ጥናቱ ከ2008-2013 ዓ.ም የተዘፈኑ የተመረጡ የአማርኛ ፖለቲካዊ ዘፈኖች አንድምታ የተተነተነበት ነው፡፡ በንዑስነት ደግሞ የዘፈኖቹ የጋራ ጭብጥ፣ የዘፈኖቹ አንድምታ፣ ዘፈኖቹ የወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነትና ማህበረሰባዊ ስሜት የገለፁበት መንገድ እና የነበራቸው ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ ተገልጿል፡፡ ትንተናው በአውዳዊ ንድፈ ሀሳብ (Contextual approach) እና በሀዲስ ታሪካዊ ንድፈ ሀሳብ (New historicism theory) መነሻነት ዘፈኖቹ ከተዘፈኑበት ማህበረ-ፖለቲካዊ አውድ አንፃር ተካሂዷል፡፡ የምርምሩን ዓላማ ለማሳካትም ከ2008-2013 ዓ.ም የተዘፈኑ አስር ዘፈኖች በአላማ ተኮር ናሙና ተመርጠው በሶስት ምድብ ማለትም ከ2008-2010 መጋቢት ወር፣ ከ2010 መጋቢት ወር እስከ 2011፣ እና ከ2011-2013 ዓ.ም ተመድበው ትንተናው ተካሂዷል፡፡

ምደባው የተካሄደውም የሶስቱም ጊዜያት ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ ስለሚለያይና ዘፈኖቹ የተዘፈኑበትን ጊዜም ማዕከል በማድረግ ነው፡፡ ለምርምሩ የተለያዩ የጥናት ዘዴዎች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን በሰነድ ፍተሻና በጥልቅ ማዳመጥ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተብራርተው በገለፃ መልኩ ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በገላጭ የምርምር አይነት የተካሄደ ሲሆን መረጃዎቹም በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዚህ መልክ የተካሄደው ጥናት የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ አስችሏል፡፡

በመጀመሪያው ምድብ ከ2008-2010 መጋቢት ወር ድረስ ከነበረው ፖለቲካዊ አውድ አንፃር የተዘፈኑ ዘፈኖች ዋና ትኩረታቸው የወቅቱን ማህበረ ፖለቲካዊ አውድ መሰረት አድርገው የአብዛኛውን ማህበረሰብ የተቃውሞ ድምፅ ማሰማት ነው፡፡ የጋራ ጭብጣቸውም ዘረኝነትና የፖለቲካ ትኩሳት ያመጣውን የእርስ በእርስ ግጭት አስከፊነት፣ የእኩልነትንና የመተባበርን አስፈላጊነት መግለፅና ለውጥ እንዲመጣ ማነሳሳት እንደሆነ ታይቷል፡፡ በዘፈኖቹ ከተካተቱ ግጥሞች መረዳት የተቻለውም ዘፈኖቹ የተዘፈኑት ለውጥን ፈልገውና ስርአቱ በህዝብ ላይ የሚያደርገውን ጭቆና ተቃውመው ሲሆን በተቃውሟቸው ውስጥ አንድም መንግስት ራሱን ፈትሾ ችግሮቹን እንዲያስተካክል፤ አንድም ደግሞ ችግሮቹ ካልተፈቱ ለተቃውሞ የተነሳው

ህዝብ ተቃውሞውን እንዳያቋርጥ የሚያነሳሱ ናቸው። የወቅቱ ዘፈኖች ፋይዳም የህዝብን ጭቆና መግለፅና ህዝብን በተደራጀ መንገድ ለተቃውሞ እንዲነሳሳ መጎትጎት ነው።

ከ2010 መጋቢት ወር እስከ 2011 ዓ.ም የተዘፈኑ ዘፈኖችም ወቅቱ ለውጥ የመጣበት በመሆኑ በዋናነት ትኩረታቸው ሙገሳና ህዝብ ከለውጡ የሚጠብቀውን ነገር በተስፋ የገለፁ ነበሩ። ዘፈኖቹ ከወቅቱ ሁነት አንፃር የተቀዱና በዋናነት የኢትዮጵያዊነትና የአንድነት ስሜትን የያዙ ግጥሞችን አካተዋል። ግጥሞቹ አንድም የኢትዮጵያዊነትንና የአንድነትን ሀሳብ ያንፀባረቀውን ለውጥ እና መሪዎቹን ሲያወድሱ አንድም ደግሞ የነበረውን አስተዳደር ከለውጡ ጋር በማነፃፀር የሚተቹ ናቸው። ፋይዳቸውም የለውጡን መሪዎችና ለውጡን ማወደስ፣ መደገፍና ለወደፊት የሚጠበቅበቀውን ተስፋ መግለፅ ነበር።

ከ2011-2013 ዓ.ም የተዘፈኑት ዘፈኖች ደግሞ በወቅቱ የነበረውን የህዝብ ቅሬታ የተመለከቱ ሲሆኑ የጋራ ጭብጣቸውም በለውጡ ተስፋ መቁረጥን፣ ትዝብትንና ያልተመለሰ ጥያቄን መግለፅ ነው። በዘፈኖቹ በወቅቱ ህዝብ ለዳግም ቅሬታ የተዳረገባቸው ኢ-ፍትሀዊነትና ዘረኝነት ተደምጠዋል። የዘፈኖቹ ፋይዳም ከወቅቱ ማህበረ ፖለቲካዊ ሁነት አንፃር የማህበረሰቡን የቅሬታ ድምፅ መነሻ አድርገው ትዝብትና ተቃውሟቸውን ማሰማት ነው።

ባጠቃላይ የኪነ-ጥበብ ስራ ከሚታየው ነባራዊ ሁነት መነሻውን እንደሚያደርገው ሁሉ፤ ለጥናቱ የተመረጡት በሶስቱም የጊዜ ምድቦች የተዘፈኑት ዘፈኖች የየወቅቱን ፖለቲካዊ ሁነትና ማህበረሰባዊ ስሜት የሚገልፁ ሆነው ተገኝተዋል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥም ዘፈኖቹ ከማህበረሰቡ ስሜት በመነሳት በየጊዜያቱ የታዩ ፖለቲካዊ ቀውሶችንና መረጋጋቶችን እንደየሁነቶቹ ልዩነት አስደምጠዋል። ፖለቲካዊ ቀውስና መረጋጋት በታየባቸው በሶስቱም የጥናቱ ጊዜያትም የተለያዩ ፋይዳዎች ነበሯቸው። ከእነዚህ ውስጥም የአብዛኛውን ህዝብ ስሜት በመከተል የትችት የተቃውሞና የውዳሴ ፋይዳ የነበራቸው ሲሆን በዋናነት ዘረኝነት፣ ኢ-ፍትሀዊነት፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ሙስና እና የስልጣን ፍቅር አደገኝነት ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል።

## 5.2. አስተያየት

የወቅቱን ማህበረ ፖለቲካዊ ሁነት ከመግለፅ አንፃር በጥናቱ የተቃኙት ዘፈኖች የጎላ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ዘፋኞች በዘፈኖቻቸው አሁንም ድረስ የህዝብን ስሜት ተከትለው ዘፈኖቻቸውን እየሰሩ እንደሚገኙ በትንተና የተቃኙት ዘፈኖች ማሳያ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት የተቃኙት ዘፈኖች ዘርፈ ብዙው የአገራችን የፖለቲካ ችግሮች የተዳሰሱባቸው ብቻ ሳይሆኑ መፍትሄዎቻቸውም የተጠቆሙባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም ዘፈኖች ከመዝናኛነት ባለፈ የተዘፈኑበትን ዘመን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎችን እንደሚይዙ ስለሚጠቁም ለታሪክም ሆነ ለማህበራዊ መስክ ጥናቶች ጠቃሚ መረጃዎችን ስለሚይዙ ትኩረት ተሰጥቶ ቢመረመሩ መልካም ይሆናል፡፡

በዚህ ጥናት በተመረጡት ዘፈኖች የሚገኙት ሁሉም ይዘቶች አልተተነተኑም፡፡ የተተነተኑት ለርዕሰ ጉዳዩ ተገቢነት ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሌሎች ጥናቶች ሁሉም የዘፈኖቹ ይዘቶች ቢተነተኑ በየጊዜያቱ ለነበሩት ማህበረ-ፖለቲካዊ ጉዳዮችና ለታሪክ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ስለሚኖር ተጨማሪ ጥናቶች ቢካሄዱ መልካም ይሆናል፡፡

# ዋቢዎች

መስፍን ወልደማርያም። (2013)። *ዛሬም እንደ ትላንት?።* አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት ያልተገለፀ።

ሙሀባው ገድፍ። (2011)። *ሚስጢራዊ ሴራ በታላቋ ምድር ኢትዮጵያ።* አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።

ምህረተስላሴ መኮንን። (2009)። "*ፖለቲካን በሙዚቃ።*" *ሪፖርተር ጋዜጣ*፣ ኪንና ባህል አምድ መስከረም 25፣6።

ብርሀኑ ገበየሁ። (1999)። *የአማርኛ ስነ-ግጥም።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

ተስፋዬ ለማ። (2010)። *የኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ።* አዲስ አበባ፣ ሮኅቦት ማተሚያ ቤት።

ታምራት ሀይሉ። (2008)። *አልጋ ላይ የተኛሁ አቅመ ደካማ ብሆንም የጎንደር ህዝብ መንፈሴን ሰባተኛ ሰማይ ላይ አውጥቶታል።* ቁም ነገር መፅሄት። አዲስ አበባ፣ ቢኒያምና በቀለ የህትመት አገልግሎት፣ ቅፅ15 ቁጥር(258)።

____________ ። (2010)። *ኢትዮጵያዊው ‹ሙሴ?› ወደ ቤተ-መንግስት።* ቁም ነገር መፅሄት። አዲስ አበባ፣ ቢኒያምና በቀለ የህትመት አገልግሎት፣ ቅፅ16 ቁጥር(339)።

____________ ። (2010)። *ለ‹ሰው› ግድ ያለው መሪ።* ቁም ነገር መፅሄት። አዲስ አበባ፣ ቢኒያምና በቀለ የህትመት አገልግሎት፣ ቅፅ 16 ቁጥር (347)።

____________ ። (2011)። *ኃይለማርያም ደሳለኝ በታሪክ ፊት ‹ይቅርታ› አልባው የአቶ ኃይለማርያም የሽኝት ንግግር።* ቁም ነገር መፅሄት። አዲስ አበባ፣ ቢኒያምና በቀለ የህትመት አገልግሎት፣ ቅፅ16 ቁጥር (343)።

______________ ፡፡ (2011)፡፡ *የታል? ‹የዜግነት ክብሩ›፡፡* ቁም ነገር መፅሄት፡፡ አዲስ አበባ፣ ቢኒያምና በቀለ የህትመት አገልግሎት፣ ቅፅ16 ቁጥር (362)፡፡

______________ ፡፡ (2011)፡፡ *‹ምዝበራ ከቢሊዮን ወደ ትሪሊዮን› በከፋ ድህነት ላይ የከፋ ዝርፊያ፡፡* ቁም ነገር መፅሄት፡፡ አዲስ አበባ፣ ቢኒያምና በቀለ የህትመት አገልግሎት፣ ቅፅ17 ቁጥር (371)፡፡

የማነ ነጋሽ፡፡ (2008)፡፡ "*መድረክና ሰማያዊ ፓርቲ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በኦሮሚያ ተቃውሞ ላይ ያቀረበውን ሪፖርት ውድቅ አደረጉ*፡፡" *ሪፖርተር ጋዜጣ*፣ *ፖለቲካ አምድ* ሰኔ 19፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ (1993)፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2006)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ናርዶስ ተሻገር፡፡ (2006)፡፡ "በቴዲ አፍሮ ዘፈኖች ላይ የይዘት ትንተና፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡

አንተነህ መርእድ፡፡ (1980)፡፡ "በገበያ ላይ የዋሉ የዘፈን ግጥሞች ይዘት ቅኝት፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1996)፡፡ *የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌትነት አዳሙ፡፡ (2010)፡፡ "ኢትዮጵያና መሪዋ"፡፡ *ሪፖርተር ጋዜጣ*፣ *ፖለቲካ አምድ* መጋቢት 26፡፡

Finnegan, R. (2012). *Oral Literature in Africa*. Topical and Political Songs, p.p. 265-290,

Open Edition books.

Hilina, f. (2020). “Analaysis of Ethiopian `Kignts` Used Dominantly in Popular Songs Produced as Commercial Music in the 1960-1980s: the modern recording songs in Addis ababa.” Department of yared school of music in partial fulfilment of the Requirements for the degree of masters of art in music.” (unpublished).

Kalashnikov, V.G. (2016). “Contextual Approach to Literary Criticism.” The Education and Science Journal; Vol.1, No. 8, P.P. 155-172, Russian Federation.

Masriyah, and et el. (2019). “Analaysis of Associative Meanings in Two Songs Albums of Lorde.” English education jornal.

Muldoon, P. (2013). *Songs and Sonnets.* London; enitharmon press.

Neguss, y. (2018). “Thematic Analysis of Selected Amharic Song Lyrics: A Sociological Approach.” Fulfilment of the requirement of the degree of doctor of philosophy In litrature. (unpubished).

Orgeret, K.S. (2008). *When Will the Daybreak Come?* Popular Music and Political Processes In Ethiopia. P.P 231-244, Nordicom Review.

Patria, and et el. (2013). “The Analysis of Figurative Language in ‹Girl on Fire› Song Lyrics By Alicia Keys.” Professional Journal of English Education, Vol.4, No.2, PP 208-215; Art And Language Study, michgan.

Sheila, D. (1985). *The Craft of Lyric Writing.* Cincinnati; ohio.

Theodor, W. A. (1976). *Introduction to the Sociology of Music.* (translated by e.b. ashton.) New york: theseabury press.

Tyson,L. (2006). *Critical Theory Today: A User-Friendly Guide.* New York: United States Of America.

Yastanti and Sususilawati. (2020). "Imagery in Song Lyrics of Tylor Swift." Jornal of Social Sciences and Humanities, Vol.4. No.2, PP 135-160; Center of Language and Cultural Studies, Surakarta.

# አባሪዎች

## አባሪ 1. ከመስከረም 2008 እስከ መጋቢት 2010 ዓ.ም. የነበረውን ፖለቲካዊ ሁነት አስመልክተው የተዘፈኑ

### ሀ) ናትናኤል አያሌው (ናቲ ማን)- የዘፈን ርዕስ፡- አሁን ተነካሁ

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ መስከረም 1/2009 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 4 ደቂቃ)**

አሁን ተነካሁ (4)

መታወቂያ መጠሪያዬ፣

እናት ኢትዮጵያዬ፡፡ (4)

በሰበብ አስባቡ ከቀየው ለራቀው፣

ያንችን መጥፎ ጭራሽ ማየት ለማይወደው፣

በደስታሽ ሁሌም ቀኑ ለሚበራው፣

ሰላምሽን እንጅ ክፉ አያሰማው፡፡

መታወቂያ መጠሪያዬ፣

እናት ኢትዮጵያዬ፡፡ (4)

----

ገዳይ ገዳይ ብሎ ወገን ያዜመለት፣

ሀገር አትርፎ እንጅ ጠብቆ ከጠላት፣

ማንስ ጀግና ሊሆን ወንድሙን ገድሎ ጥሎት፣

ቀረርቶ ሽለላው ፉከራ አያምርበት፡፡

መታወቂያ መጠሪያዬ፣

እናት ኢትዮጵያዬ፡፡ (4)

----

ኦሮሞን …

ኦሮሞን ሲከፋው አሁን ተነካሁ፣ (2)

አማራን …

አማራን ሲከፋው አሁን ተነካሁ፡፡ (2)

ከአፋር ከሱማሌ ከትግራይ ጋምቤላ፣

ጉራጌ ደቡቡን ህዝቤን በጠቅላላ፡፡
ክፉ ሲነካብኝ ቁጡ ያደርገኛል፣
የሱን ሀዘን መስማት ያንገበግበኛል፡፡
ወገኔን …
ወገኔን ሲከፋው አሁን ተነካሁ (4)

----

የኔ ቤት ሲንኳኳ ካንተ ቤት ዘልቃል፣
አፍንጫ ሲነካ አይንኮ ያነባል፡፡
ሰብስቦ ያቆየን ይህ ነበር ወጋችን፣
ዛሬም በአንድ ይሁን ሀዘንም ደስታችን፡፡
ወገኔን …
ወገኔን ሲከፋው አሁን ተነካሁ (4)
አሁን ተነካሁ … አመመኝ አመመኝ …

## ለ) ይሁኔ በላይ - የዘፈን ርዕስ፡- ሰከን በል

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ጳግሜ 5/2008 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 6 ደቂቃ ከ52 ሰከንድ)**

ኧረ ተው ተው በለው፣
ተው በለው ተው በለው፣
ማንነቴን ብሎ አደባባይ ወጥቶ ባዶ እጁን እያየው፣
ሲያልፍ ለሚያልፍ ቀን ወንድሙን ወንድሙ አልሞ ገደለው፣
ማንነት የራስ ነው፣ ሀይማኖት የግል ነው፣
ሀገር የጋራ ነው ቁልፉና ማሰሪያው ኢትዮጵያዊነት ነው፡፡

ባዲሱ አመት ባዲሱ አመት የለም መሞት፡፡ (2)
አበባ አደይ አበባ አደይ ሞት ለገዳይ፡፡ (2)
በመስከረም በመስከረም ሰላም ሰላም፡፡ (2)
የመስቀል ለታ የመስቀል ለታ በአንድ ገበታ፡፡ (2)
በአዲስ ዘመን በአዲስ ዘመን ይብቃ በለን፡፡ (2)
ያ ወገኔ ዛሬ ምን አለ? ኦሆ አትንኩኝ አለ፣ (2)
ማንነቴን አትንኩ እያለ ኦሆ ሲዘምር ዋለ፣ (2)

ማንነቴን አልሸጥም አለ ኦሆ አያሻኝም አለ። (2)
ስሙት ወገኔን አተኩሱበት፣
እዩት ወገኔን አታፍጥጡበት፣
በአዲሱ አመት አዲስ ብስራት። (2)
ሰከን ሰከን ሰከን፣
ሰከን በል ሰከን፣ (2)
ሰከን ሰከን ሰከን።
ሰከን ማለት ሰከን ነው ጨዋነት፣
ሰከን ማለት ሰከን ነው ጀግንነት።
ወታደሩ ሰከን ሰከን በል፣
አፈሙዙን ሰከን ሰከን አርገው፣
ቃታህንም ሰከን እንዳትስበው፣
ባዶ እጁን ነው ሰከን የሚጮኸው፣
ሰላማዊ ሰከን ወንድምህ ነው።
ሰከን በሉ ሰከን፣
ህዝቤን ተውት ሰከን፣
ድምፁን ስሙት ሰከን፣
አትግደሉት ሰከን።
መንግስት በሀገሩ ሰከን በህዝቡ ላይተኩስ፣
ዘሀጢያት ይኩኑ ሰከን ንጉስ ከማሪዎስ።
ሰከን በል ተው ሰከን፣
ሰከን በል እንጅ ሰከን።
አንዱ ካንዱ ሳይበልጥ አንዱ ካንዱ ሳያንስ፣
አንዱ አንዱን ሳይገለው ደምም ሳይፋሰስ፣
በወላጁ ጥፋት ልጁ ሳይወቀስ።
ተባብሮ ተፋቅሮ በአንድነት መኖሩ፣
ይጠቅመናል እንጅ ምንድን ነው ችግሩ።
ሰከን በል ተው ሰከን፣
ሰከን በል እንጅ ሰከን። (2)

----

ድር እንኳን ቀጭኑ ድር እንኳን ለስላሳው፣

ሲያብር ሲተባበር ይበልጣል ከአንበሳው፡፡

ስማኝ በጥሞና ልንገርህ ወገኔ፣

መለያየት ሞት ነው ላንተም ሆነ ለኔ፡፡ (2)

ሰከን በል ሰከን፣ (2)

ሰከን በልማ ሰከን፣

ሰከን በል እንጅ ሰከን፡፡

ከታሪካዊዋ ከድንቅነሽ አገር፣

ከእምዬ ኢትዮጵያ ከሆደ ቸጉርጉር፣

ቀይና ቀይዳማ ጠይምና ጥቁር፣

ወርቀዘቦ ሆነን አምረን ብንፋቀር፣

እንዴት እንለያይ በቋንቋና በዘር፣

በቋንቋና በዘር፡፡

ሰከን በል ተው ሰከን

ሰከን በል እንጅ ሰከን (2)

የወገን ጥያቄው ክብሩ ተመልሶ፣

በሰላም ለመኖር መግባባቱ ነግሶ፣

በስደት ያለውም ወደ አገሩ ገብቶ፣

በነፃነት ሊኖር እንደልቡ ገብቶ፣

እንደልቡ ወጥቶ፡፡

ተማምሏል ህዝቧ ላንዴና ለሁሌ፣

እልል እልል በሉ እንዲፈታ ህልሜ፡፡

ሰከን በልማ ሰከን፣

ሰከን በል ተው ሰከን፡፡ (2)

እባክህ ጌታዬ ኢትዮጵያን ህዝቦቿን ጠብቃት

የጦር መዝመቻ የጠላት መዛበቻ

የመከራ መካተቻ ከመሆን አድናት

አደራ እምዬን ኢትዮጵያን ጠብቃት፡፡

## ሐ) ጌትሽ ማሞ - የዘፈን ርዕስ፡- ተቀበል 2 (እንከባበር)

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ግንቦት 21/2009 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 6 ደቂቃ ከ33 ሰከንድ)**

አለኝ!!!፣

አለኝ እውነት እውነት አለኝ ሰሚ ባገኝ፣ (2)

አለኝ!!!፣

ከፍቅርሽ ያጣሁት የጎደለኝ ብዙ ነገር አለኝ፣

አለኝ!!!፣

አለኝ እውነት እውነት አለኝ ሰሚ ባገኝ፣ (2)

አለኝ!!!፣

ከፍቅርሽ ያጣሁት የጎደለኝ ብዙ ነገር አለኝ፡፡

በይ ስሚኝማ፣

ስሚኝ በይ ስሚኝማ፣

ስሚኝማ በይ ስሚኝማ፣

ስሚኝ በይ ስሚኝማ፣

ስሚኝማ ስሚኝማ ስሚኝማ፡፡

----

ለኔ እንዳልተፈጠረ ሰው ያላንች ምድር ላይ፣

ልብሽ ከፍቅር ርቆ ለቤቱ ሆነሽ የበላይ፡፡

ይውጣልኝ …

በደልሽን ዛሬ ተንፍሼው፣

ይምጣ የመጣው፡፡

አድምጭኝ …

አዳም ቢፈጠርም ያላማራጭ፣

እኔ አለኝ አቋራጭ፡፡

የኔን ነገር በክፋት ሁል ጊዜ እያየሽው፣

ተይ ብል የርሜን ብናገር ታመሽ አይቻለው፡፡

አውቃለሁ …

እቴ ያንችን አመል ሲሰሙሽ ነው፣

ውስጥሽ ደስ የሚለው፡፡

ተይ ውዴ …

ሁል ጊዜ ያንችን ብቻ ሲሰሙሽ፣

እንዲያው ደስ አይበልሽ፡፡

የቤቱ ምሰሶ ጣሪያው ግርግዳው፣

ባንች ብቻ አይደለም ፀንቶ ያየሽው፡፡

የልብሽን ዙፋን መንበር ባልታደል፣

እኔ አላንስም ለቤቱ ለቤቱ፣

እንከባበር፡፡ (2)

አይ እንገዲህ!!! … አይ!!!

----

የፈረሱን ምግብ ለውሻው ብሰጠው፣ (2)

የኮርቻው ነገር ሰው ሆዱን ቆረጠው፡፡

አንቺ ግፍ አትፈሪም በኔ ቤት ሆነሽ፣ (2)

ዳንቴል ትሰሪያለሽ ለዚያኛው ቤትሽ፡፡ (2)

ፍቅርሽ ቢያሳንሰኝ አንገት ቢያስደፋኝ፣ (2)

መቼ ከፋኝ አልኩሽ ስትከፊብኝ፡፡

አንችን ተመርኩዘው ጊዜን ቢታደሉ፣

አለቃ ሆኑብኝ ዘመዶችሽ ሁሉ፣

ዘመዶ…ችሽ ሁሉ፡፡ (2)

----

መሄድሽ ነው ብየ ጫፍ ደርሰሽ ተመለስሽ፣

ተለያየን ብየ ጫፍ ደርሰሽ ተመለስሽ፣

ሚገርመው አታርፊም ትነካኪኛለሽ፡፡

ዘመናይ ዘመናይ የኔ ዘመንማኒት፣ (2)

ምነው አይደክምሽም ወይ ማዘዝ ቀን ከሌሊት፣

መዘዝ ቀን ከሌሊት ማዘዝ ቀን ከሌሊት፡፡

በልቶት ለሚጠፋው ስራ ተሰማርቶ፣ (2)

ሲኖር አይቻለሁ ሰው ለሆዱ ሞቶ፡፡

እቴ ያንች ነገር ሳስበው ይገርመኛል፣

እንዲያው ያንችስ ነገር ሳስበው ይገርመኛል፣

የሰው ሚስት አግብቼ ምኖር ይመስለኛል፡፡

አይ እንግዲህ!!! … አይ!!! (2)

እንከባበር … እንከባበር (3)

አይ እንግዲህ!!! … አይ!!! (2)

እንከባበር … እንከባበር (4)

አይ እንግዲህ … አይ!!!

## አባሪ 2. ከመጋቢት 24/2010 እስከ መስከረም 2011 ዓ.ም. የነበረውን ፖለቲካዊ ሁነት አስመልክተው የተዘፈኑ

### ሀ) አዲስ ሙላት - የዘፈን ርዕስ፡- ሀገሬን

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ሰኔ 20/2010 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 6 ደቂቃ ከ39 ሰከንድ)**

እህህ እህህ እህህ እህህ …

እኔን ከፋኝ ብልስ ሀገሬን መች ከፋው፣

ወገኔን መች ከፋው፣

ፍቅር አበቀለ ጥላቻ እማይገፋው፣

ጥላቻ እማይገፋው፡፡ (2)

በአቢይ ፆም መያዣው ቢሾም ከመንበሩ፣

ቢሾም ከመንበሩ፣

ሰው ክፉ እንዳይሰራ እንዳይረክስ ሀገሩ፣

እንዳይረክስ ሀገሩ፡፡ (2)

ሲሆን አይደለም ወይ ንጉስ እንደ አገልጋይ፣

ንጉስ እንደ አገልጋይ፣

ሀገር የምትሞቀው የነፃነት ፀሀይ፣

የነፃነት ፀሀይ፡፡ (2)

የሞሪንጋን ቅጠል የተከልኩት በጄ፣

የሽፈራው ቅጠል የተከልኩት በጄ፣

ጤናየን ከነሳኝ ልንቀለው ከደጄ፣

ልንቀለው ከደጁ፡፡ (2)
ለቆረጡት ስጋ ላፈሰሱት ጠጅ፣
ላፈሰሱት ጠጅ፣
ከፋዩ አንተ ነህ በርትተህ ስራ እንጅ፣
በርትተህ ስራ እንጅ፡፡ (2)
ሀገሬን ሀገሬን ይለኛል፣
ዝም ስል ያመኛል፡፡ (2)

----

ለማ ለማ ሲሉኝ አረሙን መስሎኛል፣ (2)
ለካስ ጤና አዳም ነው መድሀኒት ሆኖኛል፣
መድሀኒት ሆኖኛል፡፡ (2)
በፍቅር ተጋግዘው ካልደገፉት በቀር
ካልደገፉት በቀር፣
ትንሽ ጎጆ አይቆምም እንኳን ትልቅ ሀገር፣
እንኳን ትልቅ ሀገር፡፡ (2)
አምናም ያመን ነበር ታች አምናም እንደዛ፣
ታች አምናም እንደዛ፣
ዘንድሮስ ፈስክን የምንፈታው በዛ፣
የምንፈታው በዛ፡፡ (2)
ጳጳስ ቄስ አልጠፋ በሀገር በቤቱ፣
በሀገር በቤቱ፣
ስብሀት እያሉ ምነው የማይፈቱ፣
ምነው የማይፈቱ፡፡ (2)
ዋ ምነው መቻል ምን ይከፋል፣
ሆድ ከሀገር ይሰፋል፡፡ (2)

----

አቢይ አቢይ ሲሉ ያው ያሙን ነው ብዬ፣ (2)
ሰውም አብይ አለው ኧረ እናንተ ሆዬ፣
ኧረ እናንተ ሆዬ፡፡ (2)

ሲነዳን ኖሮ ስንቱ እንክፍ ጋሬጣ፣
ስንቱ እንክፍ ጋሬጣ፣
ይገዛኛል ያልኩት አባት ሆኖኝ መጣ፣
አባት ሆኖኝ መጣ፣
ወንድም ሆኖኝ መጣ፡፡
እንዴት አድሯል አባይ ያ ፈለገ ጣና፣
ያ ፈለገ ጣና፣
ገዴን ያመጣልኝ አርጎ ባለዝና፣
አርጎ ባለዝና፡፡ (2)
መሪ ማለት አብሮ ሲባክን ነው እንጅ፣
ሲኳትን ነው እንጅ፣
እንደ አይን እንደ ጆሮ እንደ እግር እንደ እጅ፣
እንደ እግር እንደ እጅ፡፡ (2)
አይከፋፈልም ሀገር እንደ ቅርጫ፣
አንከፋፈልም በመደብ በቅርጫ፣
መደመር ብቻ ነው ያለን አንድ ምርጫ፡፡ (2)
ሀገሬን ሀገሬን ይለኛል፣
ዝም ስል ያመኛል፡፡ (4)

## ለ) አቡሽ ዘለቀ - የዘፈን ርዕስ፡- አነቃን

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ሀምሌ 3/2010 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 6 ደቂቃ ከ23 ሰከንድ)**

አነቃን … አነቃቃን፣ (4)
አነቃቃን … አነቃቃን፣
አነቃን … አነቃቃን፡፡

----

ባንቺ ሰማይ ጥላ ስር ክፉ ደጉንም አይተናል፣
ሌላ እናት ሀገር የለንም ሲከፋሽም ይከፋናል፣
ባንቺ ሰማይ ጥላ ስር የተስፋ ብርሀን ይታየናል፣
ሌላ እናት ሀገር የለንም ደስ ሲልሽ ደስ ይለናል፡፡
እማማዬ ደስ ሲልሽ ኢትዮጵያዬ ደስ ይለናል፣

እማማ …

ደስ ሲልሽ ኢትዮጵያ ደስ ይለናል፡፡

ኢትዮጵያ …

----

አነቃን … አነቃቃን (2)

አነቃን አንዱ ከአንዱ ሳያንስ አንዱም ከአንዱ ሳይበልጥ፣

ከኔ ወንዝ አይደለህ ከኔ ወንዝ አይደለሽ፣

ብለን ሳንጣላ ብለን ሳንለያይ፣

አገር ማለት እኛ እኛ ማለት አገር ብሎ አበሰረን፣

ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ ነን፣

አነቃን … አነቃቃን፡፡ (2)

----

አነቃን አስተውለን ካየን ታሪክ ሳንረሳ፣

የአብሮነቱን ገመድ ቋጠሮን ሳንፈታ፣

የሚያግባባን ብዙ የሚያስማማን ብዙ፣

ሰፊውን በር ዘግተን ጠባቡን አናንኳኳ፣

ኢትዮጵያዊነቱ ነው ያስተሳሰረን ጎልቶ ይታይ በቃ፡፡

አነቃን … አነቃቃን፡፡ (2)

ላሚቷ ሳትነጥፍ ሳታጣ ምትግጠው፣

ሞፈሩም ሳይጠፋን በሬው ሚጎትተው፣

ይቅር እንባባል ተባባሉ የሚለን ሰው፣

አተን ነው እንጅ ቀድሞ ጥላቻው የነገሰው፣

ከታረሰው ይልቅ እልፍ ነው ያልታረሰው፡፡ (2)

ባንቺ ሰማይ ጥላ ስር ክፉ ደጉንም አይተናል፣

ሌላ እናት ሀገር የለንም ሲከፋሽም ይከፋናል፣

ባንቺ ሰማይ ጥላ ስር የተስፋ ብርሀን ይታየናል፣

ሌላ እናት ሀገር የለንም ደስ ሲልሽ ደስ ይለናል፣

እማማዬ ደስ ሲልሽ ኢትዮጵያዬ ደስ ይለናል፣

እማማ …

ደስ ሲልሽ ኢትዮጵያ ደስ ይለናል።

ኢትዮጵያ …

-----

አነቃን … አነቃቃን (2)

አነቃን ከአርበኞቹ ሀውልት ትንሽ ዝቅ ብሎ

ከዛ ሰፊ ግቢ ሰው ከማይደርስበት

አዲስ ነገር ሰማን ሰምተን ማናውቀውን

ደስታችን ወደር አጣ ፍቅር ያሸንፋል

ከክፋት እንራቅ ከበቀል እንፅዳ

ተዋደን እንኑር የሚል ጀግና መጣ

አነቃን … አነቃቃን (2)

----

አነቃን በሰሜን ደቡቡ

በምስራቅ ምዕራቡ

በሁሉም ተሰማ የመደመሩ ጥሪ

ከእኛም ተሻገረ ተከዜንም አልፎ ሄደ ገሰገሰ

ቀይ ባህርን አቋርጦ ከአስመራ ደረሰ

ኢትዮጵያ

ያ የጥላቻ ግንብ በፍቅር ፈረሰ

አነቃን … አነቃቃን (2)

----

ማነው ማነው ማነው?

ማነው ሚመልሰን?

ማነው ማነው ማነው?

ከዚህ ቀና መንገድ

ማነው ማነው ማነው?

ከዚህ የፍቅር ጉዞ

ማነው ማነው ማነው?

ወደፊት ነው እንጅ

ማነው ማነው ማነው?

እጅ ለእጅ ተያይዞ

ማነው ማነው ማነው?

እንደ አለት ይጠንክር

ማነው ማነው ማነው?

ይብዛ አንድነታችን

ማነው ማነው ማነው?

ዛሬም ነገም ሁሌም

ማነው ማነው ማነው?

ትኑር ኢትዮጵያችን

ማነው ማነው ማነው?

ዛሬም ነገም ሁሌም

ማነው ማነው ማነው?

ትኑር ሀገራችን

ማነው ማነው ማነው?

ዛሬም ነገም ሁሌም

እማማዬ ኢትዮጵያ፡፡

## ሐ) ጌትሽ ማሞ - የዘፈን ርዕስ፡- ተቀበል ቁጥር አራት (4)

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ነሀሴ 29/2010 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 7 ደቂቃ ከ34 ሰከንድ)**

አወይ ጊዜ ደጉ አወይ ጊዜ ዳኛው፣

ስንቱን አሳለፍነው ከፍተን እኛው በእኛው፡፡

አያመጣው የለ እሄው ቀን ከሌት፣

ይንቆለጳጰሳል ኢትዮጵያዊነት፡፡

ገባሽ ገባሽ ውዴ ያኔ ስልሽ፣

ደርሶ አየሽ፡፡

መጣ መጣ ያ ቀን፣

በቃል በቃል አገር ሊድን፡፡

ገባሽ ገባሽ ውዴ ያኔ ስልሽ፣

ደርሶ አየሽ፡፡

መጣ መጣ ያ ቀን፣
ይሄው በቃል አገር ሲድን፡፡
ለካ ያጣነው ፍቅር ነበር፣
እንደ ሰው እንደ አገር፣
እንደሰው እንደ አገር፣
የጎደለን ነገር፣
እኛ ያጣነው ይሄን ነበር፣
እንደ ሰው እንደ አገር፣
እንደሰው እንደ አገር፣
የጎደለን ነገር፡፡

----

ልቤም ቂም አያውቅም ሆዴም ብዙ ይችላል፣
ጣት ቆሰለስ ብሎ ማን ቆርጦ ይጥላል፡፡
ክፋት ለማን ጠቅሞ ክፉ ልሁን እኔ፣
ከፍ ከፍ አድርጌሽ ላኑርሽ በቀኔ፡፡
ሽርሽሮ ሽርሽሮ ነገር አንጆቴን፣
ሊቆርጠው ነበረ እርቆኝ ይሄ ቀን፡፡
እስኪ ላወድሰው ላወዳድሰው፣
ከነሙሉ ክብሯ ስሟን ለጠራው፣
ይሄን ጀግና እስቲ ልጥራው፡፡
ቁሮ ፋኖ ስማ አንተ የአገር አርማ፣
ልጥራው ልጥራው…
ቁሮ ፋኖ ስማ አንተ የአገር አርማ፡፡

----

ከፍ አለ ሰንደቁ ደስታውም ታየኝ፣
ከፍ ሲል ሰንደቁ ልየው ጥሩልኝ፣
ድሮም በሀገሩ ነው ሚለካው ታማኙ፡፡
እናቱ ሲወልዱት አሉት አንድአርጋቸው፣ (2)
ማን ያውቃል የዛሬ ቀድሞ እንደታያቸው፡፡

በአንዱአለም በእስክንድር እውነትን ፍለጋ፣ (2)
ጨልሞ አልቀረም ና ብርሀኑ ነጋ፡፡
ናናዬ ናና ናና ናና፣
ናናዬ ናና ናና ጀግናው ናና፣
ካሰገደደው ናና ይዞ ምንሽር ጀግናው ናና፣
ለኔ ይልቃል ናና የያዘ ፍቅር  ጀግናው ናና፣
መጣው መጣው ቢል ናና ድምፁን አብዝቶ ጀግናው ናና፣
የሚሆን የለም ናና አሁን ተፈጥሮ ጀግናው ናና፣
ናናዬ ናና ናና ናና፣
ናናዬ ናና ናና ጀግናው ናና፡፡
ደመቀ አገሩ ገዱ ቢቀናቸው፣ (2)
የለማ ሆነና አቢይ ጉዳያቸው፡፡
እንዴት ነው ወገኔ እንዴት ነው ኤርትራ፣
ገዛ አባ ሻወል እንዴት ነው አስመራ፣
የከረመ ፍቅር አለ ከኔ ጋራ፡፡

----

ያ በቀለ ገርባ መራራ ጉዲና፣ (2)
ዮሙ ሲሂንደገኑ ኢሲን አባ ሴና፡፡
(Yomuu sihindaganuu isiin abba senaa)
እንግዲህ ካደለን የምህረቱን አመት፣
እንግዲህ ከታደልን የምህረቱን አመት፣
ተዋዶ መኖሩን በይ እንወቅበት፡፡
ያልሽው ሁሉ ሲሆን ወይ ሲጎል ከቃልሽ፣ (2)
ባደራ ይጠራል የኔ ስም በስምሽ፡፡
ናናዬ ናና ናና ናና፣
ናናዬ ናና ናና ጀግናው ናና፣
በል ምራው ለማ ናና ቄሮን ከፊቱ ጀግናው ናና፣
ድሮም ገዱ ነው ፋኖ ለእናቱ ጀግናው ናና፣
የደመቀ ነው ናና የአብይ ጉዳይ ጀግናው ናና፣

በኢትዮጵያዊነት ናና ፍቅር የበላይ ጀግናው ናና፣

ናናዬ ናና ናና ናና፣

ናናዬ ናና ናና ጀግናው ናና፣

ካስገደደው ናና ይዞ ምንሽር ጀግናው ናና፣

ለኔ ይልቃል ናና የያዘ ፍቅር  ጀግናው ናና፣

መጣው መጣው ቢል ናና ድምፁን አብዝቶ ጀግናው ናና፣

የሚሆን የለም ናና አሁን ተፈጥሮ ጀግናው ናና፣

ናናዬ ናና ናና ናና፣

ናናዬ ናና ናና ጀግናው ናና።

## አባሪ 3. ከመስከረም 2011 እስከ 2013 ዓ.ም የነበረውን ፖለቲካዊ ሁነት አስመልክተው የተዘፈኑ

### ሀ) አዲስ ሙላት - የዘፈን ርዕስ፡- ሀገሬን ቁጥር (2)

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ህዳር 10/2010 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 7 ደቂቃ ከ3 ሰከንድ)**

አየ ጉድ አየ ጉድ እናያለን ገና፣

ጤና ይስጠንና፣

አየ ጉድ አየ ጉድ እናያለን ገና፣

እድሜ ይስጠንና።

እንዴት ነሽ ልበልሽ እንደምን ከርመሻል፣ (2)

አንቺ ምስኪን ሀገር ኧረ እንዴት ይዞሻል፣

እስከዛሬ ድረስ ስትበይ ኖረሻል፣

አንቺ ምስኪን ሀገር ኧረ እንዴት ይዞሻል።

----

ቃኘሁ ጠረጠርኩት የፈጣሪን መምጫ፣ (2)

ሲበለት እያየሁ ሀገር እንደ ቅርጫ። (2)

የሰሞን እንቅልፌ በቅዠት ታትሞ፣ (2)

መአት ያሳየኛል ሀገር እርቃን ቆሞ። (2)

ወልቃይት ሁመራ እንኳን ዘር ተምሶ፣ (2)

ይጥላል በጥላ እንደ ደጋ ኮሶ። (2)

ዛሬ ላይ አይሎ ለአሞራም ተረፈ፣ (2)
ክንፉን ሲነቅል ዋለ እያርገፈገፈ፡፡ (2)
ጠበቃሽ ማን ይሆን?፣
እማኝሽ ማን ይሆን?፣
ዋስሽስ ማን ይሆን?፣
እማኝሽ ማን ይሆን?፣
የነበረሽ ሁሉ እንዳልነበር ሲሆን፡፡ (3)
አየ ጉድ አየ ጉድ እናያለን ገና፣
ጤና ይስጠንና፡፡
እንዴት ነሽ ልበልሽ እንደምን ከርመሻል፣ (2)
የአባቶችን ፀሎት አምላክ ሰምቶልሻል፣
ጨለማው ተገፎ ዛሬ ነግቶልሻል፣
እንዴት ነሽ ልበልሽ እንደምን ከርመሻል፣ (2)
የእናቶችን ፀሎት አምላክ ሰምቶልሻል፣
ጨለማው ተገፎ ዛሬስ ነግቶልሻል?፡፡

----

ቃላባይ ወንዝ ነው ሲከዳን የኖረ፣
ዛሬ በጋ መቶ አባይ ተሸበረ፡፡
ይሸሻል ይላሉ ወንዝም እንደሰው፣
ሰንሰለቱ ታይቶት ሆድ እየባሰው፣
አጀብ አዝመራየን ምን ጳጳስ ጎበኘው፣
እንዴት ያለ ፀበል ምን እምነት አገኘው፣
ደምቆ ተንዠርጎ ተበላ ስመኘው፣
እንደ ሽምብራ እሾክ ሲጠረጠር አየሁ፡፡
የቅሊንጦ መቅደስ አያሻም መነኩሴ፣ (2)
ሲያሰለጥን ያድራል ሹሙን በቅዳሴ፡፡ (2)
እሱን በመናፈቅ ፀንቷል ፀሎታቸው፣ (2)
ስለታቸው ሰምሮ ይመጣል ጌታቸው፡፡ (2)
ጠበቃሽ ማን ይሆን?፣

እማኝሽ ማን ይሆን?፣

ወዳጅሽ ማን ይሆን?፣

ጠላትሽ ማን ይሆን?፣

የነበረሽ ሁሉ እንዳልነበር ሲሆን። (2)

እናያለን ገና ጤና ይስጠንና፣

ይቀጥላል ገና ብቻ እንሁን ደህና።

ሀገሬን ሀገሬን ይለኛል፣

ዝም ስል ያመኛል። (4)

## ለ) አቡሽ ዘለቀ - የዘፈን ርዕስ፡- ታመናል

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ የካቲት 7/2012 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 5 ደቂቃ ከ59 ሰከንድ)**

ታመናል ታመናል ታመናል በጣሙን፣

ሀያ ሰላሳ አመት ፊደል ቆጥረን አውቀን፣

የተሻለ ሀሳብ እንዴት ማምጣት አቃተን፣

ዛሬም የዘር ሀረግ ገመድ የሚጠልፈን፣

አዎ ታመናል ታመናል ታመናል በጣሙን። (2)

----

ሁሉም የየራሱን ገንብቶ ካጠረ፣

ሁሉም የየራሱን ዘር ከመለመለ።

የአብሮነትን ካባ ማን ሊያለብሰን መልሶ፣

ለሩብ ክፍለ ዘመን የበረደን መች አንሶ።

ከየትኛው ክልል ነው ከየትኛው ከተማ፣

ከዚያኛው ሰፈር ነው ከዛ ጎሳ መጣ፣

መቼ ነው እሚለቀን? እናስተውል ለአንድ አፍታ፣

ይራቀን እንራቀው ይህን ክፉ በሽታ።

ታመናል ...

እርም እርም እርም እርም፣

ስንት ሽህ አመት ልኖር፣

እርም እርም እርም እርም፣

ከህሊናየ እርቄ፣

እርም እርም እርም እርም፣

በቀል ተንኮል ክፋት ለትውልድ አውርሼ፣

እርም እርም እርም እርም፣

ከጎዳናው ልውደቅ ልለምን አንጥፌ፣

እርም እርም እርም እርም፣

ሆዴን ከምሞላው ሰው ከሰው አራርቄ፣

ታመናል ታመናል ታመናል በጣሙን፣ (3)

ታመናል ታመናል ታመናል በጣሙን፣

ሀያ ሰላሳ አመት ፊደል ቆጥረን አውቀን፣

የተሻለ ሀሳብ እንዴት ማምጣት አቃተን ፣

ዛሬም የዘር ሀረግ ገመድ የሚጠልፈን፣

አዎ ታመናል ታመናል ታመናል በጣሙን፡፡ (2)

----

ምክንያት እየፈለግን ሰበብ እየፈጠርን፣

በትንሽ ትልቁ ጦር እየተማዘዝን፣

አይደለም እሚበጀን አይደለም እሚተርፈን፣

በቀን ሶስቴ እንኳን መብላት እያቃተን፡፡

የማን ዘር ነው ከእሳት ከመብረቅ የተሰራ፣

የማን ዘር ነው ከጭድ ከሰበዝ የተሰራ፡፡

አንዱን እያሳነስክ አንዱን አታግዝፈው፣

ሆዱ አምላኩ አትሁን ፍቅር ስበክ አንተ ሰው፡፡

ታመናል …

እርም እርም እርም እርም፣

የት ነው የተማሩት፣

እርም እርም እርም እርም፣

እነኛ የአድዋ ጀግኖች፣ (2)

እርም እርም እርም እርም፣

እነኛ የአድዋ አርበኞች፣

እርም እርም እርም እርም፣

ከራሳቸው አልፈው፣

እርም እርም እርም እርም፣

ምሳሌ የሆኑት ለአለም፣

እርም እርም እርም እርም፣

ለሰው እንጅ ለዘር፣

እርም እርም እርም እርም፣

ስለታገሉ አይደለም፣

ታመናል ታመናል ታመናል በጣሙን፡፡ (2)

## ሐ) ጌትሽ ማሞ - የዘፈን ርዕስ፡- ተቀበል ቁጥር አምስት 5 (ሳቢው)

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ግንቦት 12/2011 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 6 ደቂቃ ከ23 ሰከንድ)**

አሜን የአሜን ልጅ አሜን የወለደው፣ (2)

የዘራው ይፀድቃል ያድጋል የወለደው፡፡

አሜን ብዬ ነበር እባክህ እርዳኝ ጓዴ፣ (2)

የአባቶች ምርቃት እርግማን ነው እንዴ?፡፡

ሰሮ ቴታ ደሮ ኢትዮ አሜን፣

ሰሮ ዲቴ አሜን፣

ሆራ አሜን ቡላ… አሜን፣

ቢይ ኬኝ ነጋ ሀታቱ አሜን፣

የረገጣችሁት ምድር ትባረክ አሜን፣

ተባረኩ ልጆቼ አሜን፣

ሰላም ያብክን አሜን፣

ፍቅር ያብክን አሜን፣

እኛክ  ያብክን አሜን፣

ተባረኩ አሜን፣

ሰላምክም ይብዛ አሜን፣

ብሩክ ሁኑ አሜን፡፡

ይሁን ይሁን ይሁን ይሁን፣

መቼ? … አሁን፡፡

----

ላንች የቀለለሽ ለኔ ከባድ ነው ከባድ ነው፣
ይሄ ነው እንግዲህ እወቂው፡፡
ፍቅር ያለቦታው ቢውል ከአፍሽ ከአፍሽ፣
ከበደኝ ልኖር አብሬሽ፡፡
ሳቢው ሳቢው ኧረ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው እስኪ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው ኧረ ሳቢው፣
ፍቅርን ሳቢው ወደ ልብሽ ሳቢው፡፡

----

ይሁን ይሁን ካሉ ፀብ የለም በሰው ልጅ አውቃለሁ፣
አምናለሁ አንች የነካሽው የማይነካ ነው፣
ደሞስ ምን ነበረን የኔና አንች ብለን ምንቆጥረው፣
ምንቆጥረው እንኳን የጁ ቀርቶ እኔስ ያንች አይደለው፣
መልካም ስረው እንጅ ቋሚ እሚያደርገው፣
ነፍሱ የወጣች ጊዜ ስሙ ሬሳ ነው፡፡
ህመምሽ ህመሜ ሆኖ ይኑር እንጅ፣
እኔ እወድሻለሁ በይ ነገር አብርጅ፡፡
ሳቢው ሳቢው ኧረ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው እስኪ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው ኧረ ሳቢው፣
ፍቅርን ሳቢው ወደ ልብሽ ሳቢው፡፡

----

ጉዲዲዲዲዲ....
እያደር ጉዲዲ.... (2)
አብረን ፀሎት ይዘን ወደ አምላካችን፣
በዛ በመከራ ተጨንቃ ነፍሳችን፡፡
ቢፈርስ እያሪኮ የክፋቱ ግንብ፣
ተለያይቶ አደረ የኔም ያንችም ልብ፡፡
ቆመን ባደባባይ ሲሰማ ድምፃችን፣

ተዋልዶ እንዳልኖረ አንድ ላይ ደማችን፡፡
እንዳልመሰከርን ደርሰን ቀኑ ላይ፣
አይዘልቁም እንዳሉት ላንዘልቅ ነው ወይ?፡፡
ግፋ ቢል አዶራ አንሳድና አካፋ፣
ይላል ያገሬ ሰው አምርሮ ሲከፋ፡፡
እንደው እንደው ሳንል በሆነው ባልሆነው፣
ብርሀን ሳለ ቀኑ እንዳናጨልመው፣
ሳቢው ሳቢው ኸረ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው እስኪ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው ኸረ ሳቢው፣
ፍቅርን ሳቢው ወደ ልብሽ ሳቢው፡፡

----

ዛሬ በማን ልፍረድ ማን ይሁነን ምክንያት፣
ዘርተን እያደርን ምድር ሙሉ ክፋት፡፡
የሞተው ወንድሜ የገደለው አባትሽ፣
ሀዘን አልወጣ አለ ከዘጠኝ ወር ቤትሽ፣
እኔ ትሻል ብዬ ስም ባወጣልሽ፣
ሰማሁ ትብስ ብለው ሰዎች ሲጠሩሽ፡፡
ኸረ ተይ አይሆንም ባንችም ከደገመኝ፣
እናቴም ልጅ የላት እኔም ወንድም የለኝ፡፡
ግፋ ቢል አዶራ አንሳድና አካፋ፣
ይላል ያገሬ ሰው አምርሮ ሲከፋ፡፡
እንደው እንደው ሳንል በሆነው ባልሆነው፣
ብርሀን ሳለ ቀኑ እንዳናጨልመው፣
ሳቢው ሳቢው ኸረ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው እስኪ ሳቢው፣
ሳቢው ሳቢው ኸረ ሳቢው፣
ፍቅርን ሳቢው ወደ ልብሽ ሳቢው፡፡

አብርጅ በሷ

ነገር አብርጅ

አብርጅ አብርጅ

## መ) ጌትሽ ማሞ - የዘፈን ርዕስ፦ ዙፋኑ ነው መሰል

- **ዘፈኑ የወጣበት ጊዜ ጥቅምት 3/2012 ዓ.ም. (የጊዜ ቆይታ 7 ደቂቃ ከ30 ሰከንድ)**

ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም፣ (3)

ያለምንም ደም። (2)

በልባቸው አምነው በአፋቸውም ጭምር፣

ወተው ካደባባይ ሲሆኗት ምስክር።

በጠላቶቿም ፊት በድል ትቆማለች፣

በውድቀታቸው ቀን ተስፋ ስለሆነች፣

ትላንትም ትልቅ ዛሬም ትልቅ ነች፣

ኢትዮጵያ እኮ ነች።

አዲስ አይደለም ለሷ መከራ፣

ያልፋል አትፍራ።

----

እውነት ከኛ እርቆ ጠፍቶ መነጋገር፣

ሳይኖር ለምስኪኑ ጠብ ያለለት ነገር።

በጎጥ እያሰቡ በእንብላው መንፈስ፣

ዛሬም ሊቆምሩ በድሀ ልጅ ነፍስ።

ቆርጠው ተነስተዋል ሚያጠፉን መስሏቸው፣

ገድለውን ሊያበዙን እንደልማዳቸው።

ነፍስ ባላወቁ በህፃን ባዛውንቱ፣

በተማሪ ሬሳ አትሙላ ምድሪቱ።

ታገስ ያገሬ ሰው መታገስ ይሻላል፣

ጨለማን ያለፈ ብርሀንን ያያል።

ዙፋኑ ነው መሰል ያለበት አባዜ፣

እንዳይሆን ያረገው ሁሉም ባለጊዜ።

ሴረ ቀባ ኦሮሞን ሴረ ቀባ። (2)

ሴረ ቀባ ኦሮሞ ሴራፍ ሄረ ጉቱ፣
ቢየ ኢጃሩ መሌ ቢየ ዲጉ ሂንቤኩ፣
ኢልማን አባ ገዳ ሴና ዳንጋ ቀቡ፣
ቢየ ኢጃረተኒ ኦርማፍ ፊረ ተኡ፡፡

----

ካልኩ ወደኋላ በሀገሬ ጉዳይ፣
የጀግኖች አጥንት እሾህ ሆኖ ይውጋኝ፡፡ (2)
እኔም በእናቱ ጠርቼሀለሁ፣
ብትዘገይ እንኳን እቀየማለሁ፡፡ (2)
ይድፋው አንገቱን አይኑም ደም ይልበስ፣
ቆሞ እያየት ኢትዮጵያ ስትነግስ፡፡
እንስፍስፍ አርጎ ህመሟ ቢያመኝ፣
አባቴ አርበኛ እኔ ወታደር ነኝ፡፡

----

ጥራት ጥራት ጥራት፣
ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ፣
ክብሬ ናት ክብሬ፣
እናቴ ናት ክብሬ፣
ማሪኝ በላት እሷም መሀሪ ናት፣
እናት እናት እናት፡፡
እንኳን ለአንድነቷ የፈሰሰው ደሙ፣
እንኳንስ ለክብሯ የረገፈው አፅሙ፣
ሲጠሩበት ጌጥ ነው የጀግና ሰው ስሙ፡፡
በሀገሬ ሰማይ በኢትዮጵያ ምድር፣
ዋጋው ከፍ ያለ ነው ሲኖር በፍቅር፡፡
አንድ ህፃን ነበረች ድንገት በጎዳና፣
ወድቃ የተገኘች ነገሌ ቦረና፤፤
እናቷም ሆነቻት ደረቅ ጡት አጥብታ፣
ዘሯን ሳትቆጥር ሰው መሆኗን አይታ፡፡

በቤንሻንጉል ወርቅ በትግራይ ሹሩባ፣
በአማራ ነጭ ጤፍ ደግሳ አስውባ፡፡
በደቡብ ሰው ሸማ በሀረሪ ሰንጋ፣
ልጇን ለሱማሌ ስትሰጥ በአሀይሎጋ፡፡
በአፋር በጋምቤላ ነበረ ታጅባ፣
ተለያይተን ስታይ እንዴት አታነባ፡፡

----

ዛሬም አንሰስትም እነሆድ አምላኩ፣
ሰላም ስጡንና ያሻችሁን እንኩ፣
ዞሮ መግቢያየን ግን ኢትዮጵያን አትንኩ፡፡
በላ ልበልሀ…
ስማ ስማ…
ታማኙ አያቴ ከመንዝ ተነስቶ፣
በቾ ተቀመጠ ኦሮሞ አግብቶ፡፡
ከዛች ከኦሮሞ ሁለት ይወልድና፣
እነሱም ለአቅመአዳም ሲደርሱ እንደገና፣
የሶዶ ጉራጌ ሴቷም ታገባና፣
ከትግሬ ተጋብቶ ወንዱም ወለደና፡፡
ከነዛ ልጆቹ እኔ ነኝ አንዱ፣
ሁሉም ሰው ይለኛል ጌትዬ ዘመዱ፡፡
እስኪ እኔን ፍረዱኝ ዘሬ ምን ሊባል ነው፣
ዘሬን አጠይቁኝ ዘሬ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡
በዘር በሀይማኖት ከፍሎ በጎሳ፣
ቆጥሮ ሊሸጠኝ ቆርጦ ሲነሳ፡፡
አባቴ ይሙት! እጋፈጣለሁ፣
ኢትዮጵያ ትቅደም ብዬ እሞታለሁ፡፡